# የጳውሎስ ሕይወትና

## ትምህርቱ

ከሎዊስ ብክስቢ

# ማውጫ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ ስለ ጳውሎስ | 1 |
| 2. | የጳውሎስ መለወጥና የመጀመሪያ አገልግሎቱ | 5 |
| 3. | የመጀመሪያ የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 10 |
| 4. | የኢየሩሳሌም ጉባኤ 49 ዓ.ም. | 17 |
| 5. | ሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 22 |
| 6. | ሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 35 |
| 7. | ጳውሎስ የደረሰበት መከራ | 45 |
| 8. | ጳውሎስ ስለ መከራ የሰጠው ትምህርት | 49 |
| 9. | የሰው መሠረታዊ ፍላጎት– ጽድቅን በእምነት ማግኘት | 53 |
| 10. | የቤተ ክርስቲያን አመራር | 59 |
| 11. | ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ማንነት ያቀረበው ትምህርት | 63 |
| 12. | የኦሪት ሕግና ብሉይ ኪዳን | 70 |
| 13. | መናፍቅነት | 74 |
| 14. | ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ያስተማረው ትምህርት | 81 |
| 15. | ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር | 87 |
| 16. | የቤተ ክርስቲያን ወደ ብስለት መድረስ | 99 |
| 17. | የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት | 95 |
| 18. | መንፈስ ቅዱስና የወንጌል ስርጭት | 104 |

# የጳውሎስ ሕይወት፥ አገልግሎቱና መልእክቱ

## ትምህርት 1

## መግቢያ ስለ ጳውሎስ

የትምህርቱ ዓላማ፡- ሳውል የተባለውንና በኋላም ሐዋርያ የሆነውን ጳውሎስን ለማስተዋወቅ ነው። ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት ምን ዓይነት ሰው እንደነበረ፥ ከመለወጡ በፊት ለአገልግሎቱና ለመልእክቱ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዘጋጀው ለመረዳት እንድንችል ነው።

## 1. የጳውሎስ የትውልድ ስፍራ - ጠርሴስ

ጠርሴስ የኪልቂያ ዋና ከተማ ነበረች። በዚያን ጊዜ ኪልቅያ ከሶርያ ክፍላተ አገራት አንዱ አውራጃ ነበረች። ጠርሴስ በውስጧ ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖሩባት በስድኑስ ወንዝ አጠገብ የነበረች ከባሕር ዳርቻ 16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ነበረች። ምሥራቅና ምዕራብን የምታገናኝና መናኸሪያ ከተማ ነበረች። በከተማዋ ውስጥ ግሪኮችና ሮማውያን ይኖሩባት ነበር። በጠርሴስ ከተማ ውስጥ አይሁዶችም እጅግ ትልቅ የሆነ ቅኝ ግዛት ነበራቸው። በጳውሎስ ዘመን ጠርሴስ የግሪኮችና የሮማውያን ሥልጣኔ የሰፈነባት ከተማ ነበረች።

ጠርሴስ በተጨማሪም ታላቅ የባህልና የትምህርት ማዕከል የሆነች ከተማ ነበረች። የከተማዋ ዩኒቨርስቲ በጊዜው ከነበሩት ከማናቸውም ዩኒቨርስቲዎች የበለጠ እንደነበር ይነገራል። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚማሩትም ለመማር ጉጉት ያላቸው የአገሪቱ ተወላጆች ነበሩ። ይህች ከተማ የግሪክና የሮም ግዛት ለሆነችው ክፍለ ዓለም ወንጌልን ላስተዋወቀው ለጳውሎስ አስፈላጊ የሆኑ የማኅበረሰብ፥ የመንግሥታዊ አስተዳደርን፥ የአእምሮ ብስለትንና የሃይማኖትን ትምህርቶች በሚገባ አስተምራዋለች። ጳውሎስ የጠርሴስ ዜጋ በመሆኑ ይመካ ነበር (የሐዋ. 21፡39)።

## 2. የጳውሎስ የትምህርት ደረጃ

በአይሁድ ሕግ አንድ ልጅ አምስት ዓመት ሲሞላው የአይሁድን መጻሕፍት ያጠናል፥ በአሥር ዓመቱ ሕጋዊ ባህልን ያጠናል። ጳውሎስ እነኚህን ትምህርቶች ተምሯል።

አይሁዳዊ የሆነ ልጅ በአሥራ ሦስት ዓመቱ «የትእዛዝ ልጅ» ይባላል። በዚያን ጊዜ የአሪት ሕግጋትን በሙሉ እጠብቃለሁ ብሎ ቃል

ይገባ ነበር። ችሎታ ያላቸው ልጆችም ወደ ረቢዎች ትምህርት ቤት ገብተው ብዙ ትምህርት ባላቸው ምሁራን እንዲማሩ ይደረግ ነበር።

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በገማልያል ሥር ትምህርቱን መከታተል የጀመረው በአሥራ ሦስት ዓመቱ ሳይሆን አይቀርም (የሐዋ. 22፡3)። በኢየሩሳሌም ትኖር ከነበረችው ባለትዳር እኅቱ ጋር ተቀምጦ ይሆናል (የሐዋ. 23፡16)።

አንድ ጥንታዊ የአይሁዶች አነጋገር «ማንኛውም ሰው ልጁን ሥራ ካላስተማረው ዝርፊያን አስተማረው» ማለት ነው ይላል። የአይሁድ ባህል የሥራን ክቡርነትና መልካምነት ስለሚያስተምር አይሁዶች ለወጣቶቻቸው ማሰብንና በእጃቸው መሥራትን ያስተምሯቸዋል። ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ ይህ ትምህርት ጠቅሞት እንደነበር አረጋገጠ።

ጳውሎስ ድንኳን መስፋት ተምሮ ነበር። በኋላም ጳውሎስ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር በሚኖርበት ጊዜ ድንኳን እየሰፋ የዕለት ኑሮውን በማሸነፍ ወንጌልን ለመስበክ ችሏል (1ኛ ቆሮ. 4፡11-12)።

ጳውሎስ «ከዕብራውያን ዕብራዊ» ነበር (ፊልጵ. 3፡5፥ 2ኛ ቆሮ. 11፡22፤ የሐዋ. 22፡3)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ጳውሎስ በመጀመሪያ የምንረዳው ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ ነው። እስጢፋኖስ ሲወገር ጳውሎስ በአካባቢው ቆሞ ነበር (የሐዋ. 7፡58)። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የነበሩትን ክርስቲያኖች ከየቤታቸው ጎትቶ በማውጣት ያሳስራቸው ነበር፥ በደማስቆ ያሉትንም ክርስቲያኖች አስሮ ለማምጣት አቅዶ ነበር (የሐዋ. 9፡1-2)።

እንደ አይሁዳውያንና እንደ ሳውል አስተሳሰብ የእስጢፋኖስ መልእክት ስሕተት ነበር። አይሁዶች መሢሁ በቅርብ ጊዜ እንደሚመጣ ያምኑ ነበር። መሢሁ መጥቶ እስራኤልን አንድ እንዲያደርግ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ክርስትና በመካከላቸው ያመጣው መከፋፈል የመሢሁን መምጣት ያዘገየዋል የሚል ግምት ነበራቸው። ጳውሎስ በአይሁዶች መካከል መከፋፈልን ያመጣው ይህንን ትምህርት የሚቃወመው በቅንነትና በበጎ አስተሳሰብ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ተግባሩን ሙሴ ወይም ፊኒያስ ካደረጉት ጋር ያመሳስለው ነበር (ዘኁ. 25፡1-5፤ 26፡1-15)። ጳውሎስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ200 ዓመት በፊት ከሀሲዲም አስተዳዳሪዎች አንዱ የሆነውን የቀናተኛው የማታቲያስን አሳብ በምሳሌነት ሳይከተል አይቀርም።

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው በልጅነቱ ስለነበር ወደ ጠርሴስ ዩኒቨርሲቲ መግባቱን አናውቅም፤ ነገር ግን ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ ጠርሴስ በቆየባቸው ዓመታት ውስጥ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ተምሮ ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርትና ጽሑፎቹ የተማረ ሰው እንደነበር ያመለክታሉ።

## 3. የጳውሎስ ስም

ጳውሎስ «ከእስራኤል ትውልድ፥ ከብንያም ወገን» ነበረ (ፊልጵ. 3፡5)። ስሙም ጳውሎስ ከመባሉ በፊት ሳውል ነበር» (የሐዋ. 13፡9)።

ሳውል የዕብራውያን ስም ሲሆን ትርጕሙ «በልመና የተገኘ» ማለት ነው። ይህ ስም የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ ስም ነበር።

ጳውሎስ ሮማዊው ስሙ ሲሆን ትርጕሙም «ትንሽ» ማለት ነው።

## 4. የጳውሎስ ሮማዊ ዜግነት

የጳውሎስ ቅድመ–አያቶች ከተበተኑት አይሁዶች ጋር የተበተኑ ሳይሆኑ አይቀሩም። የጳውሎስ አባት የሮማዊ ዜግነት ነበረው፤ ሆኖም ይህን ዜግነት እንዴት እንዳገኘ አይታወቅም። የሮም መንግሥት የተገዙትን ሰዎች የበለጠ ታማኝ እንዲሆኑ የሚያደርገው የሮማዊ ዜግነት በመስጠት ነበር። ይህ የሮማዊ ዜግነት በብዛት የሚሰጣቸው በሮም ውትድርና ክፍል አገልግለው የአገልግሎት ጊዜያቸውን ለፈጸሙት ነበር። ጳውሎስ የሮማዊ ዜግነቱን ያገኘው ከአባቱ በመውረስ ነበር፤ የጳውሎስ አባት የሮማዊነት ዜግነታቸውን ያገኙት በውትድርና አገልግሎት ሳይሆን አይቀርም።

ጳውሎስ በሮማዊ ዜግነቱ ምክንያት የሮም ግዛት በሆኑት አገሮች ሁሉ ዜጋ ነበር። ይህም አንዳንድ ጊዜ ሊፈጸምበት ከሚታቀደው ሕገወጥ ድርጊት ይከላከልለት ነበር (የሐዋ. 16፡37–39 እና 22፡29)። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተባቸው ብዙዎቹ በታዎች በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር ነበሩ፤ ለምሳሌ የጲስድያንዋ አንጾኪያ፥ ፊልጵስዩስና ቆሮንቶስ። ጳውሎስ የሮማውያንን ሕግና ባህል ማወቁ ወንጌልን ለሮማውያን ለማቅረብ ጠቅሞታል። ለምሳሌ ስለ ጉዲፈቻ ልጆችና ሰለ ወራሽ ልጆች በማስመልከት በሮማውያን ባህል ውስጥ ያሉትን ማብራርያዎች ይጠቀማል።

ጳውሎስ የላቲን ቋንቋንም ሳይናገር አይቀርም። የሮማዊ ዜግነቱና እውቀቱ በነገሥታትና በአስተዳዳሪዎች ፊት እንዲቀርብ ከማስቻሉም በላይ የወንጌልን ምስክርነት በድፍረት እንዲናገርና እነርሱም በአክብሮት እንዲያዳምጡት አድርጎታል።

በባህሉ መሠረት፥ የሮማዊ ዜግነቱ ጳውሎስን በመስቀል ላይ ከመሞት አትርፎታል። ከዚህም የተነሣ ጳውሎስ በሰይፍ ተሰይፎ ሞተ።

## 5. ጳውሎስ ሚስት አግብቶ ነበርን?

ጳውሎስ ሚስት ያለማግባቱን በ1ኛ ቆሮ. 7፡8 በግልጽ አመልክቶአል። ይሁን እንጂ ጳውሎስ በአይሁድ ኅብረተሰብ ውስጥ ትልቅ ሹመትና ሥልጣን የነበረው ሰው ነበር (ፊልጵ. 3፡5፤ ገላ. 1፡14፤ የሐዋ. 7፡58፤ 9፡1)። ለአይሁድ አስተዳዳሪዎች ሸንጎ አባል ለመሆን ትዳር መያዝ አንዱ መመዘኛ ስለ ነበረ ጳውሎስ ሚስት ካላገባ የሸንጎ አባል አልነበረም ማለት ነው። ምናልባትም ጳውሎስ ሚስቱ የሞተችበት ሆኖ፥ ወደ ቆሮንቶስ መልእክቱን በጻፈ ጊዜ ደግሞ ያላገባ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የሸንጎ አባል ለመሆኑም ፍጹም የሆነ ማረጋገጫ የለንም።



## ማጠቃለያ

ሳውል ፍጹም የአይሁድ ባሕርይ የሚያንጸባርቅ፥ የአባቶቹን ባህል በሚገባ የተማረና የእስራኤልን ሕዝብ የሚከፋፍል መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም የስሕተት ትምህርት ለመቃወም የሚቀና ሰው ነበር (ፊልጵ. 3፡4-6)። ይሁን እንጂ የእርሱ ቅንዓት እውነትን ከመደገፍ ይልቅ እውነትን የሚቃወም ነበር።

ሳውል የተወለደበት አካባቢና የሮማዊ ዜግነቱ ከግሪክ-ሮማዊ ክፍለ ዓለም ወይም ቅኝ ግዛት ጋር አስተዋውቆታል። ይህም በኋላ ለሚጠራበት አገልግሎት በጣም አስፈላጊ የሆነ ዝግጅት ሆኖታል።

# ጥያቄዎች

1. ሳውል የተወለደበትን የጠርሴስ አቀማመጥ ግለጽ።
2. ጳውሎስ የአይሁድ ትምህርት የተማረበትን ሦስት ወቅቶች ግለጽ።
3. ጳውሎስ የድንኳንን ሥራ የተማረው ለምን ነበር?
4. ጳውሎስ በሮማዊ ዜግነቱ ምን ጥቅም አገኘበት?
5. «ሳውል» የሚለውንና «ጳውሎስ» የሚለውን የስም ትርጉም ስጥ።

# ትምህርት 2

## የጳውሎስ መለወጥና የመጀመሪያ አገልግሎቱ

የትምህርቱ ዓላማ፡- እግዚአብሔር ጳውሎስን ያዳነበትንና ለአሕዛብ መልእክተኛው እንዲሆን ያደረገበትን ምክንያትና ዕቅዱን ለመረዳት እንድንችል ነው።

### 1. የሳውል መለወጥ

ከዕብራውያን ዕብራዊ የሆነው ሳውል ክርስቲያኖችን ባሳደደ ጊዜ የአይሁድን እምነት ከስሕተት ትምህርት መከላከሉ ይመስለው ነበር። ጳውሎስ ይህን ያደረገው በቅንዓት በቅን መንፈስ ተመርቶ ቢሆንም በስሕተት መንገድ ላይ ነበር።

ሳውል የተለወጠው ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በመለኮታዊ መገለጥ በማየት ነበር። ይህንን መገለጥ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ የተደረገ የመጨረሻ መገለጥ ብሎታል (1ኛ ቆሮ. 15፡8)። ይህም ከሞት

የተነሣው የክርስቶስ መገለጥ ለሳውል የታየው በደማስቆ መንገድ ላይ፥ በታላቅ ድምፅና በታላቅ ብርሃን ውስጥ ነበር (የሐዋ. 9፡3-7)። ከሳውል ጋር የነበሩት አጃቢዎቹ አዩ፥ ድምፁንም ሰሙ፤ ሳውልም ዓይኑ ታወረ። ለሳውል ብቻ የመጣው ይህ ከሞት የተነሣው የክርስቶስ ድንገተኛ መገለጥ የወንጌል መልእክት ትክክለኛ መሆኑን አሳመነው።

በለውጡ ጊዜ ሳውል በጣም አስፈላጊ በሆኑ ሦስት ነገሮች ላይ ሊረታ ቻለ።

ሀ/ ቅንዓቱ፥ ከኢየሩሳሌም ያገኘው የሥልጣን ደብዳቤና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸምኩ ነው ብሎ ማሰቡ በእግዚአብሔር ፊት ስሕተት መሆኑን ተገነዘበ (ሮሜ 9፡4-5፤ 10፡2-4፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡13-14)።

ለ/ እርሱ የሚያሳድደው ኢየሱስ በሕይወት መኖሩንና እስራኤላውያን ከሚያመልኩት ከእግዚአብሔር አብ ጋር በአንድነት መሆኑን ተገነዘበ። የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ለሰው ልጆች ኃጢአት እግዚአብሔር የሰጠው ችሮታ መሆኑንና የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን በመረዳቱ ከክርስቲያኖች ጋር በአሳብ ለመስማማት ተገደደ (1ኛ ቆሮ. 15፡3-4)።

ሐ/ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን እንደመረጠውና አይሁዶችም ከአሕዛብ ጋር በአንድነት የክርስቶስ አካል እንደሚሆኑ በግልጽ ተረዳ (ሮሜ 11፡13-14፤ ሮሜ 15፡15-16፤ ገላ. 1፡11-16፤ 2፡7-8፤ ኤፌ. 3፡1-9፤ የሐዋ. 9፡15፤ 22፡2)።

በኋላም በደማስቆ ሐናንያ በጌታ ተመርቶ የሳውል ዓይን እንዲበራ አደረገ። ሳውልም በጌታ የተሰጠውን አዲሱን ትእዛዝ ተቀብሎ ለአሕዛብ የጌታ መልእክተኛ ሆነ። መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ፥ ተጠመቀም።

## 2. ጳውሎስ ኢየሱስን ያውቀው ነበርን?

ጳውሎስና ኢየሱስ ዕድሜያቸው ተመሳሳይ ነበር። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ሲመላለስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የገማልያል ተማሪ ነበር። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ኢየሱስን ያየውና ሲያስተምርም ያዳመጠው ይመስላል (2ኛ ቆሮ. 5፡16)። ይሁን እንጂ ጳውሎስን ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት እንዲለውጥ ያደረገው በደማስቆ መንገድ ላይ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ማየቱ ነበር።

## 3. የጳውሎስ የመጀመሪያ አገልግሎት

ጳውሎስ አገልግሎቱን ወዲያውኑ በደማስቆ ጀመረ። በዚያን ጊዜ ለሦስት ዓመታት ወደ ዓረብ አገር ሄዶ ነበር (ገላ. 1፡17–18)። ምናልባትም ይህንን ጕዞ ያደረገው ደማስቆን ሳይለቅ በፊት (የሐዋ. 9፡23–25) ማለት ወደ ምኩራቦቹ እየሄደ ከመሰከረ በኋላ ሳይሆን አይቀርም (የሐዋ. 9፡20–22)። ምናልባትም ይህንን ጕዞ ያደረገበት ምክንያት የነበረውን አስተሳሰብ በክርስቶስ ካገኘው አዲስ ብርሃን ጋር ለማስተካከል ጊዜ ስላስፈለገው ይሆናል። የደማስቆ ደቡባዊና ምሥራቃዊ ክፍል አርስጦሲዩስ በሚባል ንጉሥ ሥር የሚተዳደሩና ናባቲያን በመባል የሚታወቁ የዓረብ ነገዶች ይኖሩ የነበሩበት ስፍራ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡32–33)። ጳውሎስ የሄደው ከደማስቆ ብዙ ወደ ማይርቀው ወደ ሶርያ ምድረ በዳ አካባቢ ነበር። (በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ያለውን ካርታ ተመልከቱ።)

ኢየሱስን እንደ መሢሁ አድርጎ ጳውሎስ የተቀበለበት እምነቱ በደማስቆ ካሉት አይሁዳውያን ጓደኞቹና አብረውት ከሚሠሩት ሰዎች ጋር ብዙ ቅራኔዎች ፈጠረበት። ምክንያቱም እነርሱ ለአይሁድ ሕግ ይቀኑ ስለነበር ነው። በዚህ ምክንያት ለራሱ ደኅንነት ከተማዋን ለቅቆ ለመውጣት ተገደደ (የሐዋ. 9፡23–25)።

በኢየሩሳሌም ያሉ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም ደግሞ ጳውሎስን አላመኑትም። ክርስቲያኖችን ለማሳደድ እንዲያመቸው የሚያታልላቸው መሰላቸው። ቢሆንም በርናባስ ከጳውሎስ ጋር ጓደኛ በመሆን ጳውሎስ መለወጡን ለደቀ መዛሙርቱ በማስረዳት እንዲቀበሉት አሳመናቸው (የሐዋ. 9፡26–27)።

የጳውሎስ ስብከት በተለይም ከግሪክ በመጡት አይሁዳውያን ዘንድ የማሳመን ኃይል ስለነበረው ብዙዎቹ አመኑበት። የተቀሩትም አይሁዶች ጳውሎስን ለመግደል ዝተው ስለነበር በኢየሩሳሌም የነበሩት ደቀ መዛሙርት ወደ ተወለደበት ከተማ ወደ ጠርሴስ ላኩት (የሐዋ. 9፡28–30)።

## 4. ከግሪክ አገሮች የመጡ ሔለናውያን

በአይሁዶች መካከል ሁለት በጣም የተለያዩ ክፍሎች ነበሩ።

ሀ/ በምሥራቅ የተበተኑት አይሁዶች «ዕብራውያን» በመባል ይታወቁ ነበር። የአይሁድን እምነት አጥብቀው የሚይዙ ሲሆኑ በምኩራብም የሚጠቀሙት የዕብራይስጥን ቋንቋ ነበር። የብሉይ ኪዳንንም ባህልና ሥርዓት አጠንክረው ይጠብቃሉ። ብዙዎቹ ዕብራውያን

በኢየሩሳሌም ከተማ ሲኖሩ አንዳንዶቹ በአካባቢው የሚኖሩ ቢሆኑም ብሉይ ኪዳንን በትክክል የሚጠብቁ ነበሩ።

ለ/ በምዕራብ የተበተኑት አይሁዶች «ሔለናውያን» በመባል ይጠራሉ፤ ምክንያቱም የግሪኮችንና የሮማውያኖችን ባህል ስለተቀበሉ ነው። የአይሁድ እምነታቸውን ቢከተሉም አስተሳሰባቸው ሰፋ ያለ ነበር። ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ይልቅ በግሪክ ቋንቋ በተጻፈው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መጠቀምን ይመርጣሉ።

በእነዚህ በሁለት ቡድኖች መካከል የነበረው ልዩነት የጥንቲቱን ቤተ ክርስቲያን አንድነትን ብዙ ጊዜ አደጋ ላይ ጥሏል (የሐዋ. 6:1)።

## 5. ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጋቸው ጉዞዎች

ሀ/ ጳውሎስ ከተለወጠ ከሦስት ዓመት በኋላ ጴጥሮስን ለመገናኘት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (ገላ. 1:15–19)። ለሕይወቱ በሚያሰጋ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ ወንድሞች ወደ ቂሳርያ ከዚያም ወደ ትውልድ አገሩ ወደ ጠርሴስ ወሰዱት (የሐዋ. 9:26–30)።

ለ/ ጳውሎስና በርናባስ ለኢየሩሳሌም የሚሆን ስጦታ ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሉ (የሐዋ. 11:29–30)።

ሐ/ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ የሄደው ለኢየሩሳሌም ጉባኤ ሲሆን፥ ከእርሱም ጋር በርናባስንና ቲቶን ወስዶአቸው ነበር (ገላ. 2:1–10፤ የሐዋ.15:1–29)።

መ/ በሁለተኛ የጳውሎስ ጉዞ መጨረሻ ላይ ጳውሎስ ስላምታ ለማቅረብና ምናልባትም ከአሕዛብ ክርስቲያኖች ያገኘውን ስጦታ ለመስጠት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (የሐዋ. 18:22)።

ሠ/ ጳውሎስ ለአምስተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው በሦስተኛው ወንጌላዊ ጉዞው መጨረሻ ላይ ነበር (የሐዋ. 21:17–19)።




10 ዓ.ም. ጳውሎስ በጠርሴስ ተወለደ (የሐዋ. 22:3)

20 ዓ.ም. ጳውሎስ የአይሁድን ሕግ ትምህርት ተማረ (የሐዋ.22:3)

33 ዓ.ም የጳውሎስ መለወጥ (የሐዋ. 9:3-18)

35 ዓ.ም ጳውሎስ ወደ ዓረብ አገር መሄድ (ገላ. 1:17)

39 ዓ.ም የጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ (የሐዋ. 9:25-30)

## ማጠቃለያ

ጳውሎስ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በመገለጥ ካየ በኋላ በፊት በተቃዋሚነት የነበረው ቅንዓት ተለውጦ ለክርስቶስ የሚቀና ሆነ። ጳውሎስ ምንም እንኳ ፈሪሀ-እግዚአብሔር ያላቸው ግሪኮች ወደሚሰበሰቡበት ምኵራብ በቅድሚያ በመሄድ ቢያሳምናቸውም፥ የተጠራው ግን በተለይ ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ ነበር። ጳውሎስ

ከተለወጠ በኋላ በመጀመሪያ፥ ደቀ መዛሙርቱ ሊያምኑት አልቻሉም፤ ከዚያም፥ በአይሁዶችም መጠላትንና ተቃውሞን አስከተለበት።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ስለ ወንጌልና ስለ ክርስቶስ አስተሳሰብ ያስለወጠውና ያሳመነው ምን ነበር?
2. ጳውሎስ በተለወጠ ጊዜ የተገነዘባቸውን ሦስት ነገሮች በአጭሩ ግለጽ።
3. ሁለቱ የአይሁድ ቡድኖች ማንና ማን ነበሩ? ልዩነታቸውስ ምን ነበር?
4. ጳውሎስ በቅድሚያ ኢየሱስን ለማወቁ ምን ማስረጃ አለ?
5. ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ የሄደበት «ዓረብ» የሚገኘው በየት አካባቢ ነበር?
6. ጳውሎስ ከደማስቆ የሸሸው ለምን ነበር? ከኢየሩሳሌም የሸሸውስ?

# ትምህርት 3

## የጳውሎስ የመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞ

የትምህርቱ ዓላማ፡- የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማሰራጨት መልእክተኞችን ወደ አሕዛብ የላከችው አስፈላጊ ተግባርን እንድንረዳ ለማድረግ ነው።

ደግሞም ጳውሎስ ወንጌልን ለማሰራጨት የተጠቀመበትን ዘዴና ወንጌል የተቀበሉት ሰዎች እነማን እንደ ነበሩ መረዳት እንድንችል ነው።

### 1. በሶርያ የምትገኘው አንጾኪያ

የአንጾኪያ ከተማ የተቆረቆረችው ሲሉሲድ ተብሎ በሚጠራው ዘመነ መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ300 ዓመተ ዓለም ነበር። ከተማይቱ ጥንትም የግሪኮች ከተማ ነበረች፤ በጳውሎስ ዘመን ግን ግሪኮች፥ አይሁዶችና ሶሪያውያን የነበሩባት ስትሆን የሁሉም ነገዶች መብት በእኩልነት ደረጃ የተጠበቀ ነበር። አይሁዶች በከተማው ውስጥ የምኵራብ አምልኮ ነበራቸው።

በሮማውያን አገዛዝ ሥር አንጾኪያ በለጸገች። ከተማይቱ ለንግድና ለወታደራዊ እንቅስቃሴ መተላለፊያ በር ነበረች።

## 2. በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተቋቋመችው እስጢፋኖስ በተወገረበትና ክርስቲያኖች በተበተኑበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም። አማኞች በቆጵሮስና በቀሬ ወደ አንጾኪያ በመሄድ ወንጌልን ለግሪኮች ስለ ሰበኩ ብዙ ሰዎች አመኑ (የሐዋ. 11፡19-21)።

የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አንጾኪያን እንዲጐበኝ በርናባስን ላኩት፤ በርናባስም ለጥቂት ጊዜ በዚያ አገለገለ (የሐዋ. 11፡22-24)። በአንጾኪያ ያለው የወንጌል ሥራ በጣም ስለ ተስፋፋ በርናባስ ወደ ጠርሴስ ሄዶ ጳውሎስ እንዲያግዘው ጠየቀው (የሐዋ. 11፡25-26)። ከዚያም በፊት ጳውሎስ ለሕይወቱ ስለሚያሠጋው ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ልከውት ነበር (የሐዋ. 9፡29-30)።

ጳውሎስና በርናባስ ለአንድ ዓመት ሙሉ በአንጾኪያ በማስተማርና በመስበክ ለብዙ ሰዎች አገልግሎት ሰጡ። አማኞች በመጀመሪያ «ክርስቲያን» የተባሉት በአንጾኪያ ነበር (የሐዋ. 11፡26)።

በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ያመኑ አሕዛብ ከመኖራቸውም በላይ የአሕዛብ አማንያን እናት ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

ሀ/ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጉባኤ ያካሄዱባት ማዕከል ነበረች።

ለ/ ለአሕዛብ ወንጌልን በመስበክ ስመጥር የሆኑት ብዙዎች ሰባኪያን ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት ነበራቸው።

ጴጥሮስ - ገላ. 2፡11

በርናባስ- የሐዋ. 13፡1-3

ቲቶ - የሐዋ. 15፡2፤ ገላ. 2፡1-3

ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ - የሐዋ. 12፡25-13፡5

በርስያን የተባለው ይሁዳ - የሐዋ. 15፡22

ሲላስ - የሐዋ. 15፡22

ሉቃስ - የሐዋ. 16፡12። «እኛ» የሚል ቃል የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር እንደነበረ ያመለክታል።

ሐ/ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ወደ አሕዛብ ወንጌላውያን በመላክ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

በመጀመሪያ ሰዎች ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ የአይሁድ እምነትና ባህል ተከታዮች እንደሆኑ ይመስላቸው ነበር። በኋላ ግን የአሕዛብ አማንያን እየበዙና የተለያየ ትምህርትም ይዘው ወደ አማኞች ስለተደባለቁ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ወይም «ክርስቲያን» ተብለው ተቆጠሩ።

## 3. «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» አሕዛብ ወንጌልን ተቀበሉ

ጳውሎስ በሄደበት ሁሉ አንዳንድ አይሁዶች የሚሰብከውን ወንጌል ይቀበሉ ነበር፥ ሆኖም ጳውሎስን እየተከታተሉ ይቃወሙትና ከምኵራቦችም ያስወጡት የነበሩ የምኵራብ አለቆች ነበሩ። እነርሱም የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችና ለሃይማኖታቸው ቀናተኛ የሆኑ ነበሩ።

ከአሕዛብ ወገን የሆኑት አንዳንዶች የሮማውያንና የግሪኮችን አማልክት ብዛት አይቀበሉም ነበር። እነዚህ አሕዛብ አይሁዶች በሚያምኑት በአንዱ በእግዚአብሔር ብቻ የሚያምኑ ሲሆኑ የአይሁድን ሃይማኖት ሥርዓትና ወግ ግን ሙሉ በሙሉ አይጠብቁም ነበር። እነዚህ ሰዎች «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» አሕዛብ ሲሆኑ ብዙዎቹም ወንጌልን ለመቀበል የተዘጋጁ ነበሩ (የሐዋ. 10፡1–2፥ 35፤ 11፡20–21፤ 16፡14)።

## 4. የመጀመሪያው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ – 46 ዓ.ም.

በአንጾኪያ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እጃቸውን በጳውሎስና በበርናባስ ላይ በመጫን በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ ወደ አሕዛብ ላኳቸው (የሐዋ. 13፡1–3)።




# ቆጵሮስ

ጳውሎስና በርናባስ ዮሐንስ የተባለውን ማርቆስን አስከትለው በቅድሚያ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ (የሐዋ. 13፡4)። ቆጵሮስ የበርናባስ የትውልድ አገሩ ነበር (የሐዋ. 4፡36)።

በመጀመሪያ በሶሪያ ክፍለ አገር ወደምትገኘው አንጾኪያ የሄዱት ወንጌላውያን ጥቂቶቹ ከቆጵሮስ ነበሩ (የሐዋ. 11፡20)። እንደ ጳውሎስ ልማድ በዚህ ከተማም በቅድሚያ ወደ ምኵራብ ገብተው ለአይሁድ ወንጌልን ሰበኩ (የሐዋ. 13፡5)። ኤልማስ የተባለው ጠንቋይ የአገሩ ገዢ የወንጌልን መልእክት እንዳይሰማ ፈልጎ ሐዋርያቱን ተቃወማቸው። ይህ ተቃውሞ ከሰይጣን መሆኑን ጳውሎስ ስላወቀ ኤልማስን

ገሠጸው። አገረ ገዥውም በኤልማስ ላይ ወዲያውኑ የወረደውን ፍርድ ተመልክቶ አመነ (የሐዋ. 13፡8-12)።

ከሐዋርያት ሥራ 13፡13 ጀምሮ የወንጌል ተልእኮውን ቡድን መሪነት ጳውሎስ ያዘ። በሐዋርያት ሥራ 13፡2 ውስጥ «በርናባስና ሳውል» ይላል። በኋላ ግን ስለ «ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር» ወይም ስለ «ጳውሎስና በርናባስ» በማለት ይናገራል (የሐዋ. 13፡13)።

## የጲስድያዋ አንጾኪያ

ጳውሎስና በርናባስ ወደ ታናሹ እስያ ጉዞ ቀጠሉ፤ ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ ግን ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ለምን እንደተመለሰ ምክንያቱ አልተገለጸም።

ጳውሎስ በጲስድያዋ አንጾኪያ የሰበከው መልእክት እስጢፋኖስ በተወገረበት ሰዓት ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነበር። ተመሳሳይነቱም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት እንደሚገናኛቸው በተናገሩት ላይ ነው (የሐዋ. 13፡16-43)። ሆኖም ጳውሎስ የጨመረው አዲስ አሳብ ጽድቅ በእምነት ብቻ የሚገኝ መሆኑን ነው (የሐዋ. 13፡38-39)። ይህንን መልእክት አሕዛብ በደስታ ሲቀበሉት አይሁዶች ግን በመራርነት ተቃወሙት (የሐዋ. 13፡42-50)።

## ኢቆንዮን፥ ልስጥራንና ደርቤ

በሌሎች ከተሞች እንዳደረጉት ሁሉ በኢቆንዮንም አይሁዶች ጳውሎስንና በርናባስን ተቃወሟቸው። ሆኖም ለተወሰነ ጊዜ በከተማው ውስጥ ሊያስተምሩ በመቻላቸው ሰዎች ከአይሁድም ከአሕዛብም አመኑ። በመጨረሻም ሊወግሩዋቸው ሲዝቱባቸው ወደ ልስጥራ ጉዞአቸውን አመሩ። በልስጥራም ጳውሎስ አንድ ሽባ ሰው ስለፈወሰ ጣዖትን የሚያመልኩ አሕዛብ ጳውሎስና በርናባስ ወደ ምድር የወረዱ አማልክት ናቸው ብለው ስለገመቱ መሥዋዕት ሊሠውላቸው ተነሡ። ጳውሎስ ግን ገሠጻቸውና «ዝናብንና ፍሬያማ ምርትን» ወደሚሰጠው ወደ እግዚአብሔር አመለከታቸው (የሐዋ. 14፡17)። በሐዋርያት ላይ ዓመፅ የሚያስነሡት አይሁዶች ጳውሎስን ተከትለው ወደ ልስጥራ በመምጣት ሕዝቡን አነሣሡባቸው። ጳውሎስ የሞተ እስኪመስል ድረስ በድንጋይ ተወገረ፤ ሆኖም ተነሥቶ ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤ ሄደ።




በደርቤም ጳውሎስና በርናባስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ፤ አንዳንዶች ሰዎችም አመኑ። ከዚያም በልስጥራና በኢቆንዮን በኩል አድርገው ወደ ጲስድያዋ አንጾኪያ ተመለሱ። ሲመለሱም አማኞችን እያስተባበሩና እያጽናኑ አለፉ። ከዚያም በመጀመሪያ ጉዞአቸውን ወደ ጀመሩበት ወደ ሶሪያዋ አንጾኪያ ተመለሱ።

ጳውሎስ የገላትያን መልእክት የጻፈው በደቡባዊ ገላትያ ውስጥ ለሚገኙት ለእነዚህ አራት አብያተ ክርስቲያናት ሳይሆን አይቀርም።

## 5. የጳውሎስ የአሠራር ዘዴ

ጳውሎስ በቅድሚያ ወደ አይሁዶች ምኵራብ በመሄድ አይሁዶች ለመስማት ፈቃደኞች እስከሆኑ ድረስ ይሰብከላቸው ነበር። ሆኖም

ምን ጊዜም ጳውሎስን እየተከታተሉ የሚቃወሙት የአይሁድ ተቃዋሚ ቡድኖች በእርሱ ላይ ያነሣሡበት ነበር። አይሁዶች ወንጌልን ከጳውሎስ ለማድመጥ ፈቃደኞች በማይሆኑበት ጊዜ እርሱ ወደ አሕዛብ ይሄድ ነበር።

ሰዎች በሚያምኑበት በማንኛውም ቦታ፥ ጳውሎስ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ቤተ ክርስቲያንን ይመሠርት ነበር። ከዚያም አመቺ ጊዜ ባጋጠመው ቁጥር እነዚህን አብያተ ክርስቲያናትን ለማጽናናትና ለማነጽ ተመልሶ ይጐበኛቸው ነበር። ብዙዎች የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉት ራሱ ላቋቋማቸው አብያተ ክርስቲያናት ነበር።

## ማጠቃለያ

30 ዓ.ም.

33 — ጳውሎስ አመነ፥ የሐዋ.9፡3–18

36 ዓ.ም. 46 ዓ.ም. — ጳውሎስ በጠርሴስ የቆየበት ዘመን የሐዋ.9፡30።

46–47 — የጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ የሐዋ.13፡4–12።

48 ዓ.ም ጳውሎስ የገላትያን መልእክት ጻፈ።

50 ዓ.ም.

የጳውሎስ የመሪነት ተሰጥኦ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ በመጀመሪያው የወንጌል ስርጭት ቡድን ውስጥ መሪ ለመሆን አበቃው። የመጀመሪያ ጉዞአቸው ወደ ቆጵሮስ፥ ጵንፍልያ፥ ጲስድያና ገላትያ ነበር። የጳውሎስ የአሠራር ዘዴ መጀመሪያ ለአይሁዶች በምኩራባቸው ውስጥ መስበክ ነበር። እነርሱ ሲቃወሙት እርሱ ወደ

አሕዛብ ሄዶ ይሰብክ ነበር። የተወሰኑ አማኞች በአንድ አካባቢ በተገኙበት ጊዜም ሽማግሌዎችን በመምረጥ በቤተ ክርስቲያን መልክ ያስተባብራቸው ነበር። ከዚህ በኋላም ያጽናናቸዋል፤ አብሮአቸው ይጸልያል፤ ከዚያም ወደ ሌላ ስፍራ ይሄዳል። በተጨማሪም ጳውሎስ ተመልሶ በመሄድ ያጽናናቸዋል፤ ያበረታታቸዋል፤ ደብዳቤም ይጽፍላቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. ወንጌላውያንን የምትልከዋ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት ቡድን ለምን ጠቃሚ ሆነች?
2. የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለምን የአሕዛብ አማኞች እናት ቤተ ክርስቲያን ሆነች?
3. «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» እነማን ነበሩ?
4. በቆጵሮስ፥ በጲስድያዋ አንጾኪያ፥ በኢቆንዮን፥ በልስጥራና በደርቤ ምን እንደተፈጸመ በአጭሩ ግለጽ።
5. የጳውሎስን የወንጌል አሰረጫጨት ዘዴ ግለጽ።

# ትምህርት 4

## የኢየሩሳሌም ጉባኤ 49 ዓ.ም.

የትምህርቱ ዓላማ፡- በኢየሩሳሌም የተካሄደው ጉባኤ አስፈላጊ መሆኑንና ዓላማውም ወንጌልን ለአሕዛብ ለማዳረስ መሆኑን ለመግለጽና የጉባኤውንም ውጤት ለመረዳት እንድንችል ነው።

ጳውሎስና በርናባስ የመጀመሪያውን የወንጌል ጉዞ አድርገው ከተመለሱ በኋላ ለአሕዛብ በሰጡት አገልግሎት ላይ ብዙ ጥያቄዎችና ተቃውሞዎችን በአንጾኪያና በኢየሩሳሌም ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንኳ ሳይቀሩ እንዳስነሡባቸው አስተውሉ። ከአይሁድ ወገን ያመኑት አማኞች እግዚአብሔር ጥንት በሚሠራበት መንገድ እንዲሠራ ይጠባበቁ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙ ከተወያዩ በኋላ ጳውሎስና በርናባስ ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ሆነው ኢየሩሳሌም ካሉት ሐዋርያት ጋር በጉዳዩ ላይ እንዲወያዩበት ወደ ኢየሩሳሌም ተላኩ (የሐዋ. 15፡1–3)። ጳውሎስም ይህንን ሁኔታ በገላትያ 2፡1–10 ጠቅሶታል።

### 1. የጉባኤው የውይይት ነጥብ

በፈጣን ዕድገት ላይ ያለው የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን በአይሁድ ክርስቲያኖች ዘንድ ጥያቄን ፈጠረ። እንዲሁም በተጨማሪ እነዚህ ያመኑ አሕዛብ እስከምን ድረስ ነው የአይሁድን ሕግ መጠበቅ ያለባቸው የሚለው ሌላ ጥያቄ አከራካሪ ነጥብ ሆነ።

ጌታ ኢየሱስ ራሱንና ትምህርቱን ከኦሪት ሕግ ለይቷል። ልጅ ከአሽከር እንደሚበልጥ ሁሉ እርሱም ከሙሴና ከነቢያት የበለጠ መሆኑን ገልጾአል (ዮሐንስ 8፡33-36)። ይሁን እንጂ አይሁዶች ይህንን ትምህርት የተረዱት ቀስ በቀስ ነበር።

ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቀስ በቀስ ኦሪትን ከማክበር እየተላቀቀች መጣች። የድሮ ኪዳን የማይመለከታቸው አሕዛብ ወደ ክርስቲያኖች ኅብረት በእምነት ብቻ ገቡ። ለብዙ ዘመን አይሁዶች ይጠብቁት የነበረው የድሮው ሥርዓት በአዲስ የተተካ መሆኑን መገንዘብ ለአይሁዶች በጣም አስቸጋሪ ነበር።

ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ላሉት ለአይሁድ ክርስቲያኖች ቀደም ሲል በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአይሁዶች ላይ እንደወረደ በተመሳሳይ ሁኔታ በአሕዛብም ላይ መውረዱን ነግሯቸው ነበር (የሐዋ. 11፡1-8)። ይሁን እንጂ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት አይሁድ ክርስቲያኖች ማንኛውም የአሕዛብ ወገን ሳይገረዝ መዳን ይችላል የሚለውን ትምህርት መቀበል አልቻሉም።

ጳውሎስና በርናባስ ከመጀመሪያው ተልእኮአቸው እንደተመለሱ ወንጌልን ለአሕዛብ በመስበካቸው የተገኘውን ውጤት በአንጾኪያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን መሰከሩ። አንዳንድ ከአይሁድ የመጡ ከአይሁድ ወገን ያመኑ ክርስቲያኖች እንዲህ ብለው አስተማሩ፡- «እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» (የሐዋ. 15፡1)። የእነዚህ አስተማሪዎች ዓላማ የጳውሎስን አገልግሎት በማጥላላት አማኞችን ከእርሱ ለመገንጠል ነበር (ገላ. 2፡1-10፤ 5፡1-13)።

ከአይሁድ ወገን ባመኑት ክርስቲያኖችና ከአሕዛብ ወገን ባመኑት ክርስቲያኖች መካከል በተፈጠረው በዚህ አለመግባባት ምክንያት ጳውሎስ፥ በርናባስና ሌሎች የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተመርጠው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ተደረገ።

## 2. የኢየሩሳሌም ጉባኤ አባላት

ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ከመጡት ክርስቲያኖች ጋር ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ። በኢየሩሳሌም ያሉት ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም ከአንጾኪያ ለመጡት ልዑካን አቀባበል

አደረጉላቸው። የፈሪሳውያንን ትምህርት ያልለቀቁት አማኞች ሕግን መጠቀም አስፈላጊ ስለመሆኑ አጥብቀው ለመከራከር ወደ ጉባኤው ደግሞ መጡ።

### 3. በጉባኤው የነበረው ውይይት

ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑት አማኞች የኦሪት ሕግ መጠበቅ አለበት በሚለው አሳብ ጸንተው ተሟገቱ።

ስለ ወንጌል አርነት የሚከላከል አሳብ በሦስት ምስክሮች ተሰጠ።

ሀ/ ጴጥሮስ፡- የመጀመሪያዋ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው ጴጥሮስ የወንጌል አርነት የእግዚአብሔር ምርጫ ስለመሆኑ እነዚህን ነጥቦች ተናገረ፡-

(1) አሕዛብ የክርስቶስን መልእክት መስማት አለባቸው (የሐዋ. 15፡7)።

(2) አይሁዶች መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ አሕዛብም ተቀብለዋል (የሐዋ. 15፡8-9)።

(3) የሥርዓቱ ሕግ ለአይሁድም እንኳ ለመሸከም የሚያዳግት ቀንበር ሆኖባቸዋል (የሐዋ. 15፥10)።

ለ/ ጳውሎስና በርናባስ፡- መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ተጠቅሞ በአሕዛብ መካከል ያደረገውን ተአምራትና ድንቅ እንዲሁም በአሕዛብ መካከል ስለነበራቸው አገልግሎት ገልጸው ተናገሩ (የሐዋ. 15፡12)።

ሐ/ ያዕቆብ፡- አጥብቆ ሕግን የሚጠብቅ ሰው ነበር (ገላ. 2፡12)። በጉባኤው ጊዜ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበረና የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጠ። በውሳኔውም በተለይ ለአይሁዶች አስቀያሚ ከሆኑት አራት ልምምዶች አሕዛብ እንዲታገዱ አሳብ አቀረበ (የሐዋ. 15፡19-20)። እነርሱም፡-

(1) ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ መብላትን።

(2) የታነቀ ከብት ሥጋ መብላትን

(3) ደም መብላትን

(4) ዝሙት ወይም በብሉይ ኪዳን የተከለከለውን ጋብቻ መፈጸምን ናቸው።

ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመላው ቤተ ክርስቲያን ጋር ያዕቆብ ባቀረበው አሳብ ተስማሙ። ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ሆነው የውሳኔውን ደብዳቤ ለአሕዛብ ክርስቲያኖች እንዲያደርሱና ውሳኔውን ለእነርሱ እንዲያስረዱቸው ተጨማሪ ሰዎችን መረጡ።

## ማጠቃለያ

የኢየሩሳሌም ጉባኤ ውጤት አማኞች ከኦሪት ሕግ ፍጹም ነፃ የሆነ ንጹሕ ወንጌልን ብቻ እንዲቀበሉ መፍትሔ አበጀላቸው። ከሙሴ ሕግ ዘመን ወደ አዲሱ የክርስቶስ የጸጋ ዘመን መሸጋገሪያው ወቅት በብዙዎች አይሁዶች አእምሮ አለመስማማትንና መዘበራረቅን አመጣ። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ እንደሠራው በአሕዛብም ውስጥ መሥራቱን በሰሙ ጊዜ ቀስ በቀስ ወደ መቀበል ደረጃ ደረሱ። ይሁን እንጂ ያለ ምንም የሕግ ሥራ ጽድቅ በእምነት ይገኛል የሚለው ትምህርት ለብዙ ዘመናት ሲያከራክር ኖረ።

## ጥያቄዎች

1. የኢየሩሳሌም ጉባኤ ለምን ተሰበሰበ?
2. ያዕቆብ በጠቀሰው መሠረት ጉባኤው ምን ውሳኔ ላይ ደረሰ?
3. አሁን ባለንበት ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የወግ አጥባቂነት ግጭት አለብንን? ካለብን፥ አንዳንድ ግጭትን የሚያስነሡ ነገሮችን ጥቀስ?


ገላትያ
ጠርሴስ
የሶርያዋ
አንጾኪያ
ደማስቆ
ታላቁ ባሕር
ኢየሩሳሌም

# ትምህርት 5

## ሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ

**የትምህርቱ ዓላማ፦ የቤተ ክርስቲያንን አመራር፥ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተደረጉትን የደብዳቤ ልውውጦችና የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች በሚመለከት በሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ ወቅት የተደረጉትን እርምጃዎችና ዕድገቶች ለማጥናት ነው።**

### 1. የጳውሎስ ወደ አንጾኪያ መመለስ–(የሐዋ. 15፡22–40)

ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጳውሎስንና በርናባስን ተከትለው ወደ አንጾኪያ የሚሄዱትን ሰዎች መረጡ። የተመረጡት ሰዎች የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሆኑ፥ የጉባኤውን ውሳኔ በደብዳቤና በቃላቸው ለአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን እንዲያደርሱ የተመረጡ ነበሩ።

#### ሀ/ ሐዋርያት እነማን ነበሩ?

በግሪክ ቋንቋ ሐዋርያ ማለት የተላከ ወይም ተልኮ የወጣ ማለት ነው። ሐዋርያት የሚለው ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ከኢየሱስ ጋር የነበሩትንና ትንሣኤውን የሚመሰክሩትን ወይም ኢየሱስ በዮሐንስ ከተጠመቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዐረገበት ጊዜ ድረስ ከእርሱ ጋር የነበሩትን ነው።

ጳውሎስ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት ኢየሱስ በሚያገለግልበት ወቅት አብሮት አልነበረም። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን በልዩ መገለጥ አይቶታል፥ እንዲሁም ወደ አሕዛብ እንዲላክ የተለየ ተልእኮ ተሰጥቶታል (የሐዋ. 26፡16–18፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1፤ 15፡8)።

የኢየሩሳሌሞቹን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ስጦታዎች እንደሆኑ አድርገን እንመለከታቸዋለን (1ኛ ቆሮ. 12፡28፤ ኤፌ. 4፡11)። የእውነተኛ ሐዋርያት አገልግሎት በተአምራት፥ በምልክቶችና በታላቅ ሥራዎች የታጀበ ነበር (2ኛ ቆሮ. 12፡12፤ የሐዋ. 8፡6–8፥ 14–19)።

ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረት ክፍል ሆነው ይታዩ ነበር (ኤፌ. 2፡20)። ሐዋርያ የሚለው ቃል የኢየሱስ ወንድም ለሆነው ለያዕቆብ (ገላ. 1፡19፤ 2፡9)፥ ለበርናባስ (የሐዋ. 14፡4፥ 14)፥ ለስልዋኖስና ለጢሞቴዎስ (1ኛ ተሰሎ. 2፡6)፥ ለአንዲራቆንና ለዩልያን (ሮሜ 16፡7) ተሰጥቶአቸው ነበር።

እነዚህ መስካሪዎች፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የወንጌል ምሥራች አብሣሪ የሆኑ ሰዎች በሮም ግዛት ሁሉ ክርስቶስ የሰጠውን ተልእኮ ፈጽመዋል።

## ለ/ ሽማግሌዎች እነማን ነበሩ?

በአዲስ ኪዳን፥ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ሥራ በበላይነት እንዲቆጣጠሩ የተመረጡ፥ የጸኑ መንፈሳዊያን ክርስቲያኖች ናቸው (የሐዋ. 14:23)። ደግሞ እነርሱ ጳጳሳት ነበሩ (የሐዋ. 20:17፤ 20:28፤ ቲቶ 1:5–9፤ 1ኛ ጴጥ. 5:1–4)። በሽማግሌዎችና በጳጳሳት መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ አይደለም፤ ምናልባትም አስተማሪ የሆነ ሽማግሌ ልዩ ሥልጣን ተሰጥቶት ጳጳስ እንዲሆን የተሾመ ሳይሆን አይቀርም።

## ሐ/ ነቢያት እነማን ነበሩ?

ጳውሎስና በርናባስ ወደ አንጾኪያ ሲመለሱ ከእነርሱ ጋር እንዲሄዱ የተመረጡት ሁለት ሰዎች በርስያን የተባለው ይሁዳና ሲላስ ነበሩ (የሐዋ. 15:32)።

ነቢይ የእግዚአብሔር ልሳን ነው። በአዲስ ኪዳን ማንኛውም ክርስቲያን ነቢይ ለመሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ነቢይ ኃጢአትን፥ ደኅንነትን፥ የእግዚአብሔርን ፍርድና ጸጋውን፥ በአጠቃላይ ሙሉውን ወንጌል የሚያውጅ ስለሆነ ነው። ነቢይ ማለት በልሳን የሚናገር ወይም የሚተረጉም ማለት አይደለም (1ኛ ቆሮ. 14:22–25፥ 27፥ 29፥ 32፥ 33)።

ማንኛውም ትንቢት በሁለት ፈተናዎች ይመዘናል፥

(1) ሌሎች ነቢያት የተናገረውን ይመዝኑታል (1ኛ ቆሮ. 14:29)።

(2) የሚናገረው መልእክት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት አለበት (1ኛ ቆሮ. 14:37–38)።

በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ነቢያት ተብለው የተጠሩና ለትንቢት ስጦታ የተለዩ ሰዎች ነበሩ (1ኛ ቆሮ. 12:28–29፤ ኤፌ 4:11)። ነቢያት በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ (የሐዋ. 13:1፤ 15:32)። ጳውሎስ እንደሚታሰር (የሐዋ. 21:10–11) እና በይሁዳ ራብ እንደሚመጣ አጋቦስ ተንብዮ ነበር (የሐዋ. 11:28)። የፊልጶስ ሴቶች ልጆች ትንቢት ተናጋሪዎች ነበሩ (የሐዋ. 21:9)።

### መ/ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሥልጣን ነበራትን?

ሐዋርያት በመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ ያላቸውን ልዩ ሥልጣን መጠቀማቸው ያለ ነገር ነበር። ሆኖም የሚጠቀሙበት ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመረኮዘ ነበር። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በሚመረጡበት ጊዜ እነርሱ የሚሾሙት ላሉባት አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ብቻ ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመን ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ኢየሩሳሌምም ሆነች አንጾኪያ በሌላው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነት ሥልጣን መጠቀም አይችሉም ነበር።

## 2. ጳውሎስ የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን በድጋሚ ጐበኘ (የሐዋ. 15፡41–16፡5)

ጳውሎስና በርናባስ ለተወሰነ ጊዜ በአንጾኪያ አስተማሩ። ከዚያም ጳውሎስ በርናባስን፡- «ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንባቸው በየከተማ ሁሉ እየሄድን ወንድሞችን እንጐብኛቸው፤ እንዴት እንዳሉም እንወቅ» አለው። የሁለተኛውን ጉዞ እንዲያደርጉ በመጀመሪያ አሳቡን ያቀረበው ጳውሎስ እንደሆነ አስተውል። (የሐዋ 13፡2ን ከ15፡36 ጋር አነጻጽር።)

ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ አብሮአቸው እንዲሄድ በርናባስ አሳብ አቀረበ፤ ጳውሎስ ግን በዚህ አሳብ አልተስማማም። ምናልባትም ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ በመጀመሪያው ጉዞአቸው ጊዜ አብሮአቸው እስከመጨረሻው ስላልተጓዘ ሊሆን ይችላል። በአሳቡ ያለመስማማታቸው ጳውሎስንና በርናባስን እንዲለያዩ አደረጋቸው። በርናባስ ዮሐንስ የተባለውን ማርቆስ ይዞ ወደ ቆጵሮስ ሲጓዝ፥ ጳውሎስ ደግሞ ሲላስን መርጦ ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ተጓዘ። በአሳብ ያለመስማማቱ ከአንድ የወንጌል ቡድን ይልቅ ሁለት የወንጌል ቡድን እንዲሆኑ አደረገ።

### ሀ/ ለገላትያ የተላከ መልእክት

የገላትያ መልእክት የጳውሎስ የመጀመሪያው ደብዳቤ ነው። በገላትያ ሰዎች እንዳመኑ ወዲያውኑ የተጻፈላቸው ነበር (ገላ. 1፡6–7)። የተጻፈውም ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ በነበሩ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በፊት ወይም በኋላ ሊሆን ይችላል።

የገላትያ ሰዎች እንዳመኑ ከጳውሎስ ትምህርት ፈቀቅ ብለው ወደ አሪት ሕግ ፊታቸውን አዞሩ። ጳውሎስ ያስተማረው ሌላ ወንጌል

እንደሆነ አድርገው የነገሯቸውን የሌሎችን ሰዎች ምክር አደመጡ። ጳውሎስም እርሱ ከሰበከው ወንጌል በቀር ሌላ ወንጌል የሚባል ነገር እንደሌለ ጻፈላቸው። እርሱ የሰበከው ወንጌል ከእግዚአብሔር የተሰጠው መገለጥ እንጂ ከሰው እንዳልሆነ ነገራቸው። ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነቱ ከማረጋገጡም በላይ በክርስቶስ ስለተፈጸመላቸው ነፃነት አስታውሷቸው ነበር። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑት ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ በእርሱ ወደ አሕዛብ መሄድና ማገልገል እንደሚስማሙ፥ እንደሚደግፉትና እንደሚተባበሩትም ገለጸላቸው። የጳውሎስ ወደ አሕዛብ ሄዶ ማገልገል ጴጥሮስ ለአይሁድ ከሚሰጠው አገልግሎት እኩል መሆኑን እንደሚቀበሉት ገለጸላቸው (ገላ. 2፡7–9)። ጴጥሮስ ከትክክለኛው እምነት ጋር ስላልተስማማ ጳውሎስ ጴጥሮስን እስከመገሰጽ እንደደረሰም ነገራቸው (ገላ. 2፡11–14)። ይህ ሁሉ ጳውሎስ ከሌሎቹ እኩል ሐዋርያ መሆኑን ያረጋግጣል።

ጳውሎስ የሐዋርያነቱን ሥልጣን ትክክለኛነት ካሳመነ በኋላ በክርስቶስ በማመን የሚገኘው ይህ ጽድቅ ያለ ምንም የኦሪት ሕግ ሥራ የሚገኝ መሆኑን በሰፊው ማብራራቱን ተያያዘው። የክርስትናን ሕይወት የሚገዛው ጸጋ እንጂ ሕግ ያለመሆኑን አስታወሳቸው። ጳውሎስ ለዚህ ማረጋገጫ እንዲሆን የራሱን ልምምድ እንደ ምሳሌ አድርጎ አቀረበ፤ እንዲሁም የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት በመጠቀም ትምህርቱን ግልጽ አደረገ። ጽድቅ በእምነት ብቻ እንደሚገኝና ደኅንነት የጸጋ ስጦታ እንደሆነ አብራርቶ የሚገልጽ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጳውሎስን መልእክት የሚያክል አይገኝም።

ከዚህ ወቅት በኋላ ስለ ገላትያ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ነገር የለም። ከዚህ በኋላ ምን ያህል በያዙት እምነት እንደጸኑ ወይም በጳውሎስ መልእክት እንደተማረኩ አናውቅም።

## ለ/ ቲቶ፡- ከአሕዛብ ወገን የሆነው የጳውሎስ ተባባሪ

ቲቶ ግሪካዊ የሆነ የጳውሎስ ታማኝ ተባባሪና ለእርሱም ሥራ የረዳትነት ብቃት ያለው ክርስቲያን ነበር። ጳውሎስ «አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው» ብሎታል (2ኛ ቆሮ. 8፡23)። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የቲቶ ስም አልተጠቀሰም፤ ግን በጳውሎስ አንደኛ ወንጌላዊ ጉዞ መጨረሻ አካባቢ ስለ መገረዝና ያለ መገረዝ ጉዳይ ችግር በተፈጠረ ወቅት ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ከሄዱት መካከል አንዱ ቲቶ ነበር (የሐዋ. 15፡2ን ከገላ. 2፡4–5 ጋር አገናዝብ)። የመገረዝና ያለመገረዝ ችግር በኢየሩሳሌም ጉባኤ መፍትሔ አገኘ። የአሕዛብ የመገረዝና ያለመገረዙን ችግር መፍትሔ ያስገኘው ቲቶ ነበር።

የቲቶ ስም ዳግመኛ የተጠቀሰው በጳውሎስ ሦስተኛ ጉዞ ወቅት ነበር። በዚያን ወቅት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በተደረገው አስቸጋሪ ዕርቅ ላይና ራብ ላጠቃቸው ሰዎች በተደረገው የመዋጮ ስብሰባ ላይ ቲቶ በሥራው ጳውሎስን በጣም አስደስቶት ነበር (2ኛ ቆሮ. 7፡6፥ 13፤ 8፡1–23፤ 12፡18)። ከዚህም ሌላ ቲቶ ከጳውሎስ ጋር ወደ ቀርጤስ ተጉዞአል። ይህን ጉዞ ያደረጉት ጳውሎስ በሮም በታሰረበት በመጀመሪያውና በሁለተኛው እስራቱ መካከል ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ ቲቶን በዚያ ስፍራ ትቶት ከሄደ በኋላ «የቲቶ መልእክት» የተባለውን ጻፈለት። ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ በሮም በታሰረበት ወቅት ጳውሎስም ወደ ድልማጥያ እስከላከው ድረስ ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በሮም ነበር (2ኛ ጢሞ. 4፡10)።

## ሐ/ ጢሞቴዎስ፡–

ግሪካዊ አይሁድ የሆነው የጳውሎስ አገልጋይ ነበር።

ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በኋላ ከዚህ ቀደም ጳውሎስ ያቋቋማቸውን አብያተ ክርስቲያናትን ለማበረታታት ጳውሎስና ሲላስ ተመልሰው ጉዞ ጀመሩ (የሐዋ. 15፡40–41)።

ከዚያም ጳውሎስ በልስጥራ አባቱ ግሪክ እናቱ አይሁዳዊት የሆኑትን ጢሞቴዎስን ተገናኘው። ጳውሎስ በመጀመሪያ በልስጥራ በነበረበት ጊዜ የጢሞቴዎስ እናት በክርስቶስ ሳታምን አትቀርም። ጢሞቴዎስ የብሉይ ኪዳንን ትምህርት ከእናቱና ከአያቱ ተምሯል (2ኛ ጢሞ. 1፡5፤ 3፡14–15)።

ጢሞቴዎስ ወጣት ቢሆንም እንኳ ጠንካራ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊሆን እንደሚችል ጳውሎስ ስለተረዳ ይዞት ለመዞር ፈለገ። ሆኖም ጢሞቴዎስ በእናቱ ምክንያት አይሁድ ቢሆንም፥ ካልተገረዘ በቀር በአይሁዶች ዘንድ ተቀባይነት ስለማይኖረው ጳውሎስ አስገረዘው። ከዚያ በኋላ ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር ተጓዘ።

ጳውሎስና ሲላስ ከኢየሩሳሌም ጉባኤ የተላከውን ውሳኔ ያዘለ ደብዳቤ ለአብያተ ክርስቲያናት በማድረስ በቃላቸውም ውሳኔውን አብራሩ። ከዚህ የተነሣ ብዙ ሰዎች አምነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ተቀላቀሉ (የሐዋ. 16፡1–5)።

ጢሞቴዎስ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያጽናና በመጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ተላከ (1ኛ ተሰ. 3፡2)። ከዚያም ወደ መቄዶንያና ወደ ቆሮንቶስ ተላከ (1ኛ ተሰ. 3፡4–7)። ከዚያ የተሰበሰበውን የእርዳታ ገንዘብ ይዞ ከጳውሎስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (የሐዋ. 20፡4)። ጳውሎስ የፊልጵስዩስንና የቈላስያስን መልእክቶች ሲጽፍ ጢሞቴዎስ

አብሮት ነበር (ፊልጵ. 1:1፤ ቈላ 1:1)። ጳውሎስ ሁለቱን መልእክቶች ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግል ነበር (1ኛ ጢሞ. 1:3)። ጢሞቴዎስ በትክክል ባልታወቀ ወቅት ታስሮ ነበር (ዕብ. 13:23)።

ጢሞቴዎስ የጳውሎስ ታማኝ ረዳት በመሆን እስከ መጨረሻ ጸንቶ አገለገለው። ጢሞቴዎስ ወጣት በመሆኑ ስለ ተሸከመው ኃላፊነት ሥጋት ነበረበት፤ ጳውሎስ ግን አጽናናው (1ኛ ጢሞ. 4:12-16)። ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ጋር በነበረው ግንኙነት አንድ በእምነት ውስጥ ብዙ የቆየና ብቃት ያለው መሪ ወጣት የሆነን ሰው እንዴት ማስተማር፥ ማጽናናትና መንፈሳዊ መሪ ማድረግ እንደሚችል የሚያሳይ ግሩም የሆነ ምሳሌነት እናገኛለን።

## 3. የጳውሎስ አገልግሎት በግሪክ አገር - (የሐዋ. 16:6-18:17)

ጳውሎስና ሲላስ ጕዞአቸውን ቀጠሉ፤ የጕዞ መሪያቸውም መንፈስ ቅዱስ ነበር። ጳውሎስና የሥራ ባልደረቦቹን መንፈስ ቅዱስ ወደ ሚስያ እና ወደ ቢታንያ እንዳይሄዱ በከለከላቸው ጊዜ ወደ ጢሮአዳ ሄዱ። በዚያም ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ ተሻገረና እርዳን የሚለውን ጥሪ ተቀበሉ ወደ ፊልጵስዩስ ተጓዘ።

### ሀ/ ፊልጵስዩስ (የሐዋ. 15:12-40)

ከተማይቱ የተሰየመችው በመቄዶንያዊ ፊልጶስ ስም ሲሆን ዘመኑም 359 ዓ.ዓ. ነበር። ከተማይቱ በጠንከረ ሁኔታ ድንበሯን ከጠላቶችዋ ያስከበረችውና የተስፋፋችው በዚህ ሰው ዘመን ነበር፤ ስሟም ፊልጵስዩስ የተባለው ያን ጊዜ ነበር። ከተማዋ በብዛት ወርቅ ታመርት ነበር፥ ገንዘቧም ከወርቅ የተሠራ ነበር። በ168 ዓ.ዓ. ላይ ከተማይቱ በሮማውያን እጅ ገባች፤ ከዚያም በ146 ዓ.ዓ. ላይ መቄዶንያ ከሮም ክፍለ ሀገር አንዱ እንድትሆን ተደረገ።

በ42 ዓ.ዓ. የፊልጵስዩስ ጦርነት ተደረገ፤ ጦርነቱ የተካሄደው አንቶኒ እና አክታቪያን ከብሩተስ እና ከቃሲዩስ ጋር ነበር። ከጦርነቱ በኋላ ከተማዋ የሮም ቅኝ ግዛት ሆነች። ሕዝቧም በቅንዓት ተነሣሥተው የሮም ዜግነትን በመቀበል የፖለቲካ መብታቸውን አስጠበቁ። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «አገራችን በሰማይ ነው» በማለት ሰማያዊ ዜግነታቸውን አስታወሳቸው (ፊልጵ. 3:20)።

ፊልጵስዩስ ሉቃስ የተወለደባት ከተማ ሳትሆን አትቀርም። ጳውሎስ ፊልጵስዩስ ከደረሰ በኋላ ሉቃስ «እኛ» ብሎ መጻፉን አቋረጠ። ከሐዋ.

16፡10–17 እስከ የሐዋ. 20፡5 ድረስ «እኛ» የሚለውን ቃል አልተጠቀመበትም። ይህም የሚያመለክተው ሉቃስ በፊልጵስዩስ መቆየቱን ይሆናል።

## በፊልጵስዩስ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን

በከተማይቱ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አይሁዶች በብዛት አልነበሩም። ስለዚህ ጳውሎስ አገልግሎቱን የሚጀምርበት ምኩራብ አልነበረም። ጳውሎስ ጥቂት ሰዎች ከከተማው ከልል ውጭ ለጸሎት መሰብሰባቸውን ስለተገነዘበ ወደዚያ ስፍራ ሄደ። በጸሎት ስፍራ ምናልባት ጥቂቶች አይሁዶች ሲሆኑ ሌሎቹ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እንደ ልድያ ያሉት አሕዛብ ነበሩ።

ከጳውሎስ ሞት በኋላ ስለ ፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ወሬ እምብዛም ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን የአንጾኪያ ጳጳስ የነበረው አግናሲዩስ በሁለተኛው ምእተ ዓመት ላይ ክርስቲያን በመሆኑ ተከሶ ወደ ሮም ታስሮ ተወስዶ በአውሬ እንዲበላ ተፈረደበት። በጉዞው ላይ እንዳለ ወደ ሮም ሲያልፍ በፊልጵስዩስ ቆም ብሎ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖችን ሲጐበኝ ደግቅ አቀባበል አደረጉለት። በዚያን ጊዜ እነዚህ ክርስቲያኖች በአንጾኪያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን የመጽናናት ደብዳቤ መጻፋቸው ይታወሳል።

በፊልጵስዩስ ስላሉ ኤጲስ ቆጶሳት ጥቂት የተዘገበ ነገር አለ። ይኸውም በሳርዲቃ ጉባኤ በ344 ዓ.ም.፥ በኤፌሶን ጉባኤ በ431 ዓ.ም. እንዲሁም በቻልሲደን ጉባኤ በ451 ዓ.ም. በወሰኑት ውሳኔ ላይ ስማቸው ተጠቅሶ ይገኛል።

ዛሬ ከተማይቱ ቀድሞ በነበረችበት ስፍራ የለችም፥ ስለ አፈራረስዋም ምንም ተመዝግቦ የተቀመጠ ታሪክ አናገኝም፤ የከተማይቱ ፍርስራሽ ቢገኝም እንኳ የአርኪዩሎጂ ጥናት በሰፊው አልተካሄደበትም።

### ለ/ ተሰሎንቄ

## የተሰሎንቄ ከተማ

ከተማይቱ በ316 ዓ.ዓ. በቃሳንደር ተመሠረተች። እርሱም ከተማይቱን በሚስቱ ስም ሰየማት። ሚስቱም የታላቁ እስክንድር እኅት ነበረች። ወዲያውም ከተማይቱ የመቄዶንያ ዋና ከተማና የሮም አስተዳደር ማዕከል ሆነች። ይህች ከተማ ብዙ ሸቀጦች የሚለዋወጡባት የንግድ መናኸሪያ ስትሆን እስከ አሁንም ታላቅ ከተማ ነች።

በከተማይቱ ውስጥ የአይሁድ ማኅብረሰብ አባላት ነበሩባት። እነርሱም በጳውሎስና ሲላስ ላይ በማሤር የሮምን አስተዳደር አሳብ እስከማስለወጥ ደርሰው ነበር (የሐዋ. 17:5)። ይሁን እንጂ የሮም አስተዳደር ሕጋዊ ጥበቃ ስላደረገላቸው ጳውሎስና ሲላስ ከከተማይቱ ለመውጣት ቻሉ።

## የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን (የሐዋ 17:1–9)

ተሰሎንቄ በአማካኝ ስፍራ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ወንጌል ከዚያ በመነሣት በመቄዶንያ በሙሉ እንዲሁም በአካይያና ከዚያም አልፎ ተሰራጨ (1ኛ ተሰ. 1:8)። አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ከአሕዛብ ወገን ሲሆኑ፥ እጅግ ጠንካራና እንቅስቃሴ የሚታይባት ቤተ ክርስቲያን ሆነች (1ኛ ተሰ. 1:9–10፤ 2:14)።

ጳውሎስ ተገዶ ከተማይቱን ከለቀቀ በኋላ ተመልሶ ለመጐብኘት አስቦ ነበር፤ ሆኖም አልተሳካለትም (የሐዋ. 17:9–10፤ 1ኛ ተሰ. 2:18)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከአቴና የተሰሎንቄን ቤተ ክርስቲያን እንዲጎበኝ ላከው (1ኛ ተሰ. 3:2–10)።

ጳውሎስ በሦስተኛው ጉዞው ተሰሎንቄን ሳይጐበኝ አልቀረም (የሐዋ. 20:1፥3)። ጳውሎስ ከእስር ቤት ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ሊጐበኝ እንደሚፈልግ ጠቅሶ ነበር። ምናልባትም በሁለቱ እስራቶቹ መካከል ሳይጐበኛቸው አልቀረም (ፊልጵ. 1:25–26፤ 2:24)። በኤፌሶን ለነበረው ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክትም ሌላ ጕዞ ወደ መቆዶንያ ማድረጉን ገልጿል (1ኛ ጢሞ. 1:3–4)።

ከዚያ ጊዜ በኋላ ስለ ተሰሎንቄ ተጠቅሶ የምናገኘው ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ዴማስ ትቶት ወደ ተሰሎንቄ መሄዱን ሲያሳስብ ብቻ ነው።

ለብዙ ምእተ ዓመታት ከተማይቱ እጅግ ከጸኑት የክርስቲያን ከተሞች እንዷ ሆና ኖራለች፤ ስሟም፥ «የቀና ክርስትና እምነት ከተማ» ይባል ነበር፤ ምክንያቱም ያልሠለጠኑትን የጐረቤት አገሮች ወደ ክርስትና ለማምጣት በመቻሏና ለወንጌል በመቆሟ ነው።

## ለተሰሎንቄ ሰዎች የተጻፈው መልእክት

ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ሁለት መልእክቶች የጻፈው ተሰሎንቄን ለቅቆ እንደሄደ ወዲያውኑ ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ አዲስ ለመሠረታት የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋትን በቂ

ትምህርት ሳይሰጥ ከከተማይቱ እንዲለቅ ተገደደ። ስለዚህ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሆኖ ክርስቲያኖች ሆነው ስለሞቱት ሰዎች የገጠማትን የቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ለመመለስና የሞቱባቸውን ሰዎች ለማጽናናት ዐቅዶ የጻፋቸው መልእክቶች ሳይሆኑ አይቀሩም።

## ሐ/ የቤርያ ቤተ ክርስቲያን

በቤርያ ያሉ አይሁዶች «በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ጨዋዎች ነበሩ» (የሐዋ. 17፡11)። በተሰሎንቄ ካሉት ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል በተከፈተ አእምሮ ይመረምሩ ነበር። ከዚህም የተነሣ ብዙ አይሁዶችና አሕዛብ ክርስቶስን ተቀበሉ (የሐዋ. 17፡10–12)። ጳውሎስን እየተከታተሉ ያሳድዱት የነበሩት አይሁዳውያን መጥተው ችግር ስላስነሡ ጳውሎስ ከከተማይቱ ለመሸሽ ተገደደ። ሆኖም በቤርያ የነበሩት አይሁዶች በስደቱ ስላልተባበሩ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከተማ ውስጥ በመቅረት አገልግሎቱን ቀጠሉ (የሐዋ. 17፡13–15)።

ከዚያን ጊዜ በኋላ አናሲሞስ የቤተ ክርስቲያን ጳጳስ እንደነበረ ከሚነገርለት አፈ–ታሪክ በቀር ስለ ቤርያ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ነገር የለም።

## መ/ አቴና

### ከተማው

አቴና የአቲካ ዋና ከተማ ነበረች። የግሪክ ሥልጣኔ የሰፈነባት ከተማ ስትሆን በአሁኑ ጊዜም የግሪክ ዋና ከተማ ነች። የከተማይቱ ስም የተሰየመው አቴኔ በምትባለው ሴት አምላክ ስም ነው። አቴና ባላት ባህልና ትምህርት የተከበረች ነበረች። ከተማይቱ በ86 ዓ.ዓ. በሮማውያን ቊጥጥር ሥር ብትወድቅም በአውጉስጦስ አማካኝነት ነፃ ወጣች።

በእስክንድሪያ፥ ጠርሴስና አቴና ከሚገኙት ሦስት ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የአቴና ዩኒቨርስቲ ከሁሉም ታላቅ ነበር።

አቴና በፍልስፍና ትምህርት ቤቷ አማካይነት በጣም የታወቀች ነበረች። ክርስትናን ከአረማውያን ትምህርት ለመከላከል ታዋቂ መጻሕፍት ይጽፉ የነበሩት ምሁራን ብዙዎቹ የአቴና ሰዎች ነበሩ። የአቴና ፈላስፋዎች ጳውሎስን ወደ አርዩስፋጎስ ወሰዱት። አርዩስፋጎስ የግሪክ አምላክ የአርዩስ አደባባይ ነበረ። አርዩስ በግሪኮች አስተሳሰብ የጦርነት አምላክ ሲሆን፥ ሮማውያን ማርስ ብለው ይጠሩት ነበር። የአርዩስፋጎስ ሸንጎ በአቴና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነበር። የከተማይቱን ትምህርት ቤቶች በሙሉ ከመቈጣጠሩም በላይ

በከተማይቱ በኩል በማለፍ ንግግር የሚያደርጉትን መምህራንም ይቈጣጠር ነበር። ጳውሎስ ለዚህ ሸንጎ ንግግር እንዲያደርግ ተጠየቀ። እርሱም ስለ ሙታን ትንሣኤ በተናገረ ጊዜ ብዙዎቹ ፈላስፋዎች አፌዙበት፤ አንዳንዶቹ ግን ደግመው ሊሰሙት እንደሚፈልጉ ገለጹለት (የሐዋ. 17፡22–32)።

## ፍልስፍናዎች

ከብዙ ፍልስፍናዎች መካከል ሁለት ብቻ የብዙ ሰዎችን አእምሮ የሚማርኩ ነበሩ።

## የኢስጦኢኮች ፍልስፍና

ሰው ሙሉ በሙሉ በራሱ ዕቅድና አመለካከት እንዲተማመንና በማንኛውም ሁኔታ የበላይነት ስሜት እንዲኖረው የሚያደርግ ትምህርት ነበር። ይህም ሮማውያን ወደሚወዱት ወደ ትምክሕተኝነትና አምላክ ነኝ ወደ ማለት አሳብ መራቸው።

## የኤፊቆሮስ ፍልስፍና

ሰው ለዛሬው ብቻ መኖር እንዳለበትና ሥጋዊ ፍላጎቱን ሙሉ በሙሉ ማርካት እንዳለበት የሚያምን ነበር። ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት በሙሉ ይክዳል። ይህም ሮማውያንን ወደ ማፍቀር ወደ ወራዳና አሳፋሪ ፍትወት መራቸው። ለሮም መንግሥት ድክመት ምክንያት የሆነው ይኸው ነበር።

እነዚህ ሁለቱ ፍልስፍናዎች የሰውን ሞራል ስላላሸቁ የሰዎችን ልብ ለክርስቲያን ወንጌል መልእክት አዘጋጁ። ሆኖም እነዚህ ሁለት ፍልስፍናዎች የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ያስቸገሩና ቤተ ክርስቲያንም በወንጌል ተልእኮ ጒዞዋ የተዋጋቻቸው ነበሩ (የሐዋ. 17፡18)።

## የአቴና ቤተ ክርስቲያን

ጳውሎስ በምኩራብ ለአይሁዶች መሰከረ። በአሪዮስፋጎስ ሸንጎ መሰከረ፤ ሆኖም በአቴና የጳውሎስ ስብከት ውጤት በጣም አነስተኛ ነበረ። ከአርዮስፋጎስ ሸንጎ ያመነ አንድ ሰው፥ እንዲት ደማሪስ የምትባል ሴትና አንዳንድ ሌሎች ሰዎች ብቻ ነበሩ (የሐዋ. 17፡34)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ አቴና የተጠቀሰው በሐዋ. 17ና በ1ኛ ተሰሎ. 3፡1 ውስጥ ብቻ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የአቴና ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰችው በሁለተኛው ምእተ ዓመት ንጉሥ አንቶኒዩስ ፓዩስ የክርስቲያኖችን ጭንቀት ለመግታት በሞከረበት ወቅት ነው። በ529

ዓመተ ምሕረት ንጉሥ ጄስቲንያን የፍልስፍናን ትምህርት ከለከለ። የግሪክ ሥልጣኔ እንደገና በሰፈነበት ዘመን ጥንታውያን መቅደሶች የክርስቲያኖች የአምልኮ ቦታ ማለትም አብያተ ክርስቲያናት ሆኑ። በ1204 ዓ.ም. አቴና በላቲኖች ሥር ተገዛች። ይህም ቱርኮች መጥተው እስከገዟት እስከ 1456 ዓ.ም. ድረስ ነበር። በ1833 ዓ.ም. ዘመናዊ የግሪክ መንግሥት ተቋቋመ፤ አቴናም ዋና ከተማ ሆነች። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነፃ ሆና በአቴና ጳጳስ መመራት ጀመረች።

## የጳውሎስ ስብከት በአቴና–(የሐዋ. 17፡22–32)

ጳውሎስ የሚሰብካቸው ሰዎች ምን ዓይነት መሆናቸውን ያውቅ ነበር። ስለዚህ የማይታወቅ አምላክ ብለው የሠሩትን መሠዊያ በመጥቀስ ስለሚያውቁት ነገር በመናገር የማድመጥ ስሜታቸውን ሳበ። የእርሱ ተልእኮ ይህንን ያልታወቀ አምላክ ለእነርሱ ለመግለጽ መሆኑን ተናገረ።

እርሱም ግሪኮቹ የሚጠቀሙበትን ግጥም በመጥቀስ ሰው በሠራው ጣዖት በኩል ይህንን አምላክ ማምለክ እንደማይችሉ ጠቅሶላቸው ንስሐ እንዲገቡ እግዚአብሔር እንደ ጠራቸው ከነገራቸው በኋላ ሊመጣ ካለው ፍርድ እንዲድኑ መከራቸው። የእግዚአብሔርም ፍርድ መቃረቡን ገለጸላቸው። የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥራ፥ ፍርዱንና ለሰው ስላዘጋጀው የመዋጀት ዕቅድ አብራራላቸው። ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ፈራጅ እንደሚሆን ነገራቸው። ሆኖም ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ ሲናገር ፈላስፋዎቹ አፌዙበት (የሐዋ. 17፡22–32)።

በአንጻሩ ጳውሎስ ኢየሱስ እርሱ መሢሕ መሆኑን ለማረጋገጥ በጺስድያ ላሉት አይሁዶችና እግዚአብሔርን ለሚፈሩ አሕዛብ በሰበከላቸው ጊዜ ብሉይ ኪዳንን በመከለስ ነበር። በክርስቶስ በኩል አይሁዶችና አሕዛብ እኩል መሆናቸውን በማሳየት አሕዛብ የአይሁድን የሕግ ሥርዓት መጠበቅ እንደማያስፈልጋቸው አስተማረ።

## ሠ/ ቆሮንቶስ (የሐዋ. 18፡1–17)

### የቆሮንቶስ ከተማ

ቆሮንቶስ ሁለት ጥሩ ወደቦች የነበሯት በውኃ ዳርቻ የምትገኝ የግሪክ ከተማ ነበረች። ከተማዋ በመሬት መናወጥ ሁለት ጊዜ ተደምስሳ ነበር። በ146 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በጦርነት ተደምስሳ ነበር። በ46 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በጁሊየስ ቄሳር እንደገና ተቆረቆረችና በትዕቢተኞች አቴናውያን የተናቁ ድብልቅ ሰዎች

ሰፈሩባት። ከተማይቷ በፍትወትና በዝሙት የተበከለች ስለ ሆነች ለማስተዳደር እንኳ አስቸጋሪ ነበረች።

በ51 ወይም በ52 ዓ.ም. ላይ ጋልዮስ በአስተዳዳሪነት ተሹሞ ወደ ቆሮንቶስ መጣ (የሐዋ. 18፡12–17)። የጋልዮስ የፍርድ ወንበርና የሥጋ ገበያ የነበረ ስፍራ በቍፋሮ ተገኝተዋል (የሐዋ. 18፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 10፡25)።

## አቂላና ጵርስቅላ (የሐዋ. 18፡2)

በ49 ዓ.ም. አይሁድ የሆኑ ሁሉ ከሮም ግዛት እንዲባረሩ ቀላውዴዎስ ቄሣር አወጀ። አቂላና ጵርስቅላ ከሮም ግዛት ተባርረው ወደ ቆሮንቶስ ከገቡት መካከል ነበሩ። ሁለቱም ክርስቲያኖች ሲሆኑ ሥራቸውም ድንኳን መስፋት ነበር።

## አጵሎስ (የሐዋ. 18፡24–28)

ጳውሎስ ከኤፌሶን ተነሥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ጕዞውን ቀጠለ። አቂላና ጵርስቅላ ግን በኤፌሶን ቀሩ። የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው አይሁዳዊ አጵሎስ ከእስክንድርያ ወደ ኤፌሶን መጣ። እርሱም በብሉይ ኪዳን ትምህርት እጅግ የበሰለና ስለ ክርስቶስም ትክክለኛ የሆነ ዜና የሰማ ሰው ነበር። አጵሎስ ጐበዝ ተናጋሪና ስለ እውነት ያለውንም እውቀት በግልጽ ይሰብክ ነበር። ሆኖም ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ ክርስትና ጥምቀት አያውቅም ነበር፤ ሆኖም አቂላና ጵርስቅላ ይህንን ነገር ሊያስረዱት ቻሉ (የሐዋ. 18፡26)።

አጵሎስም ከኤፌሶን ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ በማስተማር ብዙ አይሁዶችን ለማሳመን ቻለ (የሐዋ. 18፡27–28)።

በቆሮንቶስ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በአንዳንድ ቡድኖች የተከፋፈለች ነበረች። አንዳንዶቹ የአጵሎስ ነን፥ ሌሎቹ የጳውሎስ ነን፥ ሌሎች የኬፋ ነን፥ ሌሎቹ ደግሞ የራሱ የክርስቶስ ነን በማለት ተከፋፈሉ (1ኛ ቆሮ. 1፡12)። ጳውሎስና አጵሎስ በአንድነት መሥራት ጀመሩ፤ ጳውሎስም እርሱና አጵሎስ በአገልግሎታቸው አንድ ላይ መሆናቸውንና መተባበራቸውን ለቆሮንቶስ ምእመናን ለማሳየት ሞከረ (1ኛ ቆሮ. 3፡4–6፥ 21–23)። ምንም እንኳ ጳውሎስ አጵሎስን አብረው ወደ ቆሮንቶስ እንዲሄዱ ቢጠይቀውም በነበረው መለያየትና የቡድን መንፈስ ምክንያት አጵሎስ ዳግመኛ ወደ ቆሮንቶስ መመለስ አልፈለገም፤ አልተመለሰምም (1ኛ ቆሮ. 16፡12)።

አጵሎስ ለመጨረሻ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በቲቶ መልእክት ውስጥ ስለ ጉዞው በተጻፈው ነገር ላይ ነው (ቲቶ 3፥12)።

አንዳንድ ሰዎች የዕብራውያንን መልእክት የጻፈው አጵሎስ ነው ይላሉ፤ ሆኖም ስለ መጻፉ የተገኘ ማስረጃ የለም።

## የጳውሎስን ሁለተኛው ወንጌላዊ ጉዞ የሚያመለክት ካርታ።



## ማጠቃለያ

ሁለተኛው የጳውሎስ ጉዞ የተደረገው ከ50 እስከ 54 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ የመንፈሳዊና የገንዘብ ፈተናዎች አጋጥመውታል። በእስያ፣ በሚሲያና በቢታንያ እንዳያገለግል በመንፈስ ቅዱስ ተከለከለ። በጐበኛቸው ከተሞች ከብዙዎቹ ስደት ደረሰበት። ጳውሎስ በጢሞቴዎስና በሲላስ መዘግየታቸው ምክንያት በተሰሎንቄ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን ሠግቶ ነበር። ከፊልጵስዩስ ርዳታ እስካገኘ ድረስ ድንኳን በመስፋት ራሱን ለመርዳት ተገድዶ ነበር። በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በአውሮፓ ተሰራጨ፣ በዚያ ያለችው ቤተ ክርስቲያንም ተቋቋመች።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ባስተማረበትና በሰበከበት ስፍራ ሁሉ ለሚነሣው ተቃውሞ ዋናው ምንጭ ምን ነበረ?
2. ከመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደሚሰጠው ጥምቀት የተደረገውን ሽግግር አስረዳ።
3. ጳውሎስ ካስተማረባቸው ስፍራዎች ሁሉ የቤርያ ነዋሪዎች በተለይም አይሁዶች የሚለዩበት ባሕርይ ምንድን ነው?
4. ጳውሎስ በአሪዮስፋጎስ ያሉትን የአቴና ፈላስፎች ስሜትና ፍላጎት እንዴት ሊማርክ ቻለ? የዚህ ማስተማር ዘዴ ጥሩነቱ ምንድን ነው?
5. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ድክመትና ችግር ሊፈጥሩ የቻሉት አንዳንድ ልምዶች ምን ምን ነበሩ?

# ትምህርት 6

## ሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ፥

## 52 እስከ 56 ዓ.ም. የሐዋ. 18፡23–21፡16

የትምህርቱ ዓላማ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያቋቁም መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደመራውና በመልእክቶቹ እምነታቸውን እንዴት እንደገነባ ለመረዳት እንድንችል ነው።

ጳውሎስ ሦስተኛውን ጉዞ የጀመረው በገላትያና በፍርግያ የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በድጋሚ በመጐብኘት፥ በመዘዋወር ደቀ መዛሙርትን እያበረታታና እያጠናከረ ነበር (የሐዋ. 18፡23)።

ከዚህ ቀደም ብሎ ባደረገው ጉዞ ወደ እስያ እንዳይሄድ መንፈስ ቅዱስ ከልክሎት ነበር። ይሁን እንጂ በጉዞው መጨረሻ ኤፌሶንን ጎብኝቶ ነበር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነም ዳግመኛ መጥቶ እንደሚጐበኛቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር (የሐዋ. 18፡19–21)።

ጳውሎስ በሦስተኛው ጉዞው ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ለሁለት ዓመታት ተቀመጠ።

## ጳውሎስ ገላትያንና ፍርግያን በድጋሚ ጎበኘ።



## 2. የጳውሎስ አገልግሎት በኤፌሶን

### ሀ/ የኤፌሶን ከተማ

ኤፌሶን የሮም ክፍለ አገር የሆነችው የእስያ ዋና ከተማ ነበረች። ከተማይቱ በመጀመሪያ የተቆረቆረችው በግሪክ ቅኝ ገዥዎች ሲሆን ጊዜውም በ1044 ዓ.ዓ. ነበር።

ኤፌሶን አርጤምስ ወይም ዲያና ተብላ ለምትጠራው ጣዖት ማዕከላዊ የማምለኪያ ከተማ ነበረች። የአርጤምስ ቤተ መቅደስ በዓለም አስደናቂ ነገሮች ተብለው ከሚጠሩት ከሰባቱ አንዱ ነው። ገበያና ንግድ እየቀዘቀዘ በሄደ ጊዜ ሕዝቡ የዕለት ኑሮውን ለመደገፍ የንግድ ጥቅም ለማግኘት ወደ አርጤምስ ቤተ መቅደስ ተመለከተ።

ከተማይቱ በእስያ ላለው የንግድ እንቅስቃሴ አምልኮ ማዕከል በመሆኗ ጳውሎስ ለሁለት ዓመት በተቀመጠበት ጊዜ ከመላው እስያ ለንግድና ለአምልኮ ለሚመጡ ሰዎች ወንጌል ያሰማና ያስተምር ነበር (የሐዋ. 19፡10)።

### ለ/ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን

ጳውሎስ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ «በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት» የተጠመቁ አሥራ ሁለት ሰዎች አገኘ። ጳውሎስ ሰዎቹን አስተማራቸው፤ ሰዎቹም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ። መጥምቁ ዮሐንስ ከእኔ በኋላ የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል ብሎ የሰጠው ተስፋ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በየትኛውም ምዕራፍ አልተጠቀሰም (ማር. 1፡8፤ ሉቃስ 3፡16፤ ዮሐ. 1፡33፤ የሐዋ. 1፡5፤ 10፡37፤ 11፡16፤ 13፡24)።

በኤፌሶን የነበሩት 12 ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውኃ ከተጠመቁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (የሐዋ. 19፡5–6)። የሰማርያ ሰዎች ባመኑ ጊዜ እነዚህ ሁኔታዎች የተፈጸሙት በተመሳሳይ መንገድ ነበር (የሐዋ. 8፡16–17)። «ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው» (የሐዋ. 8፡17፤ 19፡6)።

ጳውሎስ ለሦስት ወር በኤፌሶን ምኩራብ አስተማረ፤ ነገር ግን አንዳንድ አይሁዶች ልበ ደንዳኖች ስለነበሩ ወንጌልን ለመቀበል እምቢ አሉ። ስለዚህ ጳውሎስ እንደ ልማዱ ምኩራቡን ትቶ ወደ አሕዛብ ፊቱን አዞረ።

ጳውሎስ ምኩራቡን ትቶ ከምኩራቡ ቀጥሎ ባለው ጢራኖስ በተባለው አዳራሽ ውስጥ ለሁለት ዓመት አስተማረ። በዚያን ጊዜ

ውስጥ ከመላው እስያ የመጡ ብዙ አይሁዶችና ግሪኮች ወንጌልን ሰሙና ሌሎች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ተመሠረቱ። ኤጳፍራ በቈላስይስ ያገለግል ነበር (ቈላ. 1፡7)። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በዚያን ጊዜ ሳይሆን አይቀርም (ቈላ. 2፡1)። በራእይ 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት ጳውሎስ በኤፌሶን ባገለገለበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም።

## ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ራእይ 2–3




በወንጌል ምክንያት ብዙ ሕዝብ ከአርጤምስ አምልኮ ወደ ክርስቶስ ተመለሰ። አርጤምስን ማምለክ የኤፌሶን ባህል ስለነበረ ለአምልኮ

እንዲሆን የብር ማቅለጥ ሥራ የሚሠሩ ብር አቅላጮች የኤኮኖሚ ኪሳራ ደረሰባቸው። በዚህም ምክንያት በጳውሎስና በተባባሪዎቹ ላይ የከተማዋን ነዋሪ ሕዝብ ለተቃውሞ አነሣሡ። የጳውሎስ ተባባሪዎች ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን ይዘው ሲወስዷቸው ጳውሎስ እነርሱን ለማስለቀቅ ፈለገ፤ ነገር ግን ደቀ መዛሙርት ምንም ዓይነት ሙከራ እንዳያደርግ ከለከሉት። የከተማው ጸሐፊ በጳውሎስ ላይ ምንም ጥፋት አላገኘበትም። ተገፋፍቶ የመጣውንም ሕዝብ በጳውሎስ ላይ ወንጀል ካገኙ በፍርድ ቤት ክስ ሊመሠርቱ እንደሚችሉ ነግሮ በተናቸው። ከዚህ በኋላ ጳውሎስ በኤፌሶን ማስተማር እንደማይችል ስለ ተገነዘበ ወደ መቄዶንያ ሄደ።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ለብዙ ምእተ ዓመታት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ጸንታ እንደቆመችና በእስያ አገር ውስጥ ወንጌልን የማሰራጫ ማዕከል ነበረች።

## 3. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያደረገው የደብዳቤ ልውውጥ

### ሀ/ የጠፋው ደብዳቤ (1ኛ ቆሮ. 5፡9–13)

ጳውሎስ በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ ጽፎ ነበር። ይህ ደብዳቤ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ስለማይገኝ ሳይጠፋ አይቀርም፤ አንዳንዶች ይህ የጠፋው ደብዳቤ ከ2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ጋር ተደባልቋል የሚል አሳብ አቅርበዋል።

### ለ/ አንደኛው የቆሮንቶስ መልእክት

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብዛት የነበሩት ምእመናን ከአሕዛብ ወገን ስለሆኑ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተማሩ አልነበሩም። አብዛኛው ባህላቸው ከክርስትና መሠረታዊ ትምህርት ውጭ ነበር፤ ብዙ መማር ነበረባቸው (1ኛ ቆሮ. 3፡1–3)።

ከመጀመሪያው ደብዳቤ በፊት ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጻፈው (እኛ ባይኖረንም) ቤተ ክርስቲያኗ ለጳውሎስ የጠየቀችው ጥያቄ ነበር (1ኛ ቆሮ. 7፡1)። በቆሮንቶስ የነበረውን ችግር ለመፍታት ጳውሎስ ቲቶን ወደ ቆሮንቶስ ሰደደው፤ ከዚያም ከቲቶ ጋር በጢሮአዳ ለመገናኘት ዐቀደ። በዚያን ወቅት የቀሎዔ ቤተሰቦች ጳውሎስን ጐብኝተውት ነበር (1ኛ ቆሮ. 1፡11)። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለነበረው የከፋ መከፋፈል ነገሩት (1ኛ ቆሮ. 5፡1)። ይህን ከሰማ በኋላ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ ብለን የምንጠራውን መልእክት ጻፈላቸው።

### ሐ/ በሐዘን የተሞላው መልእክት (2ኛ ቆሮ. 2፡1–4፤ 12፡14፤ 13፡1)

ጳውሎስ የመጀመሪያው መልእክቱን ከጻፈላቸው በኋላ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጳውሎስን ሥልጣን መቃወምና ትምህርቱንም መንቀፍ የጀመሩ ይመስላል። ስለዚህ ጳውሎስ በሐዘን የተሞላውን መልእክቱን ከመጻፉም ሌላ ለነበረው ችግር መፍትሔ ለመስጠት «አሳዛኝ ጉዞ» ብሎ የጠራውን ጉዞ ወደ ቆሮንቶስ ተጓዘ (2ኛ ቆሮ. 2፡1፤ 12፡14፤ 13፡1)። ስለዚህኛው ደብዳቤና ጉዞ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ምንም አልተጠቀሰም።

### መ/ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 1 – 9

ጳውሎስ ወደ ጢሮአዳ በሄደ ጊዜ ቲቶን ባለማግኘቱ በጣም ስለሠጋ ወደ መቄዶንያ ሄደ (2ኛ ቆሮ. 2፡12–13)። በመቄዶንያ ምናልባትም በፊልጵስዩስ ጳውሎስ እንዳለ ቲቶ ስለ ቆሮንቶስ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ መልካም ዜና ይዞለት መጣ። ከዚህ በኋላ ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን ጻፈ። አንዳንድ ሰዎች ይህ ደብዳቤ 2ኛ ቆሮንቶስ ከምዕራፍ 1–9 ብቻ ነው ብለው ይገምታሉ።

### ሠ/ 2ኛ ቆሮንቶስ ከምዕራፍ 10 – 13

አንዳንዶች 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10–13 ያለው «በሐዘን የተሞላው መልእክት» ነው ብለው ያምናሉ። ምክንያቱም ጳውሎስ በእነኝህ ምእራፎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግርን ስለሚፈጥሩ ወገኖች ተቃውሞ ስለ ጻፈ ነው። ሆኖም ለዚህ አሳብ ምንም ማረጋገጫ የለም።

## 4. የሮሜ መልእክት

ጳውሎስ በቆሮንቶስ በነበረ ጊዜ በሮም ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ደብዳቤ ጻፈ (ሮሜ 1፡7)። የወንጌል መልእክት ስለተስፋፋ ጳውሎስ እስከ እስጳንያ ድረስ ለመጓዝ ተመኝቶ ነበር (ሮሜ 15፡24)። የሮሜ መልእክት ደብዳቤ ሳይሆን ከዚህ ቀደም ላልጐበኛቸው ሰዎች የጻፈው ስለ እምነቱ የሚገልጽ የእምነት መግለጫ የሆነ የጥናት መጽሐፍ ይመስላል ማለት ይቻላል። የሮሜ መልእክት ከደብዳቤ ይልቅ ጳውሎስ ወደ ፊት ለማድረግ ተስፋ ላደረገው የሮም ጉብኝቱ ዝግጅት ሳይሆን አይቀርም (ሮሜ 15፡24፥ 28)።

# የጳውሎስ መልእክቶች

| | መልእክቶች | ቀን | ከየት ቦታ እንደተጻፈ | የመልእክቱ ርእስ |
|---|---|---|---|---|
| የመጀመሪያው ወንጌላዊ | ገላትያ | 48 ዓ.ም. | አንጾኪያ ሶርያ | ደኅንነት በጸጋ |
| ጉዞ ፍጻሜ | 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ | 51 ዓ.ም. | ቆሮንቶስ | የክርስቶስ ምጽአትና የጌታ ቀን |
| ሁለተኛው ወንጌላዊ ጉዞ | 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ | 55 ዓ.ም. | ኤፌሶን | ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የጳውሎስ ሥልጣን |
| | ሮሜ | 56 ዓ.ም. | ቆሮንቶስ | ጽድቅ በእምነት |
| በእስር ቤት ሆኖ | ፊልጵስዩስ | 61–62 ዓ.ም. | በሮም እሥር ቤት | ሥቃይ |
| የተጻፉ | ቈላስይስ | 61–62 ዓ.ም. | በሮም እሥር ቤት | መንፈሳዊ ጉልምስና |
| መልእክቶች | ኤፌሶን | 61–62 ዓ.ም. | በሮም እስር ቤት | የመተባበርና የአንድነት አስፈላጊነት |
| | ፊልሞና | 61–62 ዓ.ም. | በሮም እስር ቤት | ንስሐ ለሚገባ ኮብላይ ይቅርታ |
| በሁለቱ የጳውሎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ | 62 ዓ.ም. | በጳውሎስ የመጀመሪያውና ሁለተኛው እሥራት መካከል | የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና አስተዳደር |
| እሥራት መካከል | ቲቶ | 62 ዓ.ም. | በጳውሎስ የመጀመሪያና ሁለተኛ እስራት | የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሥነ ምግባር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | መካከል | |
| የተጻፉ መልእክቶች | ዕብራውያን | 67–69 ዓ.ም. | ? | በቃሉ ጸና<br>የክርስቶስ ከሁሉ የበለጠ የበላይነት |

## 5. ጳውሎስ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ገንዘብ ስለማሰባሰቡ

የጳውሎስ ሦስተኛ ወንጌላዊ ጉዞ ዓላማ፡- በከባድ ራብ ለተጐዱ በይሁዳ ለሚኖሩ አማንያን የሚረዱበት ገንዘብ ለመሰብሰብ ነበር (1ኛ ቆሮ. 16፡1–4)። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ለርዳታው የሚውል ገንዘብ በቅድሚያ ሰብስባ ነበር (የሐዋ. 11፡27–30)።

በጳውሎስና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ለተነሣው ቅራኔ አንዱ ምክንያት ጳውሎስ ለራቡ ርዳታ ለመሰብሰብ በወሰደው እርምጃ ሊሆን ይችላል (1ኛ ቆሮ. 16፡1–4፤ 2ኛ ቆሮ. 8፥9)። ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸውን ግኙነት ለማቋረጥ የፈለጉ ሊኖሩ ይችላሉ (2ኛ ቆሮ. 1–7)።

በኢየሩሳሌም ላሉት ችግረኞች የሚደረገው የገንዘብ ስብሰባ በአይሁዶችና በአሕዛብ አማኞች መካከል ኅብረትን የሚፈጥር ከመሆኑም ሌላ፥ ጳውሎስ አገልግሎቱ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል የሚል ተስፋ ነበረው (ሮሜ 15፡25–32፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡14)። ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም የተሰበሰበውን ገንዘብ አሰባሰበ። ሆኖም የተሰበሰበውን ገንዘብ ካዋጡት አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ጋር ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ማስረከብ ይገባናል በሚለው አሳቡ ጸና (የሐዋ. 20፡4፤ 1ኛ ቆሮ.16፡3–4፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡16–21)።

## 6. የጳውሎስ መልስ ጉዞ (የሐዋ.20፡2–21፡15)

ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ በአይሁድ መርከብ ላይ እንዳለ ሊገድሉት ማሤራቸውን ገና ከቆሮንቶስ ሳይነሣ ሰማ። ስለዚህም ጳውሎስ የጉዞ ዕቅዱን ቀይሮ በመቄዶንያ በኩል በየብስ ተመልሶ ሄደ (የሐዋ. 20፡3)።

ጳውሎስ በመቄዶንያ በኩል በመመለሱ ከብዙ ምእመናን ጋር ተጨማሪ ግንኙነት እንዲያደርግ ጠቀመው፥ በፊልጵስዩስ ጥቂት ጊዜ ዐረፈ (የሐዋ. 20፡3–6)። በጢሮአዳም ዕረፍት አደረገ (የሐዋ. 20፡6–12)።

በሚሊጢንም ባረፈበት ወቅት የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አነጋገረ (የሐዋ. 20፡17)። ጳውሎስ ከኤፌሶን ለመጡት ሽማግሌዎች የሰጠው መልእክት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለክርስቲያኖች ስብሰባ የተናገረው ንግግር ነበር (የሐዋ. 20፡18-38)።



## 7. የጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ

ጳውሎስ የርዳታውን ገንዘብ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መመለሱ ይሠጋ ነበር (የሐዋ. 20፡22-23)። ጳውሎስ አደጋ እንደሚጠብቀው ስላወቀ በሮም የሚገኙትን ምእመናን እንዲጸልዩለት ጠየቀ። የጸሎት ጥያቄውም፡- የማያምኑ አይሁዶች ኢየሱስን መሢህቸው አድርገው እንዲቀበሉ፥ የርዳታው ገንዘብ በኢየሩሳሌም ምእመናን ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረውና ወደ ሮም ተመልሶ መሄድ እንዲችል ነበር (ሮሜ 15፡25-32)።

ሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ

| ዓመተ ምሕረት | የጐበኛቸው ስፍራዎች |
| --- | --- |
| 52 ዓ.ም. | ገላትያና ፍርግያ፥ የሐዋ.18፡23 |
| 53-56 ዓ.ም. | ኤፌሶን፥ የሐዋ. 19፡41 |
| 56 ዓ.ም. | መቄዶንያና አካይያ፥ የሐዋ.20፡1-5 |
| 56 ዓ.ም. | ጢሮአዳ፥ የሐዋ. 20፡6-12 |
| | ሚሊጢን፥ የሐዋ. 20፡13-14። |
| 56 ዓ.ም. | ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ፥ የሐዋ.21፡1-17 |
| 56 ዓ.ም. | በኢየሩሳሌም ታሠር፥ የሐዋ.21፡27-36 |

### ማጠቃለያ

ጳውሎስ በ13 ዓመት ጊዜ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ተጠቀመበት፤ ከሶርያዋ አንጾኪያና ከጠርሴስ ጀምሮ ታናሹ እስያን አቋርጦ እስከ ኤፌሶን ድረስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማቋቋም ችሏል። እንዲሁም በጢሮአዳ በመቄዶንያ፥ በአካይያ እስከ እልዋሪቆን ድረስ ተመሳሳይ ሁኔታ ሠርቷል። አብረውት የሚሠሩ ተባባሪዎች በመምረጥ ለሥራው አሠልጥኗቸዋል። እነርሱም ሉቃስ፥ ጢሞቴዎስ፥ ሲላስ፥ አርስጥራኮስና ቲቶ ነበሩ። ለብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናትም መልእክቶችን መጻፍ ጀምሮአል። ከጻፋቸውም ውስጥ ገላትያ፥ ቆሮንቶስ፥ ሮሜና ሌሎችም ይገኛሉ።

ጳውሎስ ባጋጠመው ተቃውሞ ውስጥ እያለ የአሕዛብን ቤተ ክርስቲያን በጠንካራ መሠረት ላይ መሥርቷል፤ እንዲሁም መንፈስ

ቅዱስ በገለጸለት መሠረት መሠረታዊና መለኮታዊ ትምህርት ሰጥቶአቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የጐደላቸው ምን ነበር?
2. በታናሹ እስያ ውስጥ ኤፌሶን ለወንጌል ስርጭት ማዕከል ለምን ሆነች?
3. አጵሎስ ማን ነው? አቂላና ጵርስቅላስ ምን ዓይነት ርዳታ ሰጡት?
4. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ወደ ሶርያ በመርከብ ከመሄድ ይልቅ በአካይያና በመቄዶንያ በኩል አቋርጦ ማለፉ ምን ጥቅም አስገኘለት?
5. አብያተ ክርስቲያናትን ለማጠናከር ጳውሎስ የፈጸማቸውን ሦስት ነገሮች አስረዳ።

# ትምህርት 7

## ጳውሎስ የደረሰበት መከራ

የትምህርቱ ዓላማ፡- እግዚአብሔር በሐዋርያት ሥራ 9፡15 ውስጥ ለጳውሎስ ያለውን ዕቅድ እንዴት እንደፈጸመለት መመልከት እንድንችል ነው።

### መግቢያ

ጳውሎስ ከተለወጠበት ጊዜ አንሥቶ ካለው የሕይወቱ ታሪክ ውስጥ አንደኛው ሥቃዩና መከራው ነበር። ጳውሎስ ለአሕዛብ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር መከራ እንዳለበት እግዚአብሔር ነግሮት ነበር (የሐዋ. 9፡15-16)። ጳውሎስ እንደተለወጠ ወዲያውኑ በደማስቆ በሚገኘው ምኩራብ ውስጥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በመስበኩ አይሁዶች ጳውሎስን ሊገድሉት ዐቀዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኢየሩሳሌም ያሉት ደቀ መዛሙርት በጥርጣሬ ተቀበሉት። በዚያን ጊዜ ከግሪክ አገር የመጡት አይሁዶች ጳውሎስን ለመግደል ስላሤሩ ደቀ መዛሙርት ጳውሎስን ወደ ጠርሴስ ላኩት (የሐዋ. 9፡29-30)። ይህ የጳውሎስ መከራ መጀመሪያ ሲሆን በሄደበት ስፍራ ሁሉ አዲስ ቤተ ክርስቲያንን እየመሠረተ ይሄድ ነበር።

## 1. በገላትያ የገጠመው ስደት (47 – 48 ዓ.ም.)

በጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ እርሱና በርናባስ እስከ የጲስድያዋ አንጾኪያ ድረስ ተጓዙ፤ ይሁን እንጂ ወዲያውኑ ከከተማይቱ ተባረሩ (የሐዋ. 13)። ጳውሎስና በርናባስ በኢቆንዮንና በልስጥራ ያደረጉት ጉብኝት መጨረሻው በድንጋይ ተወግረው ከከተማይቱ መባረር ነበር። ይህም ሁሉ ሆኖ ጳውሎስ መከራ በተቀበለባቸው ከተማዎች እየዞረ አዲስ ያመኑትን ሰዎች እንዲህ እያለ ያጽናና ነበር፡- «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልጋል» (የሐዋ. 14፡22–23 አንብብ)።

## 2. እስራትና ፌዝ በመቄዶንያና በግሪክ ደረሰበት (49 – 52 ዓ.ም.)

ጳውሎስ ወደ አካይያና መቄዶንያ እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ በራእይ መራው። በፊልጵስዩስ ከተማ አንዲት የተሸጠች አገልጋይ ልጃገረድ በሰይጣን መንፈስ ተሞልታ ጳውሎስና ሲላስ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸውን አወቀች። ከዚያም እየተከታተለች ስትጠራቸው ጳውሎስ በውስጧ ያለውን ርኩስ መንፈስ ገሥጾ አስወጣው። የልጅቷ ጌቶችም ይህንን ሲያዩ በጳውሎስና በሲላስ ላይ እጅግ ስለ ተቆጡ በበትር እየደበደቡ ወደ እስር ቤት አስገቧቸው (የሐዋ. 16፡19–24)። ከእስር እንደተፈቱ ወደ ተሰሎንቄ ሸሹ። ነገር ግን በተሰሎንቄ ያሉት አይሁዶች ሕዝቡን ስላነሣሡባቸው ከዚያም ለመሸሽ ተገደዱ። ጳውሎስና ሲላስ ወደ ቤርያም በሄዱ ጊዜ የአይሁድ እምነት አክራሪዎች ተከትለዋቸው በመምጣት የቤርያን ሰዎች አነሣሡባቸው። የጳውሎስ ጓደኞችም እርሱን ሸሽገው ወደ አቴና አሻገሩት። ጳውሎስ ወደ አካይያ የመሄድ ዕቅድ የነበረው አይመስልም፤ ሆኖም ወደ አቴን መሸሹ ወደ ግሪክ መቅደስ፥ ወደ መሠዊያቸው የጣዖት ምስላቸው መካከል እንዲገባ አደረገው። ጳውሎስ በምኩራብና በገበያ ስፍራ ስለ እምነት ሲከራከር ሳለ በአሪዮስፋጎስ ማለትም በከተማይቱ ምክር ቤት ወይም ፍርድ ሸንጎ ስለ እምነት ንግግር እንዲያደርግ ተጋበዘ። መልእክቱንም ባስተላለፈ ጊዜ የሕዝብ ሊቃውንት አፌዙበት (የሐዋ. 17)።

እግዚአብሔር ጳውሎስን በመቄዶንያ ወንጌልን እንዲሰብክ ቢጠራውም እንኳ ማረፊያ ስፍራ እስኪያጣ ድረስ አይሁዶች ከከተማ ወደ ከተማ እያባረሩት ተቸግሮ ነበር። ይሁን እንጂ ስብከቱ ያለ ፍሬ አልነበረም። በተሰሎንቄ፥ በቤርያና በፊልጵስዩስ መጠነኛ ቍጥር ያላቸው ማኅበሮች አቋቁሟል፥ ስለ እነርሱም ይጨነቅ ነበር። አቴና በደረሰ ጊዜ ይህን ያህል ተቃውሞ አልገጠመውም። የሰጠውን

መልእክት በአድናቆት በመገረም ቢያዳምጡትም ተቀባይነታቸው ይህን ያህል አልሆነም። ምናልባትም የእነርሱ ፌዝ ከስደቱ ይልቅ ጳውሎስን አሳዝኖት ይሆናል።

ጳውሎስ ሁልጊዜ ባለሥልጣኖችን የሚያከብር ቢሆንም፥ በገባበት ከተማ ሁሉ በመጨረሻው ላይ ረብሻ ይነሣበት ነበር። ጳውሎስ በመጥፎ ባህልና በአመንዝራነት ወደ ረከሰችው ወደ ቆሮንቶስ የደረሰው «በድካምና በፍርሃት፥ በብዙ መንቀጥቀጥም» ነበር (1ኛ ቆሮ.2:3)። ከጌታ በተሰጠው መገለጥ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ውስጥ 18 ወራት ለመቆየት ችሏል (የሐዋ. 18:9-10)። በከተማይቱ ውስጥ ትልቅና እንቅስቃሴ የሞላባት ቤተ ክርስቲያን ብትቋቋምም፥ ጳውሎስ ከተማዋን ከለቀቀ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ እርሱን መቃወምና መካድ ጀመረች። ከዚህም የተነሣ ጳውሎስ የልብ ስብራት ደረሰበት። ሆኖም ግን ይህ ገጠመኝ ጳውሎስን በሕይወቱ እንዲጐለምስና የመጋቢነትን ችግር መረዳት እንዲችል ረድቶታል።

## 3. በኢየሩሳሌም መታሠሩና በቂሣርያ ፍርድ ቤት መቅረቡ

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ቢመለስ እስራት እንደሚያጋጥመው ብዙዎቹ ቢያስጠነቅቁትና እርሱም እስራት እንደሚጠብቀው ቢያውቅም፥ በ56 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። በኢየሩሳሌም ሳለ ጳውሎስ ከመቅደስ ውስጥ ተጐትቶ ወጥቶ በአይሁዶች ከተደበደበ በኋላ በሮማውያን ዘበኞች ወደ እስር ቤት ገባ። በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ! ከዚያም ጳውሎስ ወደ ቂሣርያ ሲሄድ አይሁዶች በመንገድ ላይ በድብቅ ሊገድሉት እንዳሤሩ በታወቀ ጊዜ በሮም ወታደሮች ታጅቦ እንዲያመልጥ ተደረገ (የሐዋ. 21-23)። ፊልክስ የተባለው አስተዳዳሪ ከጳውሎስ ጉቦ መቀበል ፈልጎ ስለነበር ጳውሎስ በቂሣርያ ለሁለት ዓመት ታስሮ ቆየ። አዲስ የተሾመ አስተዳዳሪ ፊስጦስ በመጣ ጊዜ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ አሳብ አቀረበ። ሆኖም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ቢሄድ አደጋ ላይ ስለሚወድቅ ወደ ቄሣር ይግባኝ ጠየቀ (የሐዋ. 25)። ለዳግማዊ ሄሮድስ አግሪጳ ከእኅቱ ከበርኒቄ ጋር ያደረገው ጉብኝት ጳውሎስ በነገሥታትና በአስተዳዳሪዎች ፊት ቆሞ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክርበትን ሌላ ተጨማሪ ዕድል ሰጠው (የሐዋ 9:15-16)።

## 4. አሥጊው የሮም ጉዞ (60-61 ዓ.ም).

ጳውሎስ እንደ እስረኛ በሮም ወታደሮች ታጅቦ ወደ ሮም ተላከ። ጳውሎስ የጉዞው ኃላፊ በሆነ በሮም የመቶ አለቃ ዩልዩስ ቁጥጥር ሥር ቢሆንም ጓደኞቹ ሉቃስና አርስጥሮኮስ አብረውት ነበሩ። የባሕሩ

ማዕበል፥ የመርከቡ ሠራተኞች ዓመፅና እስረኛ ሊደርስበት የሚችለው የመሰየፍ ሥጋት ጉዞውን እጅግ አሥጊና አስጨናቂ አድርጎት ነበር። መርከቢቱ ተሰባብራ ከአገልግሎት ውጭ ከመሆኗ በስተቀር በውስጧ የነበሩት ተሳፋሪዎች በሙሉ ወደ መላጥያ ደሴት ለመድረስ ቻሉ። ከብዙ ሳምንታት ኋላም ወደ ሮም ተሻገሩ (የሐዋ. 27 እና 28)።

## 5. የጳውሎስ እስራት በሮም ከተማ (61–62 ዓ.ም.)

እስረኛው ጳውሎስ ሮም ወስጥ በሚኖርበት በራሱ ቤት እንግዶች ለመቀበል ይችል ነበር፤ ይሁን እንጂ ምን ጊዜም በሮም ወታደር ዘብ ይጠበቅ ነበር። ጳውሎስም ለሁለት ዓመት በእስር ላይ እንዳለ አገልግሎቱን ቀጠለ። የሚሰጠውም አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ያለማቋረጥ ለሚለዋወጡት የሮም ወታደር ዘቦች ነበር። ከሁለት ዓመት በኋላ ጳውሎስ ተፈታ። ከዚያም በድጋሚ ተይዞና ታስሮ በ67 ዓ.ም. እስከ ተገደለበት ጊዜ ድረስ ለሁለት ዓመት አብያተ ክርስቲያናትን በድጋሚ እየተዘዋወረ ይጐበኝ ነበር።

### ማጠቃለያ

ጳውሎስ በፍቅር የተሞላና ሰዎች በቀላሉ ሊቀርቡት የሚችሉ ዓይነት ሰው በመሆኑ ብዙ ታማኝ የሆኑ ጓደኞችን ለማፍራት ችሏል። እነዚህ ያፈራቸው ጓደኞቹ አደገኛ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ስለ እርሱ ሕይወታቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች ነበሩ። ጳውሎስ ያፈራቸው ምእመናን እርሱን የሚያስደስቱና የሚኮራባቸው ሲሆኑ እነርሱን ለማፍራት ብዙ ሥቃይ ስለተቀበለ በተቀበለው መከራና ሥቃይ አማካኝነት ያተረፉቸው ዋጋዎቹ ናቸው። ጳውሎስ መከራን ታገሠ። መከራንም የተመለከተው እንደ እምነት ሕይወት አንደኛው ክፍል እንደሆነና መከራን መቀበል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ምልክት እንደሆነ አድርጎ ነበር።

ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች እንዲህ ይላቸዋል፦ «በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል» (ቈላ. 1፡24)። ለቆሮንቶስ ሰዎችም፥ «መከራን ብንቀብል፥ ስለ መጽናታችሁ ስለ መዳናችሁ ነው» ብሏቸዋል (2ኛ ቆሮ. 1፡6)።

### ጥያቄዎች

1. የጳውሎስ እስራትና መከራ ለምስክርነቱ መንሥኤ የሆነበትን ሦስት ወቅቶች ጻፍ።

2. ብዙ ጊዜ ለመቀበል በጣም ከባድና አስቸጋሪ የሚሆነው ስደት ምን ዓይነቱ ነው?

3. መከራና ስደት ለመንፈሳዊ ዕድገት መንሥኤ የሚሆንበትን መንገድ አብራራ።

4. መከራ ወይም ስደት ለመንፈሳዊ ዕድገት ምክንያት እንዲሆን ለማድረግ ክርስቲያኖች መከራን ወይም ስደትን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሊቀበሉት ይገባቸዋል? ቈላ. 1፡24 ተመልከት።

# ትምህርት 8

## ጳውሎስ ስለ መከራ የሰጠው ትምህርት

የትምህርቱ ዓላማ፦ እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ዓላማ እንዳለው እንድናውቅና መከራንና ስደትን ለራሱ ቤተ ክርስቲያንና ለልጆቹ ዕድገት እንደሚጠቀምበት ለመረዳት እንድንችል ነው።

### መግቢያ

ከሐዋርያት ሥራ አንድ አራተኛው የሚያክለው ክፍል የሚነግረን ስለ ጳውሎስ እስራት፥ ለፍርድ ስለ መቅረቡና ስለ ረጅሙ የባሕር ጕዞው ነው። ሉቃስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈው የሮም ባለሥልጣን የሆነው ቴዎፍሎስ ክርስትና ከፖለቲካ ፍላጎት ነፃ የሆነና ከሮምም መንግሥት ጋር ምን ጊዜም ሰላማዊና ጤናማ ግንኙነት ያለው መሆኑን ለማሳወቅ ነበር። የስደቱ መንሥኤ በሃይማኖት ምክንያት ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚነሣውም ከአይሁዶች ነበር።

ጳውሎስ አገልግሎቱ ፍጻሜ እንዳያገኝ የሚያሰናክለው ማንኛውም አደጋ ወይም ስደትና እስራት እንኳን ቢያጋጥመው ይህንን ፈርቶ ሥራውን ከመፈጸም ወደኋላ አይልም ነበር። ክርስቲያን ችግሮችን እንዴት መቀበል እንዳለበት በቅድሚያ በራሱ ሕይወት ባሳለፈው ገጠመኝ ምሳሌ በመሆን፥ ቀጥሎም በጻፋቸው ምክር አዘል መልእክቶቹ ሰጥቷል።

## 1. ክርስቲያን መከራ እንደሚያጋጥመው መጠበቅ አለበት

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተ በኋላ ወዲያውኑ በአማኞች ላይ ስደት ተጀመረ። መከራ ወይም ስደት ለደረሰባቸው አብያተ ክርስቲያናትና ግለሰቦች ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች ብዙዎቹ እንዲያጽናኗቸው የተጻፉ ማጽናኛዎች ነበሩ።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጳውሎስ ማንኛውንም ዓይነት ስደት በመቀበል የራሱ የሆነ ገጠመኝ ነበረው። ይሁን እንጂ በሰውነቱ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱበት ስደት ይልቅ እጅግ ከባድ ሆኖ ያገኘው መዘባበቻ፥ መሳለቂያና ማፌዣ ሲያደርጉት ነበር። ጳውሎስ ድንኳን በመስፋቱ እንደ ነውር በሚቈጥሩት ግሪኮች ዘንድ ማላገጫ ሆኖአል። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ስለ ክርስቶስ ስንል ሞኞች ሆንን» ይላል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሐሰት በመወንጀል ልቡን እንዲረበሽ በማድረግ ከማንኛውም አብያተ ክርስቲያናት ይልቅ ጳውሎን አሳዝነውታል። ጳውሎስ ጠንካራ ደብዳቤ የሚጽፍ ወደ እነርሱ ሲቀርብ ግን ደካማና ፈሪ እንደነበር የቆሮንቶስ ምእመናን ይተቹት ነበር (2ኛ ቆሮ. 10:10)። በእጆቹ የጕልበት ሥራ በመሥራት ክብሩን ያልጠበቀ እንደነበርና ከዚያ ይልቅ ከእነርሱ ገንዘብ ቢቀበል ኖሮ ከውርደቱ ሊድን ይችል እንደነበር ተናግረዋል (2ኛ ቆሮ. 11:7)። ጳውሎስ ደንበኛ ከነበሩት ሐዋርያት አንዱ እንዳልነበረና ለማስተማር ብቁ እንዳልነበረ ይናገሩ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11:5፤ 12:11–12)። ጳውሎስን ዓለማዊ ነው ብለው ይወነጅሉት ነበር (2ኛ ቆሮ. 10:2)። በትዕቢተኛነትም ወነጀሉት (2ኛ ቆሮ. 10:8፥ 15–16)። ሸንጋይ ወይም ተንኮለኛ ብለውታል (2ኛ ቆሮ. 12:16)። የተሰጠውንም ገንዘብ ያለአግባብ ተጠቅሞበታል በሚልም ወንጅለውታል (2ኛ ቆሮ. 8:20–23)።

በኋላም ምንም እንኳ ጳውሎስ ራሱ በእስራት ላይ ቢሆንም ስደትን በሚመለከት ማጽናናትንና ማስጠንቀቂያ የያዘ መልእክት በኤፌሶንና በፊልጵስዩስ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ሊጽፍላቸው ችሏል። በዓለም ላይ ያሉ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ጦርነት ላይ መሆናቸውን አስታውሶአቸዋል (ኤፌሶን 6:12)። የራሱ መታሰር አማኞች በድፍረት እንዲመሰክሩና ወንጌልን በማሰራጨት ረገድ ወደ ፊት እንዲገሠግሡ ምሳሌነት ያለው መሆኑን ነገራቸው።

ለራሳቸው ፈቃድና ምቾት በመሞት አማኞች የክርስቶስ መከራ ተካፋይ ይሆናሉ (ፊልጵ. 3:8–10)።

የዕብራውያን መልእክት እንደሚገልጸው ለተሻለና ዘላለማዊ ለሆነ ተስፋ በምድር ላይ የሚደርስባቸውን የንብረት መውደም በደስታ ይቀበሉታል (ዕብ. 10:34)። የእግዚአብሔር ሰው መሆን በሕይወት ጊዜ መከራንና የኑሮ መመሰቃቀልን ያስከትላል፤ እምነት ግን ሁኔታዎችን የመቀበል ጸጋ ይሰጣል።

ይህን እምነት የሚገልጹ ከዕብራውያን መልእክት አንዳንድ ምሳሌዎችን እንመልከት።

ሀ/ አብርሃም ገና ያላየውን ርስት ለመቀበል ቤቱን ተወ (ዕብ. 11:8)።

ለ/ አብርሃም ልጁን አሳልፎ ሰጠ (ዕብ. 11:17-18)።

ሐ/ ሙሴ ከሕዝቡ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ (ዕብ. 11:25-26)።

መ/ አንዳንድ ቅዱሳን በአንበሳ ጕድጓድ ተጣሉ፤ አንዳንዶቹ ተሠቃዩ፤ አንዳንዶቹ ተላገጠባቸው፤ አንዳንዶቹ ተገረፉ፤ አንዳንዶቹ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፤ አንዳንዶቹም ቤታቸውን ጥለው ተሰደዱ፤ አንዳንዶቹም በመጋዝ ለሁለት እየተሰነጠቁ ሞቱ (ዕብ. 11:33-38)።

ክርስቲያኖች በወንጌልም ሆነ ወንጌል በሚያስከትለው መከራ ማፈር የለባቸውም (2ኛ ጢሞ. 1:8-10)። በክርስቶስ ሆነው እግዚአብሔርን የሚወዱ ሁሉ መከራን ይቀበላሉ (2ኛ ጢሞ. 3:10-13)። እግዚአብሔር የዘገየ ቢመስልም የራሱ የሆነ ጊዜና ዓላማ ስላለው ክርስቲያኖች በመከራ ታጋሾች መሆን አለባቸው (ዕብ. 10:35-38)። በክርስቶስና በዓለም መካከል ያለው ቅራኔ በሰፋ ቍጥር ስደቱ እየጨመረ ይሄዳል።

## 2. የክርስቶስ መሠቃየት ዓላማ

የክርስቶስ መሠቃየት እግዚአብሔር ለዓለም ሲል ያቀደው ነው።

ሀ/ እኛ ጻድቃን እንድንሆን እርሱ የእኛን ኃጢአት ተሸከመ (2ኛ ቆሮ. 5:21)።

ለ/ እኛ ሀብታሞች እንድንሆን እርሱ ስለ እኛ ድሀ ሆነ (2ኛ ቆሮ. 8:9፤ ፊልጵ. 2:7-8)።

ሐ/ የራሱን ሕዝብ በገዛ ደሙ እንዲቀድስ ክርስቶስ ተሠቃየ (ዕብ. 13:12)። ምንም እንኳ ክርስቶስ በመሰቀሉና ከሞት በመነሣቱ ለደኅንነት የሚገባውን ሥራ ሁሉ ቢፈጽምና አዲሱን ኪዳን ቢመሠርትም አሁንም በሕዝቡ ሥቃይ እርሱም እየተሠቃየ ነው (ቈላ. 1:24፤ ዕብ. 2:18)።

መ/ የክርስቶስ ሥቃይ ሰዎች የእርሱ ክብር ተካፋዮች እንዲሆኑ መንገድ ከፍቷል (ዕብ. 2:9-10)።

## 3. የእግዚአብሔር ቃል በስደት አይታገድም

የጳውሎስ በኤፌሶን፥ በቂሣርያ፥ በሮምና በሌሎችም ስፍራዎች መታሰር ወንጌልን ለማሰራጨት ምክንያት እንደሆነ ተመልክተናል

(ፊልጵ. 1፡12–13)። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዳለው «የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም» (2ኛ ጢሞ. 2፡9–10)።

ሐዋርያት እንደ መቀለጃና መጫወቻ ተደርገው ቀርበዋል (1ኛ ቆሮ. 4፡9)። መልእክታቸው በመከራቸው ሊሰራጭ ችሏል፤ በስደትና በመከራ ሁሉ ምሳሌ መሆን ነበረባቸው (2ኛ ቆሮ. 6፡3–10)።

## 4. የፍርድ ቀን ቀርቧል

ጳውሎስ በመልእክቶቹ ክርስቶስ ሊፈርድ እንደሚመጣ ደጋግሞ አስጠንቅቋል። በዕብ. 9፡27 ውስጥ ከሞት በኋላ ፍርድ እንደሚጠብቀን አስጠንቅቋል። ክርስቶስ ለሚያምኑትም ለማያምኑትም ፈራጅ ነው (ሮሜ. 2፡4–11)። ክርስቶስ በልብ ውስጥ የተደበቀውን እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ነገር ይገልጻዋል (1ኛ ቆሮ. 4፡5)። ሁሉም በሥጋው ለሠራው ሥራ መልስ ይሰጥበታል ( ዮሐ. 5፡28–29፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡10)። ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ዓመፅ ይበዛል (2ኛ ተሰ. 2፡3–4)።

## 5. እግዚአብሔር በጽድቅ ይፈርዳል

እግዚአብሔር በእውነተኝነት ይፈርዳል (ሮሜ 2፡2)። በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው ይፈርዳል (ሮሜ 2፡6)፤ እንዲሁም በልቡ ባለው እውነተኛ ዓላማና ዕቅድ ይፈርዳል (1ኛ ቆሮ. 4፡5)።

በክርስቶስ መሠረት ላይ በታማኝነት የሚገነቡ ክርስቲያኖች የድካማቸውን ዋጋ ለመቀበል በፍርድ ወንበር ፊት ይቀርባሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡10–15)። ይህም ዋጋ የሚሰጠው በክርስቲያኖች አገልግሎት መሠረት ነው (1ኛ ቆሮ. 3፡8)።

እግዚአብሔር ግን ለእኛ ለክርስቲያኖች ከምንገምተው በላይ የሆነ ነገር አዘጋጅቶልናል።

## ማጠቃለያ

1. እኛ ክርስቲያኖች መከራ እንደሚመጣ ማወቅ አለብን፤ ሆኖም ተስፋችን ለተሻለውና ለዘለዓለማዊ ነገሮች ስለሆነ መከራን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አድርገን መቀበል ይኖርብናል እንጂ እንደተጣልንና እንደተረሳን አድርገን መቍጠር የለብንም።
2. የጳውሎስ እስራት ምሳሌነት ያለውና ወንጌልን ለማስፋፋት ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ክርስቲያኖችም የሚደርሰውን ሁሉ በትክክለኛው መንገድ ከተቀበሉት ምስክርነት ሊሰጥ ይችላል።

3. የክርስቶስ ሥቃይ ጽድቃችንን፣ ቅድስናችንንና የእርሱ ክብር ተካፋይ የመሆናችንን ተስፋ የተሟላ አድርጎታል።

4. ክርስቶስ ለፍርድ ይመጣል፣ ሲመጣም ፍርዱ በጽድቅ ይሆናል፣ ለእርሱ ታማኝ ለሆኑት የሚገባቸውን ሽልማት ይሰጣቸዋል።

5. መከራ መቀበል የሐዋርያነት ምልክት ነው።

6. የእግዚአብሔር ቃል በስደት አይታቀብም።

## ጥያቄዎች

1. የጥንት ክርስቲያኖች መከራና ስደት እንዲቀበሉ ጳውሎስ በምን መንገድ ረዳቸው?

2. በአካይያና በመቄዶንያ ያሉ ሰዎች ጳውሎስን እንዲሰድቡ ያደረጋቸው ምን ባህላዊ ምክንያት ነበር?

3. አማኝ ወደ ክርስቶስ ሥቃይ ተካፋይነት ውስጥ እንዴት ሊገባ ይችላል? (ፊልጵ. 3፡8-11 ተመልከት)።

4. በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለነበሩና ወደ ፊት ለሚያገኙት ቃል ኪዳን ተስፋ አድርገው ስለተሠቃዩ ሰዎች ሦስት ምሳሌዎችን ስጥ።

5. ክርስቶስ የተሠቃየበትና መከራ የተቀበለበትን ሦስት ምክንያቶች ስጥ። (2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ 8፡9፤ ዕብ. 2፡9-10፥ 18 ተመልከት።)

6. መከራ የምን ምልክት ነው?

# ትምህርት 9

## የሰው መሠረታዊ ፍላጎት፦ ጽድቅን በእምነት ማግኘት

የትምህርቱ ዓላማ፦ ጳውሎስ ጽድቅ በእምነት እንጂ በሕግ ሥራ ያለመሆኑን በማስተማሩ ያጋጠመውን ችግርና ተቃውሞ ለመረዳት እንድንችል ነው።

## መግቢያ

የወንጌል ለአሕዛብ መዳረስ አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ፈጥሮ ነበር። ይህ የወንጌል ስርጭት ዜና በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በደረሰ ጊዜ ታላቅ ደስታን ሲያስገኝ፥ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሲደርስ ግን ከባድ የሃይማኖት ክርክር አስነሣ። በአሕዛብ ዘንድ ባለው ሥነ-ምግባራዊ አቋም በአይሁዶች ዘንድ ክብር አልነበረም። የክርስትና መመዘኛ ክርስቶስ በሰጠው አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ብቻ

የተመሠረተ ነበረ። ምንም እንኳ ኢየሱስ እንደ ምግብና ሰንበትን መጠበቅ የመሳሰሉትንና ሕግን ማክበርን ዋጋ ባይሰጠውም እንደ ፍትሕ፥ ምሕረትና ታማኝነት የመሳሰሉትን ሰዎች እንዲፈጽሙ ይጠብቅባቸዋል (ማቴ. 23፡23)። ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ሲወራረስ የመጣውን የበለጠውን ጽድቅ ደቀ መዛሙርቱ እንዲከተሉ ትምህርት ተሰጥቶአቸው ነበር (ማቴ. 5፡20)። ስለሆነም በጳውሎስና በተባባሪዎቹ አማካኝነት አሕዛብ ወንጌልን የመቀበላቸው ዜና ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ አስቸጋሪ ሥራ ሽማግሌዎች ፊት ተደቀነ። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በአይሁድ እምነት ተከታዮች ተቃውሞ ተነሣባት። ያዕቆብ ተገደለ፥ ጴጥሮስም ታሰረ። ስደቱም ሄሮድስ አግሪጳ እስከሞተበት እስከ 44 ዓ.ም. ድረስ ቀጠለ (የሐዋ. 12፡1–3)። ከዚህ ተቃውሞ በኋላ ነፃ አውጪ ቡድን የተባሉት መጡ፤ በአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ እነኝህን ነፃ አውጪዎች «ሽፍቶች» ይላቸዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የገሊላው ይሁዳ ነበር (የሐዋ. 5፡37)። ይህንንም ተቃውሞ የሚያደርጉት ከሮማውያን ጋር በመተባበር እንደነበረ ይነገራል። ስለሆነም በመስፋፋት ላይ ያለው የወንጌል በአሕዛብ ዘንድ መሰራጨት በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንና በመሪዎቿ ላይ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ የሆኑ ችግሮችን ፈጠረ። አማንያን የሆኑ አሕዛብን በሙሉ እንዲገረዙ መጠየቅ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ላለው መከፋፈል መፍትሔ ይሰጣል ብለው አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች አሰቡ። ነፃ አውጪዎች የተባሉትም እንኳን በዚህ አሳብ መስማማት ይችሉ ነበር። አንዳንዶች ከአይሁድ ወገን ያመኑት ክርስቲያኖች በዚህ አሳባቸው ጸንተው ስለተሟገቱ ለኢየሩሳሌም ጉባኤ መጠራት መንሥኤ ሆነ (የሐዋ. 15)።

## 1. ጽድቅ በእምነት ነው የሚለው የጳውሎስ መልእክት

### ሀ/ ከሐዋርያት ሥራ

በአይሁድ ክርስቲያኖችና በአሕዛብ ክርስቲያኖች መካከል የተቀሰቀሰውን ችግርና ብጥብጥ ጳውሎስ ተገንዝቦ ነበር። እንዲሁም የአይሁድ ክርስቲያኖች ቀስ በቀስ አሮጌውን ትእዛዝ በከፊል ወደ አዲሱ የጸጋ ትእዛዝ ለማስገባት እንደሚሞክሩ ተገነዘበ። ጳውሎስ በሕይወቱ ዘመን በአንድ ወቅት ለሥርዓት በመታዘዝ የራሱን ጽድቅ በመሥራት ተማምኖ ነበር፤ አሁን ግን የተሻለ መንገድ በእግዚአብሔር በኩል አግኝቷል።

ክርስቶስ ለሁሉም የበለጠ መንገድ ለመሆኑ ለጳውሎስ ማረጋገጫ የሆነው፦ የራሱ መለወጥና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በመገለጥ ማየቱ ነበር (የሐዋ. 9)። ጳውሎስ ከሦስት ዓመት በኋላ ማለት ወደ

አገልግሎቱ መጨረሻ ሲቃረብ በመጀመሪያ በደማስቆ መንገድ ላይ የተገለጸለትን «ጽድቅ በእምነት ነው» የሚለውን ያንኑ ወንጌል ይሰብክ ነበር (የሐዋ. 22፡1-6፥ 26፡9-18)።

## ለ/ የጳውሎስ የጉዞ መልእክቶች

ጳውሎስ በገላትያ አገልግሎ ከሄደ ከጥቂት ቀናት በኋላ የአይሁድ እምነት የሚከተሉ ክርስቲያኖች በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመሄድ፥ ከአሕዛብ ወገን ያመኑ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ለመሆን፥ የኦሪትን ሕግ መጠበቅ እንዳለባቸው አጥብቀው ማስተማር ጀመሩ። የአይሁድ እምነት ተከታዮች የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳመን የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን ማጥፋት እንዳለባቸው ተገነዘቡ። ስለዚህ ጳውሎስ ደጋግሞ ስለ ሐዋርያነቱ መሟገት አስፈላጊ መሆኑን ተገነዘበ። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንዲህ አለ፡- «እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን» (ገላ.1፡6-8)። ጳውሎስ የሰበከው ወንጌል ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ በመገለጥ የተቀበለው ነው።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ በሰበከ ጊዜ የማያምኑ አይሁዶች ቀንተው የከተማይቱን ሰዎች በተቃውሞ አስነሡበት። መንግሥታትን በመቃወም እንቅስቃሴ ያካሄዳል በማለት ከባድ ክስ አቀረቡበት (የሐዋ. 17፡6-7)። ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ሆኖ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ጽፎ በላከው መልእክቱ ጽድቅ በእምነት ነው የሚለው የወንጌል መልእክቱ ትክክለኛነት በሕይወታቸው ውስጥ ባስገኘው ውጤት ሊረጋገጥ እንደቻለ አስረዳቸው። እነርሱም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት አማኞች ሁሉ ምሳሌ ሆኑ (1ኛ ተሰ. 1፡7)። ስደትን ቢቀበሉም ምስክርነታቸውን ሊገታ አልቻለም (1ኛ ተሰ. 1፡8)። «ጽድቅ በእምነት ነው» የሚለው መልእክት ኃይል ያለው ነበር።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በቡድን የተከፋፈለች ሥጋዊ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ትኩረታቸው በንግግር፥ በፍልስፍናና በሰው ጥበብ ላይ ነበር። ጳውሎስ በዚህ ምክንያት የክርስትና መገለጥ በሰው ጥበብ ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ የቆሮንቶስን አማኞች አስገንዘበ (1ኛ ቆሮ. 2፡4-5)። የእግዚአብሔርን ነገር ሊገልጽ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። የጌታን አሳብ መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል (1ኛ ቆሮ. 2፡9-12)። ይህ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነበር፤ እንዲሁም በዘመናችን ለብዙ ሰዎች ሕይወት አስፈላጊ ነው።

ጳውሎስ በጻፈው በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክት በሐዋርያዊ ሥልጣኑ ለሰበከው ወንጌል መሟገቱ አሁንም ገና አስፈላጊ ነበር።

ጳውሎስ ወደ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ስለ እርሱ ሐዋርያነት የሚናገር ማመልከቻ ደብዳቤ ሊወስድላቸው እንደማይገባና እነርሱ ራሳቸው ጳውሎስ ለሰበከው ወንጌል እውነተኛነት ምስክሮች እንደሆኑ ለቆሮንቶስ ሰዎች ነገራቸው (2ኛ ቆሮ. 3፡1–2)። አዲሱ ቃል ኪዳን እንደ አሮጌው ቃል ኪዳን በድንጋይ ጽላት ላይ የተጻፈ ሳይሆን በሰዎች ልብ ላይ በሕያው እግዚአብሔር ጸሐፊነት የተቀረጸ ነው (2ኛ ቆሮ. 3፡3)። ጽድቅ በክርስቶስ በእምነት መገኘቱ የኦሪትን ሕግ ሳይደመስሰው ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለተሰጠው ትምህርት እውነተኛ ፍጻሜ ሰጥቶታል። የቀድሞው ኪዳን ተሟልቶ ሊፈጸም የሚችለው በክርስቶስ ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቀን ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ሆኖ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና» (2ኛ ቆሮ. 5፡18፤19)። «እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

ጳውሎስ በሮም የሚገኙትን ክርስቲያኖች ለመጐብኘት ከመሄዱ በፊት በቆሮንቶስ ሆኖ የሮሜን መልእክት ጻፈ። ጳውሎስ በደረሰበት ቦታ ሁሉ ከአይሁዶች የሚያጋጥመው የመረረ ተቃውሞ «ጽድቅ በእምነት ብቻ ነው» በሚለው ትምህርቱ ምክንያት ነበር። ስለሆነም ጳውሎስ የሮሜ መልእክቱን የጻፈው ስላለው እምነት የሮም አማኞች ከራሱ ምስክርነት በመስማት ትክክለኛው አስተሳሰቡ እንዲገባቸው ሲሆን፥ በተለይም ሕግና ወግ አክራሪ የሆኑት ቀድመው በመሄድ የተዛባ ነገር እንዳይነግሯቸው በማሰብ ሳይሆን አይቀርም። በእምነት ብቻ የሚገኘው ጽድቅ የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ነው፤ ውጤቱም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መፍጠርን፥ ጸጋውን ለማግኘት ማስቻልን፥ በመከራ መደሰትን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡና ውስጥ ማግኘትንና፥ የዘለዓለም ተስፋን፥ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን፥ በእግዚአብሔር ነፃ መሆንንና በክርስቶስ ብፅዕና ማግኘትን ያስከትላል (ሮሜ. 5፡1–11፥ 5፡18–21)።

## ሐ/ ከእስር ቤት የተላኩ የጳውሎስ መልእክቶች

ጳውሎስ በሮም በእስር ላይ በነበረበት ጊዜ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ለጳውሎስ ታማኝ ነበረች። በ61 ወይም በ62 ዓ.ም. ላይ ጳውሎስ ስለ እስራቱ የሚያጽናናቸውን ደብዳቤ ከእስር ቤት ሆኖ ጻፈላቸው። በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 ውስጥ ጳውሎስ ድሮ ስለ ደኅንነቱ ይታመንባቸው የነበሩትን አሮጌዎቹን ነገሮች እንደ ኪሣራ በመቍጠር አውግዟቸዋል (ፊልጵ. 3፡7)። ሕግን በመፈጸም ላይ በተመሠረተውና በራሱ ትጋት ላይ እምነት እንደሌለው ነገራቸው። ከእግዚአብሔር የሚገኘው ጽድቅ በክርስቶስ በማመን ላይ

የተመሠረተ ነው (ፊልጵ. 3፡7–9)። የጳውሎስ ፍላጎት በክርስቶስ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው፥ ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረው፥ እንዲታዘዝና እንዲያገለግለው፥ እንዲሁም የመከራው ተካፋይ እንዲሆን ነበር (ፊልጵ. 3፡10)።

60–61 ዓ.ም.

ጳውሎስ ከኤፌሶን ከሄደ ከአምስት ዓመታት በኋላ በሮም ከተማ በመኖሪያ ቤቱ የቁም እስረኛ ሆነ። ለሁለት ዓመት እንግዶቹን ያለምንም ችግር መቀበል ይችል ነበር። ከእንግዶቹ አንዱ የአብያተ ክርስቲያናቱን እንቅስቃሴ ዜና ለጳውሎስ ያመጣለት ከኤፌሶን የመጣው ኤጳፍራ ነበር። የኤፌሶን መልእክት የተጻፈው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ከተቋቋሙ በኋላ ነበር። በኤፌሶን 3 ላይ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የተሰወረው ምሥጢር መግለጫ ብሎ ይጠራታል፤ ይህ አሁን የተገለጠው ምሥጢር አይሁድም ሆኑ አሕዛብ አብረው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎች መሆናቸው ነው። ይኸውም ክርስቶስን በመቀበላቸው ምክንያት ነው (ኤፌ. 3፡10–13)። በክርስቶስ ያለው እምነት አይሁድንም አሕዛብንም ያለምንም ተከላካይ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ አስቻላቸው። ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ጸሎት ጣምራ ነበር፤ አንደኛው በመከራ ውስጥ ክርስቲያኖች በሚያልፉበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲያበረታታቸው ነበር። ሌላው ደግሞ ክርስቶስ በእምነት በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ እንዲኖር፥ ክርስቲያኖችም በእግዚአብሔር ሙላት እንዲሞሉ ነበር። እነርሱም እግዚአብሔርን ለዘለዓለም እንዲያከብሩ ያደርጋቸዋል።

ቈላስይስ ሌላው የወንጌል መከላከያ ነው። የኤፌሶን መልእክት በተጻፈበት አካባቢ የተጻፈ ሲሆን ተመሳሳይ ይዘት አለው። በቈላስይስ መልእክት ጕልቶ የሚታየው ትምህርት በክርስቶስ ያለው ቤዛነት ነው። በክርስቶስ ሰዎች ከጨለማ ኃይል ነፃ ወጥተዋል። የኃጢአት ስርየት አግኝተዋል (ቈላ. 1፡13–14)። በክርስቶስ ደም ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀዋል (ቈላ. 1፡20–22)።

ፍልስፍናና የስሕተት ትምህርት የክርስቶስን ስፍራ እንዳይይዝ ያሠጋ ነበር። ራስን በፈቃደኝነት በማስጨነቅና በማዋረድ የእግዚአብሔርን የበለጠውን እውቀት እንዲያገኙ ተስፋ ይሰጡ ነበር (ቈላ. 2፡48፥ 20–22)። መላእክትን ማምለክ (2፡18)፥ ከአንዳንድ ምግቦችና መጠጥ ራስን ማግለል፥ በዓላትን ማክበር እግዚአብሔርን ለማወቅ ይጠቅማል ይሉ ነበር (ቈላ. 2፡16–17)። ጳውሎስ ግን ክርስቶስ ከሁሉም የበላይነት እንዳለውና ከእነኚህም ነገሮች ሁሉ እንደሚበልጥ አስተማረ።

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው በተለይ ለጥቂት አይሁድ ክርስቲያኖች ነበረ። ከብሉይ ኪዳን የሥርዓት ሕግ ያለውን ግንኙነት ያብራራል። የሮሜ መልእክት አማኞች ከሥነ-ምግባር ሕግ ጋር ስላላቸው ግንኙነት ያብራራል። ይህ አሳብ ማለትም የክርስቶስን ፍጹም የበላይነት፥ ብቁነትና ከኦሪት ሕግ በላይ መሆኑን ለመቀበልና ለመያዝ ለአይሁድ ክርስቲያኖች በጣም አስቸጋሪ ነበር።

ዕብራውያን 6፡1-2 በግልጽ እንደሚያስረዳው ከሞተ ሥራ ንስሐ፥ በእግዚአብሔር እምነት፥ ጥምቀት፥ እጆችን የመጫን፥ የሙታን ትንሣኤና የዘለዓለም ፍርድ የክርስቶስ መሠረታዊ ትምህርቶች ናቸው። ብዙ ምሁራን ጳውሎስ ነው ብለው የሚናገሩለት የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፡- እነዚህ ነገሮች መሠረታዊ ቢሆኑም ወደ ፍጹምነት ማምራት እንዳለብን ይናገራል። እነዚህ የእምነታችን መሠረቶች ናቸው። ሆኖም በእምነት መቀጠል አለብን።

## ማጠቃለያ

ጽድቅ ማለት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ወይም አቋም ለውጥ ማድረግ ማለት ነው። ከነበረን በደለኛነትና ኵነኔ ነፃና ተቀባይነት ያለን መሆኑን የምናገኝበት በእግዚአብሔር ፊት ያለንን አቋም የምንለውጥበት ነው። መጽደቅ ማለት የኃጢአት ይቅርታን ማግኘትንና ከሚያስከትለውም ኵነኔና ቅጣት ነፃ መሆንን ያጠቃልላል።

ሰዎች እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የሚሰማውን ስሜት ማወቅ ያስቸግራቸዋል። እኛ ከኃጢአት ያልተለየን በመሆናችን የኃጢአት ይቅርታ ቀላል ነገር ይመስለናል! ለቅዱስ እግዚአብሔር ግን ፍጹም የተለየ ነው።

ሰው ጽድቅን ለማግኘት ሟሟላት ያለበት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ እንደሆነ ጳውሎስ በግልጽ አስተምሯል። በእግዚአብሔር የነፃ ስጦታ በጸጋ እንጂ በኦሪት ሕግ ሥራ አይደለም።

## ጥያቄዎች

1. በተሰሎንቄ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ጽድቅ በእምነት ብቻ የመሆኑን እውነተኛነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ምንድን ነው? (1ኛ ተሰ. 1፡7-8 ተመልከት።)
2. የጌታ አሳብ ለክርስቲያኖች ግልጽ የሚሆነው እንዴት ነው? (1ኛ ቆሮ. 2፡9-12 ተመልከት።)
3. የጳውሎስ ዋንኛ ፍላጎት ምን ነበር? (ፊልጵ. 3፡7-10 ተመልከት።)

4. ተደብቆ የነበረው ነገር ግን በጳውሎስ ዘመን የተከሠተው ምሥጢር ምን ነበር (ኤፌ. 3፡8-10 ተመልከት።)
5. በቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን የወንጌልን ስፍራ ለመንጠቅ የከጀለው ትምህርት ምን ነበር? (ቈላ. 2፡8፥ 18 ተመልከት።)
6. የዕብራውያን መልእክት አማኞች ከአሪት ሕግ ሥርዓት ጋር ስላላቸው ግንኙነት ያብራራል፤ የሮሜስ መልእክት የሚያብራራው የትኛውን ነው?

# ትምህርት 10

## የቤተ ክርስቲያን አመራር

የትምህርቱ ዓላማ፦ ጳውሎስ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንደመረጣቸው፥ እንዴት እንዳሠለጠናቸውና እንደመራቸው ለማጥናት ነው።

## መግቢያ

የቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ ትርጕምና አሳብ የመነጨው ከአዲስ ኪዳን ነው። ቤተ ክርስቲያን በእምነት አንድ የሆኑ ሰዎች ክርስቶስ ራስ በሆነበት አንድ አካል ሥር የተሰባሰቡባት ማኅበር ናት። ቤተ ክርስቲያን በበዓለ ኀምሳ ቀን የተጀመረች ስትሆን ፍጻሜዋ ደግሞ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስትነጠቅ ሊሆን ይችላል።

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን 120 አባላት የነበሩባት የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች (የሐዋ. 1፡15)። ቀጥሎም በበዓለ ኀምሳ ቀን የአባሎች ቍጥር በ3000 ጨመረ፤ ከዚያም በ5000 ጨመረ (የሐዋ. 4፡4)። ከዚህም ሌላ የአማኞች ቍጥር በየዕለቱ ይጨምር ነበር (የሐዋ. 2፡47)።

## 1. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተገለጠው የቤተ ክርስቲያን አመራር

በማቴዎስ 16፡16-18 ውስጥ ኢየሱስ አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያን እንደምትመሠረት ተናገረ። ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው ጴጥሮስ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በተናገረው ቃል ላይ ነው። ቤተ ክርስቲያን ያደገችው ሐዋርያት በሰጡት መሠረታዊ ትምህርት ነበር (የሐዋ. 2፡42)። ሆኖም የቤተ ክርስቲያን አባላት ቍጥር እየጨመረ በመሄዱ ሐዋርያት የመሪነትን ሥራ የሚካፈሉ ሰዎችን ፈለጉ፤ ስለዚህም ዲያቆናት ተመረጡ (የሐዋ. 6፡1-6 አንብብ)።

በኢየሩሳሌም በተነሣው ስደትና በእስጢፋኖስ መገደል ምክንያት አማኞች በስደት ተበተኑ። ከዚህም የተነሣ ጌታ እንዳዘዘው በሰማርያ ቤተ ክርስቲያናት ተቋቋሙ (የሐዋ. 1፡8)። በዚህ ስደት የጠርሴሱ ሳውል ተሳታፊ ነበር። ክርስቲያኖችን ያሳደዳቸው ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ጌታን በደማስቆ መንገድ ላይ እስካገኘው ድረስ ነበር።

የጳውሎስ ጥሪ በተለይ የአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን ነበር። በአውሮፓና በእስያ በሚዘዋወርበት ወቅት ከአማኞች መካከል የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ይመርጥ ነበር፤ የተመረጡትም ሰዎች የቤተ ክርስቲያናቸው መሪዎች ሆኑ (የሐዋ. 14፡23)።

ጳውሎስ የመጨረሻውን ጉዞ ፈጽሞ ሲመለስ ሳለ፥ ሚሊጢን ድረስ መጥተው እንዲያነጋግሩት ለኤፌሶን ሽማግሌዎች መልእክትን ላከባቸው (የሐዋ. 20፡17)።

ጳውሎስ በሚሊጢን ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሰጠው መልእክት ከፍተኛ ግምት ያለው ነው። ምክንያቱም በሐዋርያት ሥራ እንደተሰጠው ዓይነት መልእክት በቀጥታ የሚያተኩረው ለክርስቲያኖች በመሆኑ ነው። ጳውሎስ ለሚያደርገውና እንዲሁም እርሱ ወደፊት ለሚሰጋበት ጉዳይ መገለጥን ይሰጣል (ሐዋ. 20)።

## 2. የጳውሎስ መሪዎችን ማሠልጠን

ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ በተለይ የቤተ ክርስቲያን አዕማድ ተብለው የተቈጠሩ ሐዋርያት ናቸው፥ ። ይሁን እንጂ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ጳውሎስ ጴጥሮስን ገሥጸው (ገላ 2፡9)። መሪዎች አንዳንዴ ሊሳሳቱ ይችላሉ (ገላ.2)። ስለሆነም ግሣጼና እርማት ያስፈልጋቸዋል።

የጳውሎስ ተቀዳሚ ጥሪ ወንጌልን ለአሕዛብ መስበክ ነበረ። በጉዞው ወቅትም ጳውሎስ ለመሪነት የሚያበቃ ችሎታ ያላቸው አንዳንድ ወጣቶችን አገኘ። እነዚህም ወጣቶች ጳውሎስን በአገልግሎቱ ተባበሩት፤ ወዲያውም የጳውሎስ አገልግሎት ተካፋይ በመሆን፥ እርሱን በመወከል፥ መልእክቱን ለማድረስና ለማስተማር ወደ የቤተ ክርስቲያናቱ በመሄድና ችግር ላለበት ቤተ ክርስቲያን ችግሮችን በመፍታት ማገልገል ቀጠሉ። ጳውሎስ በሁለተኛው ወንጌላዊ ጉዞው ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራ ሲሄድ አግኝቶ ያሠለጠነው በአባቱ ግሪክ በእናቱ አይሁዳዊ የሆነውን ጢሞቴዎስን ነበር (የሐዋ. 16፡3፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡6፤ 4፡14)። ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ተገድዶ በወጣ ጊዜ የተሰሎንቄን ሰዎች ደኅንነት እንዲመለከት ጢሞቴዎስን ላከው።

ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቍሞ ወደ ሌላ ከሄደ በኋላ እንኳ ስለ እነርሱ ያስብ ነበር። ጳውሎስ በጕዞው አግኝቶ ካሠለጠናቸው አንዱ ቲቶ ነበር። ቲቶ ግሪክ ሲሆን፥ ምናልባትም የተለወጠው በጳውሎስ አገልግሎት ሳይሆን አይቀርም (ቲቶ 1፡4)። ቲቶ ከጳውሎስ ጋር ከመጓዙም ሌላ ጳውሎስን በመወከል ወደ ቆሮንቶስ ሄዱል። በጳውሎስና በቆሮንቶስ ሰዎች መካከል በነበረው ውዝግብ መካከለኛ ሰው በመሆን አገልግሏል (2ኛ ቆሮ. 2፡13፤7፡6፥ 13፤ 8፡6፥16፥23፤ 12፡18)። ቲቶ ከጳውሎስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (ገላ. 2፡1፥ 3)፤ ደግሞም በቀጵርስ ደሴት አገልግሎት ሰጥቷል።

በቆሮንቶስ ባሉ ምእመናን መካከል አንዱ አገልጋይ ከሌላው አገልጋይ ይበልጣል በሚል መከፋፈል ተፈጥሮ ነበር። አጵሎስና ጳውሎስ የጌታ አገልጋዮችና አብረው ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠሩ ብቻ እንደሆኑ ጳውሎስ አስታወቃቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጌታ አገልጋዮችና መጋቢዎች ናቸው። እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ስጦታ ይሰጣል፤ አገልግሎታቸው ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርገው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው (1ኛ ቆሮ. 3)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተጠሪነታቸው በሰው ልብ ውስጥ የተደበቀውን ሳይቀር ለሚመረምረውና ለሚፈርደው ለእግዚአብሔር ነው። የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የሆኑት ሐዋርያት የዓለም መቀለጃ በመሆን እንደ ሞኞች የተቆጠሩት ለክርስቶስ ሲሉ ነበር። ለሚከተሏቸውም መልካም ምሳሌ ሆኑ። ጳውሎስ «በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ» (1ኛ ቆሮ. 9፡23) አለ።

ለጳውሎስ መሪነት ማለት ራስን መካድና ለወንጌል ሲል ለሚያገለግላቸው ሰዎች አሽከር መሆን ማለት ነው። ሽልማትን ለማግኘት ትጋትና በማንኛውም መንገድ ራስን መግዛት ያስፈልጋል፤ ይህም ሯጭ ውድድሩን ለማሸነፍ በትዕግሥት እንደሚሮጥ ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 9 አንብብ)።

ጳውሎስ ራሱ ለመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ ሌሎች ለመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት በጣም ያስብ ነበር። ይጸልይላቸውና የጽሑፍ መልእክትም ይልክላቸው ነበር። ጳውሎስ ጦርነታቸው መንፈሳዊ እንደሆነና የሚዋጉበትንም መንፈሳዊ የጦር መሣሪያ እንዲታጠቁ ለቆሮንቶስ ሰዎች አስታውሷቸዋል (2ኛ ቆሮ. 10፡4–6)። የቆሮንቶስ ሰዎች አንዱን መሪ ከሌላው መሪ ጋር ከማወዳደር ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ወንጌልን ማዳረስ ይገባቸው እንደነበረ በማሰብ ይጨነቅ ነበር (2ኛ ቆሮ. 10 አንብብ)።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሆኖ ሳለ ሮም ላለችው ቤተ ክርስቲያን የጽሑፍ መልእክት ላከ። ሮሜ ምዕራፍ 16 ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሴቶችና ወንዶች ረጅም የስም ዝርዝር ጽፏል። ከእነዚህ መሪዎች ውስጥ አንዳንዶቹን የሚያውቃቸውና አብሯቸው ያገለገለ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በዝና ብቻ የሚያውቃቸው ናቸው። ሆኖም ጳውሎስ ሁሉንም ስለሚያስብላቸውና ስለሚደሰትባቸው ለሁሉም ሰላምታ ጻፈላቸው። ጳውሎስ ጭንቀቱን ሲያስረዳ «የአብያተ ክርስቲያናት አሳብ» በማለት ይጽፋል (2ኛ ቆሮ. 11፡28)።

## 3. የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት

የጳውሎስ ቅርብና የታወቁ ረዳቶች ጢሞቴዎስና ቲቶ የአብያተ ክርስቲያናትን ኃላፊነት የያዙ  መሪዎች ሆኑ። ጳውሎስ በሁለቱ እስራቶቹ መካከል ወደ ኤፌሶን ሄዶ ነበር። በሐዋ. 20፡23 ውስጥ ጳውሎስ ተጠንቀቋቸው ብሎ ያላቸው የሐሰት ትምህርት አስፋፊዎች በዚህ ወቅት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሳይገቡ አልቀሩም። በእነርሱም ምክንያት ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በኤፌሶንና በእስያ የበላይ አድርጎ ትቶት ሄደ። ከዚያም በኋላ ጳውሎስ በትክክለኛ ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ሰዎችን እንዴት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት አድርጎ መምረጥ እንደሚገባውና ጤናማ ትምህርት እንዲያስተምር ደብዳቤውን ለጢሞቴዎስ ጻፈለት (1ኛ ጢሞ. 3 አንብብ)።

ጳውሎስ ከመጀመሪያ የሮም እሥራቱ ከተፈታ በኋላ ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በመጓዝ ቀርጤስ ደሴት ላይ እንደቀረ ግልጽ ነው (ቲቶ 1፡5)። ጳውሎስ ለቲቶ የጻፈው መልእክት ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከተሰጡት ትምህርቶች አንዱ ነው። (የቲቶን መልእክት በተለይም ምዕራፍ አንድን አንብቡ)።

(በግምት የዕብራውያንን መልእክት ጽፎአል የሚባለው)፥ ጳውሎስ የዕብራውያንን ሰዎች በአዲስ ትምህርቶች ሳይወሰዱ መሪዎቻቸውን እንዲያስቡና እረኛቸውንም እንዲከተሉ አስጠንቀቃቸው (ዕብ. 13፡7–9)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የምእመናኖቻቸውን መንፈሳዊ ደኅንነትን በመንከባከብ ምእመናኑ በደስታ እንዲታዘዟቸውና እንዲተማመኑባቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## ማጠቃለያ

1. ቤተ ክርስቲያን በመለኮታዊ ዕቅድ የታቀደችና የተቀናጀች፥ ክርስቶስ የበላይ ራስ የሆነባት ማኅበር ናት።

2. ቤተ ክርስቲያን መዋቅርና ሥርዓት አላት።

3. «የወላጆች» ወይም «የወንድሞችና የእኅቶች» ተግባር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሰፊውና ግልጥ በሆነ መንገድ ተገልጿል።

4. በራሳቸው ቤት ውስጥ ብቻ ከመሰብሰብ በቀር ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ግንኙነት ስለሌላቸው ቤተሰቦች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምንም የተጻፈ ነገር የለም።

### ጥያቄዎች

1. ጴጥሮስ «ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ በተናገረው ቃል ላይ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተጀመረች አብራራ። የሐዋ. 2፡14–42፤ ማቴ. 16፡16–18 አንብብ።

2. በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጳውሎስ ለአማኞች ብቸኛ መልእክት የሰጠው ለእነማን ነበር? የሐዋ. 20፡17–35።

3. ምናልባትም የጳውሎስ ትልቁ ሸክም ምን ነበር? 2ኛ ቆሮ. 11፡28 ተመልከት።

4. ለሽማግሌነትና ለዲያቆንነት የሚያበቁትን መመዘኛ ነጥቦች በዝርዝር ጻፍ። (1ኛ ጢሞ. 3፤ ቲቶ 1 ተመልከት።)

# ትምህርት 11

## ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ማንነት ያቀረበው ትምህርት

የትምህርቱ ዓላማ፦ ጳውሎስ በስብከቱና በጽሑፍ መልእክቱ ውስጥ ክርስቶስን እንዴት እንዳቀረበው ለማጥናት ነው።

### መግቢያ

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ክርስቶስን የገለጹት ሊሠራው በመጣው ሥራና ለመፈጸም በመጣው የኃላፊነት ተግባሩ አንፃር ነው። የክርስቶስ ሥራና ኃላፊነት ከአሪት ሕግና ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈጸም ጋር የተያያዘ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለክርስቶስ ብዙ የማዕረግ ስሞች ተሰጥቶታል። ኢየሱስ ራሱን ለማመልከት «የሰው ልጅ» ብሎ ጠርቶታል። ከሰማይ በመጣው ድምፅ አማካይነት በጥምቀቱ ጊዜና በተራራ ላይ በተለወጠ ጊዜ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል (ማር. 1፡11፤ 9፡7)። ቀጥሎም አጋንንት «የእግዚአብሔር ልጅ» ብሎ ጠርቶታል (ማር. 5፡7)። ጴጥሮስ ኢየሱስ «የእግዚአብሔር ልጅ» መሆኑን አውቋል (ማቴ. 16፡16)። ጳውሎስም ብዙ ጊዜ «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን ስም ቢጠቀምም አዘውትሮ የሚጠቀመው «ጌታ» ወይም «ክርስቶስ» በማለት ነው፥

ይህም መሢሑን ለማመልከት በብሉይ ኪዳን የተጠቀመበትን ቃል የሚተረጕም ነው።

ጳውሎስ በሚሰጠው ትምህርት ውስጥ የክርስቶስ ሥራ በተለይ የቀረበው ከኦሪት ሕግ አንጻር ነው። «ራሱን ከሕግ በታች» አድርጎ በመምጣት ክርስቶስ እርግማንንና ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ በራሱ ላይ ተሸከመ። እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን እርሱ ስለ እኛ ኃጢአት ሆነ (ገላ. 3፡13፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)።

## 1. የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ ውስጥ ነው

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሆኖ ረጅም ለሆነው ለሮም ጕዞ ዝግጅት ለማድረግ የእምነቱ መግለጫ የሆነውን መልእክት ጻፈላቸው። ጳውሎስ ማንም ሰው በኦሪት ሕግ ሥራ እንደማይጸድቅ ገለጸላቸው። አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል። የጸጋ ስጦታ በመቀበል ሁሉም ጻድቃን ሆነዋል። ይኸውም በክርስቶስ በመዋጀት ነው። የሰው ልጆች ኃጢአት ዋጋ የተከፈለው በፈሰሰው በክርስቶስ ደም ነው። ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሊጸድቅ የሚችለው በክርስቶስ በማመን ብቻ ነው (ሮሜ 3)።

ክርስቶስ እንደተቀበረና ከሞት እንደተነሣ፥ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ በክርስቶስ ውስጥ ተቀብረናል፤ ዳግመኛ የኃጢአት ባሮች እንዳንሆን አሮጌው የኃጢአት ሕይወታችንን ያስተካክልልናል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ከእርሱም ጋር ያለንን ኅብረት ያስተካክልልናል። ክርስቶስ አንድ ጊዜ ስለ ሁሉም ሞቷል። አዲስም ሕይወት ሰጥቶናል፤ ከኃጢአት ቀንበር ነፃ አድርጎናል፤ የዘላለምንም ሕይወት ሰጥቶናል። የክርስቶስ ኃይል ለእርሱ የተለየን አድርጎናል፤ ቀድሶናል፤ ይኸውም አዲሱን የጽድቅ ሕይወት በእርሱ በማመን እንድንኖር ነው (ሮሜ 6)።

## 2. ጳውሎስ ለአግሪጳ ክርስቶስን እንዴት አድርጎ እንዳቀረበለት

ጳውሎስ በቂሣርያ ሁለት ዓመት ሙሉ ከታሰረ በኋላ በአዲሱ አስተዳዳሪ በፊስጦስ አማካኝነት ወደ አግሪጳ እንዲቀርብ ተደረገ። ጳውሎስም እግዚአብሔር ለጻድቃንና ለኃጢአተኞች የሙታን ትንሣኤ እንደሚኖር ለአባቶቻችን የገባውን ቃል ኪዳን ተስፋ በማድረጉ በአይሁዶች እንደተወነጀለ ለአግሪጳ መሰከረለት (የሐዋ. 24፡15፤ 26፡6–8፤ 28፡20)።

በደማስቆ መንገድ ላይ ለሳውል ተገልጦ ለነገሥታት፥ ለአይሁድና በተለይም ለአሕዛብ እንዲመሰክርና እንዲያገለግለው የጠራው፥ እግዚአብሔር ከሞት ያስነሣው፥ ኢየሱስ ነበር (የሐዋ. 9፥15)።

ጳውሎስ ለአግሪጳ ሲናገር የሚሰብከው ሌላ ነገር ሳይሆን ሙሴና ነቢያት ስለ መሢሑ ሞትና ትንሣኤ ሊሆን ያለውን አስቀድመው የተናገሩትን ብቻ እንደሆነና ክርስቶስም እነርሱ የተናገሩለት መሢሑ መሆኑን ገለጸ። ከሞት በመነሣት የመጀመሪያው ክርስቶስ እደሆነና ለአይሁድና ለአሕዛብ ብርሃንን እንዳወጀ ይህንን የክርስቶስን አዋጅ ለማሰራጨት ራሱ ጳውሎስም እንደተጠራ ተናገረ።

ፊስጦስ ጳውሎስን አብደሃል ብሎታል። ንጉሥ አግሪጳ በጳውሎስ ላይ በፌዝ መልክ ክርስቲያን ሊያደርገው በመሞከር ላይ እንደሆነ ጠየቀው። (የሐዋ. 26ን አንብብ።)

## 3. አሕዛብና አይሁድን ለማዋሐድ ክርስቶስ አስታራቂ መንገድ ነው

ጳውሎስ የኤፌሶን መልእክት በሮም እስር ላይ እያለ ከጻፋቸው መልእክቶች አንዱ ነው። መከራና ስደት ጳውሎስን በመንፈሳዊ ሕይወቱ አጐልምሶታል፤ እንዲሁም ስለ ክርስቶስ ሰፊና ጥልቅ እውቀት እንዲያገኝ ረድቶታል። ይህንንም ልምምዱን ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈላቸው መልእክቱ አካፍሏቸዋል። እግዚአብሔር በክርስቶስ እምነት ያላቸውን ሁሉ በፍቅሩ፥ በምሕረቱና በጸጋው ሕያዋን አድርጎአቸዋል። ክርስቶስ የምእመናን ሰላም ሆነ፤ በመስቀሉም አይሁዶችንና አሕዛብን አንድ አካል አደረጋቸው፤ ከእግዚአብሔርም ጋር አስታረቃቸው። ሁለቱም ወገኖች በአንድ መንፈስ በእግዚአብሔር ፊት የመቅረብ ሞገስ አገኙ፤ የአንዲት አገር ዜጎችም ሆኑ፤ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባሎችም ሆኑ።

እምነት በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተመሠረተ፤ የመሠረቱ ድንጋይም ክርስቶስ ነው። ሁሉም በክርስቶስ የጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ተሰባሰቡ (ኤፌ 2.)።

## 4. የክርስቶስ አካል

አይሁድና አሕዛብ አንድ ሕዝብ እንዲሆኑና ክርስቶስም የእነርሱ ራስ እንዲሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። ይህም መታወቅ የጀመረው ጳውሎስ ለአሕዛብ በሰጠው አገልግሎት ነው። የእግዚአብሔር ዕቅድ ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን

በውስጣቸው ያኖረላቸውና በመንፈስ ለመጕልመስ ኃላፊነት የሚሰማቸው ግለሰቦች ቤተ ክርስቲያን ሆነው እንዲሠሩ ነው።

አማንያንን ሁሉ ወደ አንድ አካል የሚያሰባስበው በክርስቶስ ያለው አንድነት ነው። ሆኖም እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይህንን አንድነት ከሌሎች ጋር በስምምነት የማጠናከር ኃላፊነት አለበት። ይህንን በክርስቶስ ያለውን አንድነት የመጠበቅ ሥራ የቤተ ክርስቲያን ነው። በአካሉ ውስጥ ያሉት በእምነት እንዲጸኑና እንዲበስሉ መንፈስ ቅዱስ ለአካሉ ብልቶች ሁሉ ስጦታዎችን ይሰጣቸዋል። (ኤፌ. 4ን አንብብ።)

## 5. የአማንያን በክርስቶስ ውስጥ መመላለስ

ክርስቶስን የእነርሱ ራስ ሆኖ አይሁዶችና አሕዛብን አንድ ያደረጋቸውን፥ የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ ጳውሎስ ቀደም ሲል አብራርቶታል። አሁንም ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ያላት ጥሪ ምን እንደሆነ ይገልጻል (ኤፌ. 4፡1–16)። ምእመናን በክርስቶስ አንድ ናቸው፤ እንዲሁም ሕያው በሆነው በክርስቶስ የሚያድጉና የእርሱንም ሕይወት በመከተል ለሌሎች ምሳሌ የመሆን ኃላፊነት ያለባቸው ሕያዋን ግለሰቦች ናቸው (ሮሜ 8፡29፤ ፊልጵ. 3፡21)።

ጳውሎስ የክርስቲያን ኑሮን ለመቈጣጠር የሚጠቅሙ አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጥቷል።

1. ክርስቲያኖች አእምሮአቸውን መቈጣጠር አለባቸው፤ ምክንያቱም አእምሮአቸውን ለእግዚአብሔር አናስገዛም ማለታቸው የልብ ደንዳናነትንና እግዚአብሔርን ያለማዳመጥ ያስከትልባቸዋል። ይህም ክርስቲያኖችን ከእግዚአብሔር ኅብረት ውጭ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

2. ክርስቲያን አሮጌውን አኗኗሩንና ተፈጥሮውን እንደ አሮጌ ልብስ ማውለቅ አለበት። ይህም ያለማቋረጥ መፈጸም ያለበት የአእምሮ ተሐድሶ ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው ሥራ ነው።

በክርስቶስ የሚገኘው አዲስ ልደትና በመንፈስ ቅዱስ የሚደረገው ቍጥጥር በኃጢአት የተበላሸውን በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔር ምስል ከፈጣሪያችን ጋር ያለን ኅበረትና አንድነት ያድሰዋል። ከዚያም በኋላ መመሪያ በተግባር የሚተረጐምበትን ዝርዝር ሁኔታ ጳውሎስ ሰጥቶአል (ኤፌ. 4፡25–32፤ ኤፌ. ምዕራፍ 4ን በጥንቃቄ አንብቡ)።

## 6. ጥበብና እውቀት ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ነው

የቈላስይስና የኤፌሶን መልእክቶች በተመሳሳይ ጊዜያት እስር ቤት የተጻፉ ናቸው። ሁለቱም መልእክቶች በትንሹ እስያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ሳይነበቡ አልቀሩም። ጳውሎስ በተደጋጋሚ በሥጋው መለኮትን በሙላት የገለጸውን ክርስቶስን የእግዚአብሔር ምሥጢር ብሎ ይጠራዋል። የቈላስይስ ሰዎች በማታለልና በማባበል ቃል በሚጠቀሙ ሰዎች እንዳይጠመዱ ጳውሎስ አስጠንቀቃቸው። በቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስሕተት የገባው በሐሰት ልምምድ ሳይሆን በሐሰት ትምህርት አማካይነት ነበር።

በእምነት ሕይወት ውስጥ ክርስቶስን መቀበል ተቀዳሚ ተግባር ነው፤ ሆኖም የሚከተሉትን አራት የእምነት ደረጃዎች መጀመሪያ ብቻ ነው፡—

1. በክርስቶስ መመሥረት፥
2. በክርስቶስ ላይ መታነጽ፥
3. በክርስቶስ ውስጥ መጽናት እና፥
4. በምስጋና መሞላት ናቸው (ቈላ. 1፡21—23)።

የሐሰት ትምህርት የጀመረው በማታለያ ቃላት፥ በፍልስፍናና በሰዎች ባህል ምናልባትም በአይሁድ ባህል ሊሆን ይችላል። እነኝህ የሐሰት ትምህርቶች ምንም እንኳ ከምሁራን የወጡ ንግግሮች ቢመስሉም ከበለጸገውና በክርስቶስ ካለው እውቀት ጋር ሲወዳደሩ ፍጹም ባዶ ቃላት ነበሩ። የዓለም እውቀት ሁሉ መለኮታዊውን መገለጥ ለመተካት የማይችል ደካማ ነው (ቈላ. 2፡8)።

## 7. የመለኮት ሙላት በክርስቶስ ውስጥ አለ

ሁሉንም የሚያጠቃልል ክርስቶስ ነው። ከእርሱ የማይገኘው ነገር ምን ይሆን? በክርስቶስ የደኅንነት ሙላት አለ። የገዢዎችና የባለሥልጣኖች ሁሉ የበላይ ራስ ነው። በክርስቶስ መገረዝ አለ፥ ይኸውም አርጌውን ተፈጥሮ ወይም የግል ፈቃዱን አውልቆ በክርስቶስ ያለውን አዲስ ሕይወት የሚያላብስ ዓይነት መገረዝ ነው። እርሱ በሞትና በትንሣኤው ይቅርታን ሰጥቷል። ጥምቀት አማንያን ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ምሳሌ ነው። መጠጥን፥ መብልንና በዓላትን በሚመለከት ያሉትን የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ሁሉ ክርስቶስ ፈጽሟቸዋል ወይም አሟልቷቸዋል፤ ምክንያቱም እነዚህ ሥርዓቶች ክርስቶስ መጥቶ ለሚፈጽማቸው ተግባሮች ጥላ ብቻ ነበሩ። (ቈላ. 2፡9—17 ያለውን አንብብ።)

## 8. የአካል ራስ ክርስቶስ ነው

የቈላስይስ ሰዎች መላእክትን በማመንና ራሳቸውን ማጕሳቈልን በሚያስተምረው ፍልስፍና ተሳታፊዎች ሆነው ነበር። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱን ፍልስፍና የሚያዘወትሩ ሰዎች ራስና ብቸኛ አስታራቂ ለሆነው ለክርስቶስ የማይታዘዙ እንደሆኑ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። አካል በራስ መታዘዙን የሚያመለክተው አንዱ ምልክት የአካሉ አባላት በሙሉ ለራስ መታዘዛቸው ነው። እንግዲህ እነዚህ ከክርስቶስ ጋር የሞቱ ከዓለም ያልሆኑ ክርስቲያኖች ለምን ለዓለም ሥርዓት ይገዛሉ? ይህን የመሰለው አስተሳሰብ ጥበብን ያዘለ ይመስላል፤ ሆኖም የሥጋን ፍላጎት ሊቈጣጠር አይችልም (ቈላ. 2፡18–23)።

## 9. ክርስቶስ ለአዲሱና ለዘለዓለማዊ ሥርዓት ሊቀ ካህን ነው

ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሊቀ ካህን ነው። ለሥራውና ለማዕረጉ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም መመዘኛ ያሟላል። በሥጋዊ ሕይወታቸው ለሚጕሳቈሉ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ይራራላቸዋል፤ ምክንያቱም ራሱ ሰው ሆኖ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራስን ማስገዛት በሚገባ ስለተማረ ነው። እጅግ የላቀ ሥቃይን ተቀብሏል፤ ተዋርዷልም። የሞትንም ኃይል ፊት ለፊት ተቋቍሟል፤ በዚህም መንገድ በሥጋ ሕይወቱ ፍጹም ሆነ። ይህ ነገር ሰውን የመዋጀት ተግባሩን ለማከናወን ብቁ አደረገው። ከዚህም ሌላ በአዲሱና ዘለዓለማዊ በሆነው ሥርዓት መሠረት ለእርሱ የሚገባውን የሊቀ ካህንነት ሥልጣን እንዲቀበል ያስችለዋል (ዕብ. 5)።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከጼዴቅ «ሊቀ ካህን ነው» (ዘፍጥ. 14፡17–20)። ይህ ክህነት ከሌዋውያን ክህነት የበላይነት አለው። ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር የመግባት ዕድልና የተሟላ ደኅንነት አከናውኖአል (ዕብ. 7፡19፥25)። የመልከጼዴቅና የክርስቶስ ክህነት በጊዜ የማይወሰኑ ናቸው። የክርስቶስና የመልከጼዴቅ ክህነት ፍጹምነትን ያመጣሉ። አዲስና የተሻለ ሥርዓት በክርስቶስ ተመሠረተ። ክርስቶስ ኃጢአትና ነቀፋ የሌለበት ስለሆነ ወደ እርሱ የሚመጡትን ለዘለዓለም ሊያድናቸውና ሊያማልዳቸው ይችላል። (ዕብ. 7፡1–8፡6 አንብብ።)

## 10. ክርስቶስ የተሻለው ኪዳን አማላጅ ነው

በኤርምያስ 31፡31–34 ለእስራኤልና ለይሁዳ የተሰጠው የአዲስና የተሻለ ቃል ኪዳን አማላጅ በሆነው በክርስቶስ ተሟልቶ ተፈጽሟል (ዕብ. 8፡6)።

የእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ የተወሰኑ ሰዎች ከዓለም በመለየት ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ነው። ይህን ኪዳን ያከናወነው የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቅ ደስ የሚያሰኛቸውን መንፈስ በውስጣቸው ያስቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በመግባት ብቸኛ አማላጅ ሆነ። አሮጌው ኪዳን አለፈ፤ ክርስቶስ መካከለኛ አማላጅ የሆነበት አዲሱና ዘለዓለማዊ ኪዳን ስፍራውን ያዘ (ዕብ. 8)።

## ማጠቃለያ

የጳውሎስ መልእክት ዐቢይ ትምህርት እግዚአብሔር በክርስቶስና በሥራው አማካኝነት ለሰዎች ደኅንነት ያወጣው ዕቅድ ነበረ።

ጳውሎስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት አጠንክሮ የገለጸው ከኃጢአት ንስሐ መግባትንና በክርስቶስ ማመንን የሚመለከት ነበር። በሦስተኛው ጉዞው ወቅት ለሮሜ ሰዎች በጻፈው የእምነት መግለጫው ውስጥ በክርስቶስ ያለው እምነት የሕግ ሥራ ሳይጨመርበት መሆኑን አጠንክሮ ገለጸ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት ለተቀበሉት ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ተናገረ (ሮሜ. 3፥22)።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጳውሎስ በቂሣርያ በታሰረበት ወቅት በንጉሥ አግሪጳ ፊት ስለተናገረው መልእክት መከላከያ አሳብ እንዲሰጥ ተጠየቀ። በዚያን ጊዜ አጥብቆ የተናገረው ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ነበር። ጳውሎስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን እንደሚያውቅ፥ በደማስቆ መንገድ ላይ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን እንዳየ፤ መሢሑ ራሱ ኢየሱስ እንደሆነና እርሱም የብሉይ ኪዳንን ነቢያት ትንቢትን ሁሉ እንዳሟላ ተናገረ (የሐዋ. 26)።

ጳውሎስ በዕድሜው ፍጻሜ አካባቢም፥ በሮም በእስር ላይ እያለ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች መልእክት ጻፈላቸው። በሚያምኑት ውስጥ የተጻፈውን የክርስቶስን የደኅንነት ሥራ በድጋሚ አስታወሳቸው። ከዚያም በመቀጠል አማኞች ባመኑ ጊዜ የጀመሩትና እስከ ዘለዓለም ድረስ የሚቀጥል አዲስ የአኗኗር መንገድ ይገልጽላቸዋል (ኤፌ. 2፥5–8)። ይህም አዲስ ሕይወት የተፈጸመው በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ ነው። አማኝ በአዲስ የሕይወት ዕቅድ እንዲኖርና የክርስቶስ ሕይወት ተካፋይ እንዲሆን መንፈሳዊ ትንሣኤ አግኝቷል (ኤፌ. 2፥10፤ 1ኛ ቆሮ. 6፥17)።

ለቈላስይስ ክርስቲያኖችም የተጻፈው መልእክት ከሮም እስር ቤት ነበር። መልእክቱም ጥልቅ በሆነና በተሟላ ሁኔታ የክርስቶስን ማንነትና ክርስቶስ ለሰዎች ሲል ያደረገውን ይገልጻል፤ ቀጥሎም

ጳውሎስ የመለኮት ሙላት በክርስቶስ አካል ውስጥ እንደኖረ አስተምሯቸዋል። የጥበብና የእውቀት መዛግብት ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ናቸው፤ እርሱ ከባለሥልጣናትና ከነገሥታት ሁሉ በላይ ነው፤ የአካሉም ማለትም የቤተ ክርስቲያንም ራስ ነው (ቈላ. ምዕራፍ 2)።

ለዕብራውያን ክርስቲያኖች የተጻፈው መልእክት ክርስቶስ በሁሉ ላይ የበላይነትና ብልጫ እንዳለው ይገልጻል፤ ኢየሱስ ታላቅ ካህን፥ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ገብቶ የሚያስታርቅ ብቸኛ አማላጅ መሆኑን ያብራራል። ስለ አዲሲቱና ስለ ተሻለችይቱ ኪዳን አማላጅ እንዲሆን እግዚአብሔር ለእስራኤልና ለአይሁዶች እንደሚልክላቸው የገባው ቃል ኪዳን ክርስቶስ ነው። ይህ አዲስ ኪዳን ለእያንዳንዱ አማኝ በግሉ የጌታ መገለጥ እንዲኖረው ያደርጋል፤ በግሉ የኃጢአትን ስርየት ይሰጠዋል፤ ለእስራኤል የተገባውንም የተስፋ ቃል ወራሽ ያደርገዋል።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ለኢየሱስ የሚሰጠው የማዕረግ ስም ምንድን ነው? መግቢያውን ተመልከት።
2. የጳውሎስ መልእክቶች ዋና ፍሬ ነገር ምን ነበረ?
3. እግዚአብሔር አይሁድንና አሕዛብን አንድ ለማድረግ የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበር?
4. እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ውስጥ ሊፈጽም ያቀደው የመጨረሻው ዕቅዱ ምንድን ነው? ሮሜ 8፡29፤ ፊልጵ. 3፡21።
5. እግዚአብሔር ለእኛ ወዳለው የመጨረሻ ዕቅድ የሚያደርሱን ሦስቱ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው? ቈላ. 2፡22–23።
6. ክርስቶስ የእኛ ታላቁ ሊቀ ካህን እንዲሆን ያደረጉት መመዘኛዎች ምን ምን ናቸው? ዕብራውያን 5 ተመልከት።
7. በነቢዩ ኤርምያስ በኩል ለእስራኤል የተሰጠው የአዲሱ ኪዳን ተስፋ ቃል ምንድን ነው? ኤርምያስ 31፡31–34 ተመልከት።

# ትምህርት 12

## የኦሪት ሕግና ብሉይ ኪዳን

የትምህርቱ ዓላማ፡– አይሁዶች የአሮጌውን የሕግ ቃል ኪዳን ለአዲሱ የጸጋ ቃል ኪዳን አሳልፈው ለመስጠት የነበረባቸውን ጭንቀት ለመረዳት እንድንችል ነው።

## መግቢያ

አሮጌው ቃል ኪዳን በአዲሱ መተካቱን ጳውሎስ የተረዳው መቼ ነበር? መቼ እንደተረዳ አልገለጠልንም። ምናልባትም ኢየሱስ በመጨረሻው እራት ላይ ከተናገረው ቃል ይሆናል። ኪዳኑ ከተለወጠ ሕግም እንደሚለወጥ ያውቃል። የኦሪት ሕግ መሻር ለአይሁዶች ነገሩን ማመን እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ የሚያደርስ ታላቅ ድንጋጤ ፈጠረባቸው። በብሉይ ኪዳን ዘመን የኦሪት ሕግ በቃል ኪዳን ክልል ውስጥ ነበር! ሆኖም በአዲስ ኪዳን ዘመን አይሁዶች ስለ ሕግ አስፈላጊነት ያላቸው ትርጉም የተሳሳተ ነበር። የኦሪትን ሕግ በመጠበቃቸው በኪዳኑ ውስጥ ተገቢ ቦታ እንደሰጣቸው አድርገው ያስቡ ነበር። ክርስቲያኖች «ያ ሕግ አሁን ዋጋ የለውም» ብለው ሲነግሯቸው እንደ ስድብ ሆኖ ሳይሰማቸው አልቀረም። ጳውሎስ ይህን ነገር መስበኩ በእውነት የሚያስደንቅ ነው።

### 1. የኦሪት ሕግና ብሉይ ኪዳን በሐዋርያት ሥራ

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 መሠረት ከክርስቶስ ዕርገት ጥቂት ዓመታት በኋላ እስጢፋኖስ የሰጠው መልእክት ክርስቲያኖች ስለ ብሉይ ኪዳን የነበራቸውን አመለካከት ያሳያል። እነዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ ከአይሁድ ወገን ያመኑ መሆናቸውን አስታውስ። እስጢፋኖስ ሁለት አስፈላጊ ነጥቦችን አቀረበላቸው፦

ሀ/ እግዚአብሔር ከተስፋይቱ ምድር ውጭ ለሕዝቡ መታየቱና

ለ/ የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቡ መገለጡን።

ጳውሎስ በታናሹ እስያ ባደረገው በመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞው ላይ ማለት ከ47–48 ዓ.ም ለአይሁዶች ወንጌልን አስረዳቸው። እንዴት እንዳስተማረ ለመረዳት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13ን በጥንቃቄ አንብብ። ውጤቱ ምን ነበር? ከኢየሩሳሌም የሆኑ ጥቂት ከአይሁድ ወገን ያመኑ ክርስቲያኖች ክርስቲያን የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለበት ብለው አቋም ያዙ። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ውስጥ የተገለጸው የኢየሩሳሌም ጉባኤ በ49 ዓ.ም. ተሰበሰበ። ውጤቱ ምን ነበር? የጉባኤው ተሳታፊዎች በሁለት ነገሮች ተስማሙ፦

ሀ/ ክርስቲያኖች ከአይሁድ ወገን ላመኑት ሰዎች መሰናክያ እንዳይሆኑባቸውና

ለ/ አማኞች የሙሴን ሥርዓት እንዲጠብቁ የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ እንዳያስገድድ ወሰኑ።

ጳውሎስ በማንኛውም የጽሑፍ መልእክቱ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15ትን ሲጠቅስ አልታየም። ከ12 ዓመት በኋላ ማለት በ61 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ሆኖ እንደገና ለአይሁዶች አቋሙን አብራራላቸው። (የሐዋ. 23ን አንብብ።) አይሁዶች ክርስቲያን እንዲሆኑ ብሉይ ኪዳን መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግላቸዋል።

## 2. የጳውሎስ የመጀመሪያ ትንተና

ጳውሎስ በ47–48 ዓ.ም. በትንሹ እስያ ካደረገው የመጀመሪያው የስብከት ጉዞና በ49 ዓ.ም. ከተሰበሰበው ከኢየሩሳሌም ጉባኤ በፊት በገላትያ ክፍለ ሃገር ለሚገኙት አዲስ አማንያን መልእክት ጻፈላቸው። ለአማኞች ግልጽና የማያሻማ ምርጫ አቀረበላቸው፤ ክርስቶስን ወይም የሙሴን ሕግ መምረጥ ነበረባቸው! ጉድ ነው! ይህ ለአይሁዶች በጣም አስደንጋጭ ነበረ። የሙሴ ኦሪት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ቃል አይደለምን? እያንዳንዱ ነጥብና ጭረት መለኮታዊ ሥልጣን የላትምን? (ማቴ. 5፡18–19)። ጳውሎስ ወደ ሁለቱ ኪዳኖች በማስመልከት ለጥያቄያቸው መልስ ሰጠ።

ጳውሎስ ሁለቱን ኪዳኖች ለመግለጽ የአብርሃምን ሁለት ሚስቶች ሁለቱን ኪዳኖች እንደሚወክሉ አድርጎ በምሳሌያዊ መግለጫ ተጠቀመበት። አጋር የኦሪትን ሕግ ስትወክል፥ ሣራ ደግሞ ጸጋን ትወክላለች። እንደ ይስሐቅ ክርስቲያኖች የተስፋ ልጆች ናቸው እንጂ የሕግ ልጆች አይደሉም። ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር የመቆማቸው ሁኔታ በዘራቸው ወይም በወገናቸው ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን በጸጋው ኪዳን ላይ ነው። የሕግ ልጆች የጸጋውን ልጅ እንዳሬዙበት ሁሉ፥ አሁንም የሕግ ተገዥዎች የጸጋን ልጆች ቢያሳድዱ የሚያስደንቅ አይደለም (ገላ. 4፡19–31)።

## 3. የጳውሎስ ሰፋ ያለ ትንተና

ጳውሎስ በሮም አድርጎ ወደ እስፓኝ ለመሄድ ተስፋ ስላደረገ ለጉዞው የሚያስፈልገው ሁሉ እንዲሟላለት በ56 ዓ.ም. ሮም ላለችው ቤተ ክርስቲያን መልእክት ጻፈ፤ እርሱም በመጨረሻ ሮም የደረሰው መልእክቱን ከጻፈ ከአምስት ዓመት ገደማ በኋላ ነበር። ይህንን ደብዳቤ በጻፈበት ወቅት ጌታን ከተቀበለ ሃያ ዓመታት ሆኖታል፤ ነገር ግን «ደኅንነት በሕግ ሥራ» የሚለው ርእስ ልክ እንደ አዲስ ሞቅ ያለ ክርክር ነበር። ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 1 ና 2 ውስጥ በሙሴ ኦሪት መመርኮዝ ኩነኔን ብቻ እንደሚያስከትል ተናገረ። እስጢፋኖስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 ውስጥ እንዳደረገው ሁሉ ጳውሎስም የአብርሃምን ዘመን ጠቂመ። አብርሃም እንዴት በእግዚአብሔር ዘንድ

ተቀባይነት አገኘ? በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ የሙሴን ኦሪት ሥርዓት በመጠበቅ አልነበረም። (ሮሜ ምዕራፍ 4ን በሙሉ አንብቡ።) ስለዚህ አይሁዶች በሙሉ የተተውት ከጸጋ ይልቅ የሙሴን ኦሪት ስለሚጠብቁ ነውን? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ በሮሜ ምዕራፍ 9 ውስጥ ይመልሰዋል። ከመጀመሪያውም ቢሆን ከአይሁዶች መካከል የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሆኑት ሁሉም ሳይሆኑ የተወሰኑ ብቻ ነበሩ፤ የቀሩት ግን ታዛቢዎች ነበሩ።

## 4. በመጨረሻው ያቀረበው ትንተና

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው በሮም ለሚገኙና ከስደት ለማምለጥ ብለው ወደ ምኵራብ ሥርዓት የመመለስ ፍላጎት ኖሮአቸው ለሚያወላውሉ ክርስቲያኖች ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በጣም የቀረበ ግንኙነት ነበረው። ጳውሎስ ከመጀመሪያው የሮም እስራቱ በኋላ ወደ ግሪክና ወደ ታናሹ እስያ ዳግመኛ ሄደ። ስለእነዚህ ክርስቲያኖች መናወጥም ሰማ። ተከታታይና ልዩ የሆነ ትምህርት ጻፈላቸው። ክርስቶስ እንደ መልከጼዴቅ ካህን ነበር፥ ይህም ማለት የሌዋውያን ክህነትን ሽሮአል ማለት ነው። እንግዲህ ክህነቱ ከተለወጠ ክርስቶስ በመጣበት ልዩ ተልእኮ ምክንያት ሕግም ደግሞ መለወጥ አለበት። (ዕብራውያን ምዕራፍ 2ን አንብብ።) ይህ ብቻ አይደለም፤ ክርስቶስ የላቀ የበላይነትም አለው። (ዕብራውያን ምዕራፍ 3ን አንብብ።) የሙሴ ኦሪት በሙሉ ወደ ክርስቶስ የሚያመለክት ብቻ ነበረ፤ ስለሆነም ሕግ አሁን የሚፈጽመው ሌላ የቀረ ነገር የለውም። በዚህም ምክንያት የሙሴ ሕግ ሥርዓት በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚፈጽመው አንዳችም ነገር የለም። በተሻለ ነገር ተተክቷል። (ዕብራውያን ምዕራፍ 10ን አንብብ።) ክርስቲያኖች በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ተመልሰው ዝቅተኛ በሆነው በማይጠቅም ነገር ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም።

## ማጠቃለያ

ጳውሎስ ከራሱ ልምድ የሙሴ ሕግ ሥርዓት እምነትና ሰላምን እንደማያመጣ ያውቅ ነበር። ጳውሎስ በኢየሱስ ትምህርት መሠረት የብሉይ ኪዳን ዘመን እንዳለፈ ተረዳ (ማር. 2፡18-22)።

ይሁን እንጂ ይህ ትምህርት በማንኛውም አቅጣጫ የብሉይ ኪዳንን ሥልጣን አይነካም። ይኸውም ብሉይ ኪዳን የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ነው (ሮሜ 3፡3)። ሆኖም የአሮጌው ኪዳን ክፍል እንጂ ከአዲሱ ኪዳን ጋር ግንኙነት የለውም።

## ጥያቄዎች

1. አይሁዶች የኦሪትን ሕግ በተሳሳተ መንገድ ሊተረጉሙት የቻሉት እንዴት ነበር? መግቢያውን ተመልከቱ።
2. በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ የተወሰኑት ሁለት ዋና ዋና ውሳኔዎች ምን ምን ናቸው? (የሐዋ. 15)።
3. አብርሃም በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ተቀባይነትን አገኘ? (ሮሜ 4፡13)
4. በሮሜ 9፡31–32 መሠረት የእስራኤልን አቋም ግለጽ።
5. የኦሪት ሕግ የሚያመለክተው ወደ ማን ነው? የበላይ የሆነውስ እንዴት ነው? (ዕብራውያን 10፡9–18 ተመልከት።)

# ትምህርት 13

## መናፍቅነት

የትምህርቱ ዓላማ፡– ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ልምምድ፡– (1) ኑፋቄን ለይተን እንድናውቅ፤ (2) ኑፋቄን እንዴት መከላከል እንደምንችል እንድንረዳና (3) ስሕተትን ለመዋጋትና ለመታገል አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ማድረግ እንዳለብን ለማወቅ ነው።

## መግቢያ

አንድ ሰው ደኅንነት ለማግኘት በክርስቶስ በማመን ላይ አንዳንድ ተግባሮችን ወይም ሥራዎችን መጨመር ቢያስፈልግ ወይም ለእውነተኛ መንፈሳዊ ምልክት እንዲሆኑ አንዳንድ ስጦታዎች ወይም ኃይሎች ጐልተው መታየት ካለባቸው የክርስቶስ የተሟላና የተፈጸመ ሥራ ተካደ ማለት ነው። እነዚህን የመሳሰሉት ማንኛቸውም ለደኅንነታችንና ለጽድቃችን በክርስቶስ ካለን እምነት እንድናፈገፍግ የሚያደርጉን ነገሮች ሁሉ ኑፋቄዎች ወይም የስሕተት ትምህርቶች ናቸው።

### 1. እምነትና ሥራ

ጳውሎስ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ ለአይሁድ የሚሰጠው ምስክርነት ብዙ ተቀባይነት አልነበረውም። አይሁዶች «በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ሕግን መጠበቅ አስፈላጊ አይደለም ብሎ ጳውሎስ እንዴት ያስተምራል?» ይሉ ነበር። በአይሁዶች ሕይወት ውስጥ የሥርዓት ሕግ ትልቅ ስፍራ ነበረው። ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ

በክርስቶስ ስላገኘው አዲስ ሕይወት በደማስቆ ከተማ ውስጥ መመስከር ጀመረ። ውጤቱም ለሕይወቱ አስጊ ሆነበት። ደቀ መዛሙርቱ በቅርጫት ውስጥ አስገብተው ከከተማው ግንብ አሻግረው እንዲያመልጥ ረዱት (የሐዋ. 9:20-25)። ከዚያም በኢየሩሳሌም ከተማ ኢየሱስ መሢሕ መሆኑን ጳውሎስ ሲመሰክር አይሁዶች እንደገና ሕይወቱን ለማጥፋት ተነሡበት፤ ስለዚህ ደቀ መዛሙርት ወደ ቂሣርያ ወሰዱት፤ ከዚያም ወደ ትውልድ ከተማው ወደ ጠርሴስ ላኩት (የሐዋ. 9:28-30)። በጳውሎስ አገልግሎት ዘመን ሁሉ ትልቁ የሚያበጣብጠውና ከከተማ ወደ ከተማ እንዲባረር ያደረገው ነጥብ የኦሪት ሕግ የመጠበቅ ክርክር ነበር።

ለክርስትና ትምህርት ዕምብርት ወይም ማዕከላዊ የሆነው ፍሬ ነገር ደኅንነት የሚገኘው በጸጋ ብቻ መሆኑ ነው፤ ከጸጋና ከእምነት የሚገኘው ነፃነት ክርስቲያኖች በምንቸገረኝነት የተንዘላዘለ የሕይወት ደረጃ እንዲኖራቸው ለማድረግ አይደለም። የሥጋ ሥራን መቈጣጠር የሚቻለው በኦሪት ሕግ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ በሚቈጣጠረው ሕይወት ነው (ገላ. 5:22)።

በክርስቶስ በማመንና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን ክርስትና ሕይወት የጀመሩት የገላትያ ክርስቲያኖች እንደገና ወደ ኦሪት ሕግ ሥራ ቀንበር ተመለሱ። ክርስቶስ ከሕግ ሥራ ነፃ ያወጣል (ገላ. 3:1-5)።

ለአይሁዶች የአብርሃም ሥልጣን ትልቅ ስፍራ ነበረው። ጳውሎስ ይህንን በመመርኰዝ አብርሃም ይኖር የነበረው ከሙሴና ከኦሪት ሕግ በፊት ስለነበረ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው በሕግ ሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ መሆኑን አስታወሳቸው። ይህም ጳውሎስ የሰበከው ወንጌል ማለትም በክርስቶስ ማመን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ማረጋገጫ ይሰጣል (ገላ. 3:6-9)። በክርስቶስ ለሚያምኑ ኃጢአተኞች የክርስቶስ ጽድቅ እንደራሳቸው ጽድቅ ይቈጠርላቸዋል። ሕግ ይረገማል፤ ነገር ግን ክርስቶስ የኃጢአትን ርግማን በመሸከሙ፥ እምነት ሕይወትን ይሰጣል (ገላ. 3:10-20)።

ምንም እንኳ ሕግ ቀጥሎ የተሰጠ ቢሆንም ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል ሊደመስሰው አይችልም። እንዲሁም ሥራ የእምነትን ቦታ ሊወስድ አይችልም። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በኦሪት ሕግ ላይ አልተመሠረተም፤ ይልቁንም ሕግ የተሰጠው ኃጢአትን ለማጋለጥና በኃጢአት ላይ ለመፍረድ ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚያደርገው ዋነኛ፥ የመጨረሻና ቀጥተኛ ግንኙነት በጸጋና በእምነት በኩል ነው (ገላ. 3:22-25)።

የተስፋውን ቃል ልንወርስ የምንችልበት ብቸኛ መንገድ ከክርስቶስ ጋር በእምነት በሚኖረን ኅብረት ነው። በክርስቶስ ልዩነቶች ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ የዘርና የትውልድ ልዩነቶች ጠፍተው ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ (ገላ. 3፡26–29)።

በዚህ ዘመንስ እምነትና ሥራ የሚለው ጥያቄ በክርስቲያኖች በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? አንዳንድ የእምነት ተከታዮች አባሎቻቸውን፥ ለደኅንነታቸው ሲሉ የሚያሳትሟቸውን ጽሑፎች በተወሰነ መጠን መሸጥ አለባቸው ይላሉ፥ ሌሎቹም የተወሰኑ ቀናትን አክብሩ ይላሉ (ቈላስይስ 2፡16)፤ አንዳንዶቹም የሚታይ ልምድ መኖር አለበት ይላሉ። ለደኅንነት የሚያበቃ አንዳንድ ተግባሮችን እንድትፈጽሙ ብላ እውነተኛይቱ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ጥያቄ እንዳታቀርብ መጠንቀቅ ያስፈልጋታል። እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋና ክርስቶስ በፈጸመልን ተግባር ላይ ለደኅንነታችን የምንጨምረው አንዳችም ነገር የለም። ሌሎች ተግባሮች ወይም ሥራዎችን ለደኅንነታችን ማግኛ ለመሥራት መሞከር ማለት በክርስቶስ ካገኘነው ነፃነት ሸሽተን ወደ ባርነት ቀንበር መሄዳችን ከመሆኑም ሌላ የክርስቶስን ብቃት መካዳችን ነው።

## 2. በሐሰት አስተማሪዎች ላይ የሚወርድ የቊጣ ፍርድ

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የእምነታቸው በስደት መፈተን ለእምነታቸው ጥንካሬ ዓይነተኛ ማረጋገጫ መሆኑን ይነግራቸዋል። ታማኝነታቸውም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ብቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት መሆኑን ነገራቸው። እግዚአብሔር ትክክለኛ ፍትሕ ስለሚሰጣቸው እንዲሁም እርሱንና ቃሉን በማይቀበሉት ላይ ስለሚፈርድባቸው በትዕግሥት እንዲጠብቁት ጳውሎስ መከራቸው (ሮሜ 1፡28፤ 1ኛ ተሰ. 4፡5)። የእግዚአብሔር ፍርድ ለዘላለም ያጠፋቸዋል፤ ከጌታ ፊትና ከክብሩም ፊት ለዘላለም እንዲለዩ ያደርጋቸዋል። (2ኛ ተሰ. 1ን አንብብ።)

## 3. መሪዎችን ማምለክ

ጳውሎስ በኤፌሶን በቆየበት ጊዜ ከአካይያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ቀጠለ። በቆሮንቶስ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የተረጋጋች ባለመሆኗ ለጳውሎስ ትልቅ ሸክም ነበረች። ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለማምጣት ብዙ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነበር። አጵሎስ በቆሮንቶስ የሰጠው አገልግሎት ብዙ ረድቷል (የሐዋ. 18፡27–28፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡12)።

ጴጥሮስ ቆሮንቶስን ጐብኝቶ ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 9፡5)። ይህም ሆኖ በእነዚህ ሰዎች አገልግሎት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ቡድኖች ፈጥራ እስከ መከፋፈል ደረሰች፤ አንዳንዶችም በጳውሎስ መልእክትና ሥልጣን ላይ ተጠራጠሩ። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ትክክል ቢሆን ኖሮ ስለ መልእክቱ ተጨማሪ ማረጋገጫ አስፈላጊ አለመሆኑን አውቆ ነበር። ስለዚህ በክርስቶስ ላይ በእርግጥ ትክክለኛ እምነት እንዳላቸው ራሳቸውን እንዲመረምሩ መከራቸው። በእርግጥ ክርስቶስ በውስጣቸው ቢኖር ኖሮ የጳውሎስ መልእክት እውነተኛ መሆኑን ይገልጽላቸው ነበር (2ኛ ቆሮ. 13)።

ብዙ የስሕተት ትምህርቶች የተጀመሩት፥ ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎትና አንዳንድ መሪዎችንም በጭፍን በመከተላቸው ነው። የመሪዎቻቸውም መልእክት ትክክል መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ስለማይመረምሩት ነው። (ዮሐ. 8፡32፤ 14፡6ን ተመልከቱ።)

## 4. የተገለጸውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ያለመቀበል

የመጀመሪያዋ የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን በገላትያ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ የጳውሎስ አገልግሎት መጨረሻ ዘመን፥ አይሁዶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱትን የመሢሑን ምልክቶች ሁሉ ክርስቶስ እንደፈጸማቸው የሚመሰክሩትን አልተቀበሉም፤ የአይሁድ መምህራን ጳውሎስ በየሄደበት ከተማ በመከተል አዲስ ያመኑትን ክርስቲያኖች በጳውሎስ ላይ በማነሣሣት የኦሪትን ሕግ መጠበቅ አስፈላጊ ነው እያሉ ይበጠብጡ ነበር። ክርስቶስ መሢሑ ስለ መሆኑ፥ እግዚአብሔር በሙሴና በነቢያት ውስጥ የሰጠውን የተስፋ ቃል አልተቀበሉም፥ እንዲያውም ካዱ። በዚህም ምክንያት ጳውሎስ ለገላትያ ቤተ ክርስቲያን ስለ እምነትና ሥራ ለመጻፍ ተገደደ። እግዚአብሔር አሕዛብን በመቀበሉ አይሁዶችን ትቷቸዋል ማለት አለመሆኑን ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ በግልጽ ጽፏል። እግዚአብሔር አይሁዶችን እንዳልተወ እነርሱ ግን ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እንደተዉ ጳውሎስ ጽፏል። (ሮሜ 11 አንብብ)።

## 5. መናፍቅነትን የመከላከል ዘዴ

ጳውሎስ በእስር ላይ እንዳለ ለፊልጵስዩስ ሰዎች መልእክት ጻፈ። በመልእክቱም የስሕተት ትምህርት መኖሩን እንዲያውቁና ለመከላከልም ዝግጁ እንዲሆኑ መከራቸው። የስሕተት ትምህርትን ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎችን ሰጣቸው፡—

ሀ/ በእምነት «ጸንተው መቆም» ነበረባቸው፤

ለ/ እርስ በርስ የማይስማሙትን ሁለት ሴቶች «በጌታ እንዲስማሙ» በተለይ መከራቸው፤

ሐ/ «በጌታ ደስ ይበላችሁ» ተብሎ ተነገራቸው፤

መ/ ለሰዎች ሁሉ ይቅርታ እንዲያደርጉ፤ እንዲታገሡና አስተዋዮች እንዲሆን ተመከሩ፤

ሠ/ በጸሎት እንዲተጉ እንጂ እንዳይጨነቁ ተመከሩ፤

ረ/ በአእምሮአቸው ውስጥ እውነት የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት፤ ጽድቅ፥ ንጹህ፥ ፍቅር መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ እንዲያስቡ ተነገራቸው።

ብዙ ጊዜ መናፍቅነት የሚነሣው በትንሽ ነገር ባለመግባባት ወይም ለአንድ ነገር ያልሆነ ትርጉም በመስጠትና አእምሮን ለመልካም ነገርና ለእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ባለማስገዛት ነው። (ፊልጵስዩስ 4ን አንብቡ።)

## 6. በእምነት ጸንታችሁ ቁሙ

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው ለአይሁዶች መሆኑ አያጠራጥርም። በመልእክቱ ውስጥ ስለ ውድቀቷ የተጠቀሰ ነገር ባለመኖሩ፥ የተጻፈው ከኢየሩሳሌም መፍረስ ወይም መውደቅ በፊት ሳይሆን አይቀረም። የዕብራውያንን መልእክት የጻፈው ጳውሎስ በእስራት ላይ በነበረት ጊዜ መሆኑን ብዙ ምሁራን ያምናሉ።

በሮም የነበረው ሁኔታ ጳውሎስ ስለ ክርስቲያኖች እንዲያስብ ምክንያት ሆነው። ያላቸው ችግር ሥነ-ምግባራዊ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ጸንቶ ለመቆም አለመቻላቸው ነበረ። መለኮታዊ የሆነውን ቃል ለማወቅ ዝግጁ ወይም ፈቃደኛ ያለመሆን መንፈሳዊ ኪሳራ እንደሚያስከትል ጳውሎስ በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ውስጥ አመልክቷል። በሮም ያሉት ክርስቲያኖች በእንዲህ ያለ ውድቀት ላይ መድረሳቸውን በየትም ስፍራ አልጠቀሰም፤ ነገር ግን እዚህ ደረጃ ለመድረስ እንደሚቻል አጥብቆ አሳቡን ገልጿል።

## 7. አፈ-ታሪክና የትውልድ ሐረግ

በመጀመሪያውና በሁለተኛው የጳውሎስ እስራት መካከል ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር ወደ ኤፌሶን ተጉዞ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል እዚያው ቀረ። ጳውሎስም ጢሞቴዎስን በአገልግሎት ለመርዳትና ለማጽናናት መልእክት ጻፈለት።

ጳውሎስ በሌላ ዓይነት መንገድ ከእውነት ስለሚርቁ ሰዎች ጢሞቴዎስን አስጠነቀቀ። ይኸውም አንዳንዶች አፈ–ታሪክና ስለ ዘር ሐረግ ያስተምሩ ነበር። እነዚህ አስተማሪዎች አንዳንድ ሃይማኖት ጠቀስ ታሪኮችን፥ ለምሳሌ፥ ምናልባትም ከብሉይ ኪዳን ወስደው የሰሚዎቹን አእምሮ የሚማርክ ትርጒም ይሰጡታል። ትርጒማቸውም ከተማሩት በክርስቶስ ማመንን ትተው በዘር ሐረጋቸው እምነት እንዲጥሉ ያደርጋቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ የእውነትን ቃል ሳያውቁና ሳይገባቸው አስተማሪዎች ለመሆን ከመፈለጋቸው የተነሣ በእውነት ላይ ያልተመረኮዘ አፈ–ታሪክን ያስተምሩ ነበር። በ1ኛ ጢሞ. 1፡1–7 ያለው የብሉይ ኪዳንን ዘመን ይጠቍም ይሆናል፤ ወይም በአባቶቻቸው እንዲመኩ የሚያደርጋቸው ይሆናል።

ጳውሎስ ምእመናኑ በመጀመሪያ የተማሩትን እንዲያስታውሱና አፈ–ታሪክና የትውልድ ሐረግ ከሚያስተምሯቸው እንዲርቁ ማስተማሩን እንዲቀጥል ለጢሞቴዎስ ጻፈለት (1ኛ ጢሞ. 4፡7፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡14)።

## 8. ራስን መካድና ራስን መጨቈን

በጳውሎስ ዘመን የነበረው ሌላው ፍልስፍና ለሰውነት ጠቃሚ ስለሚሆነው ምግብና ስለ ጋብቻ ነበር። ቍሳዊ ነገሮች ሁሉ ርኩስ እንደሆኑና እግዚአብሔርም እንዳልፈጠራቸው የሚያስተምሩ ነበሩ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ለሰው አገልግሎት እንደተፈጠረ አሳሰበው። ትክክለኛ አጠቃቀማቸው ግን በእምነት የእውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል በሙላት ማወቅ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን፥ በምስጋና መንፈስ ልንጠቀምባቸው ይገባናል። እነኚህ የስሕተት ትምህርቶች ለማሳሳትና ለማታለል በሰይጣን የተሞሉ ትምህርቶች ስለሆኑ ጢሞቴዎስ እንዲጠነቀቅ ጳውሎስ ጻፈለት (1ኛ ጢሞ. 4፡1–3፤ ቈላስ. 2፡18)።

## 9. የስሕተት አስተማሪዎች ባሕርይ

እነዚህ የስሕተት አስፋፊዎች ተቀባይነትን ለማግኘት የሚለማመጡ ቢሆኑም ትዕቢተኞችና ከራተኞች መሆናቸውን ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ አስገነዘበው። ፈሪሀ–እግዚአብሔርን መለማመድ ለግል ጥቅም እንደሆነ ያስተምሩ ነበር። ትምህርታቸው ቅናትን፥ ጠብን፥ ክርክርንና ብዙ ጥያቄዎችን ፈጥሯል። የሚያስተምሩትም እውነትን ሳይሆን ቃላትን በማብዛት ሰዎች ገንዘብ ወዳድና የሥጋ ፍትወትን የሚወዱ ማድረግ ነው (1ኛ ጢሞ. 6)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው በሁለተኛ መልእክቱ ሰዎች ከእውነት መስማት የሚፈልጉትን ነገር ብቻ ወደሚያስተምሯቸው ምሁራን ለመጠጋት የሚፈልጉበት ዘመን እንደሚመጣ ገልጿል (2ኛ ጢሞ. 4)።

## 10. ትክክለኛ ትምህርት

ቲቶ በቆሮንቶስ ያለውን ችግር ለማቃለል ጥረት ያደረገ ሌላው የጳውሎስ ረዳት ነበረ። በሁለቱ የጳውሎስ የሮም እስራቶች መካከል ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በመጓዝ ወደ ቀርጤስ ሄዶ እዚያው ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ቆየ። ቲቶ በቀርጤስ እንዳለ ጳውሎስ መልእክቱን ጻፈለት (ቲቶ 1፡5)።

ስሕተቶችን በሚገባ ለመዋጋት ትክክለኛ ትምህርት ማስተማር እንዳለበት ጳውሎስ አስገነዘበው። በዕድሜ ለተለያዩ ወንዶችና ሴቶች እንዴት ማስተማር እንዳለበት መመሪያ ሰጠው።

ትክክለኛ ትምህርት የሚሰጠው በሕይወትና በቃል ስለሆነ ቲቶ በሁለቱም መንገድ ምሳሌ እንዲሆን ጳውሎስ ጻፈለት። ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ሰው ሊኖረው የሚገባውን ባሕርያት ጳውሎስ በዝርዝር አቅርቧል። (ቲቶ 2ን አንብብ።)

### ማጠቃለያ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የስሕተት ትምህርት ወይም ኑፋቄ የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን መለያየት የሚያመጣውንና ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል አስጊ የሆነውን ነገር ያመለክታል (1ኛ ቆሮ. 11፡18–19)። ይህም ከሥጋ ሥራዎች ውስጥ መሆኑ በገላትያ ተገልጿል (ገላ. 5፡20)። መለያየትን የሚፈጥሩ ከማኅበሩ ሊገለሉ ይገባል (ቲቶ 3፡10–11)። በመመሥረት ላይ በነበረችው የጥንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛው የመለያየት ምክንያት የአይሁድ እምነት ሳይሆን አይቀርም። ከሮማውያንና ከግሪክ ሥርዓት አመለካከት የተወረሱት አስተሳሰቦች ክርስቲያኖችን ይበጠብጡ ነበር።

### ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ወደ አሕዛብ በሄደበት ጊዜ ሁሉ ስደትን ለመፍጠር ዋንኛ ምክንያት የሆኑት እነማን ነበሩ? (የሐዋ. 13፡50፤ 14፡19፤ 17፡5፤ 17፡13)
2. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመለያየት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው? (1ኛ ቆሮ. 1፡11–13 ተመልከት።)

3. ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የስሕተትን ትምህርት እንዲከላከሉበት የሰጠውን አምስት ነጥቦች ዘርዝር።

4. ሦስቱ የሐሰት መምህራን ባሕርያት ምን ምን ናቸው? (1ኛ ጢሞ. 6፡3-5)።

5. የስሕተት ትምህርቶችን በሚገባ ለመከላከል ወይም ለመዋጋት ይጠቅማል ብሎ ጳውሎስ ለቲቶ የነገረው ዘዴ ምን ዓይነት ነው? (ቲቶ 1፡9 ተመልከት)።

# ትምህርት 14

## ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ያስተማረው ትምህርት

የትምህርቱ ዓላማ፡- የክርስቶስ ዳግም ምጽአትን ማወቅና እርሱን ተስፋ ማድረግ የቅድስናን ሕይወት የሚያነቃቃ መሆኑን ለማስረዳት ነው።

### መግቢያ

ጳውሎስ አገልግሎቱን ጀምሮ እስከ ጨረሰበት ጊዜ ድረስ አከራካሪ ሆኖ የቆየው ነጥብ የክርስቶስ ትንሣኤ ነበር። ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ስላየ ይህንን መገለጥ ስለ ትንሣኤና ስለ ራሱ ጥሪ እንደ መከላከያ አድርጎ ተጠቀመበት።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ወደፊቱ ዘመን ሲያስተምር የትምህርቱ ፍሬ ነገር የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሲሆን፥ ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ከዚህ ጋር ተያይዘዋል።

### 1. ጳውሎስ ስለ መሢሑ ያስተማረው ትምህርት

ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ከተማ እንደገባ እንደ ልማዱ ወደ ምኵራብ ሄደ። ኢየሱስ መሢሑ ስለ መሆኑ መሢሑ እንደ ሞተና ከሞትም እንደ ተነሣ ከመጻሕፍት እየጠቀሰ አይሁዶችን ለማሳመን ተጣጣረ።

አይሁዶች በቅንዓት ተነሣሥተው የቄሣርን አዋጅ በመቃወም እንዲስተማረ አድርገው ጳውሎስን በመክሰስ ሕዝቡን አነሣሡ (የሐዋ. 17፡1-9)።

ጴጥሮስ ከዚያም ቀደም ብሎ ኢየሱስ መሢሑ ስለ መሆኑ ተመሳሳይ መልእክት ሰጥቶ ነበር (የሐዋ. 3)።

በአቴና ውስጥ ጳውሎስ የሰበከው በአንድ ተራራ ላይ ነበር። ከዚያም የከተማው ፈላስፋዎች ጳውሎስን ካዳመጡት በኋላ ወደ

አሪዮስፋጎስ ማለትም ወደ የሕዝባዊ ሸንጎ ሹማምንት ወስደው ስለ አዲሱ መልእክቱ እንዲያብራራላቸው ጠየቁት። ጳውሎስም ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለሚመጣው ፍርድ በነገራቸው ጊዜ አፌዙበት።

## 2. ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ ክርስቶስም እንዲሁ ይመጣል።

በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ምጽአትና ስለ ሙታን ትንሣኤ ብዙ ጥያቄዎች ነበሩአቸው። ስለዚህ ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ከተመለሰ በኋ ወዲያውኑ መልእክት ጻፈላቸው። ከእነርሱ አንዳንዶቹ ከክርስቶስ ምጽአት በፊት ስለሞቱ ምን እንደሚሆኑ አልገባቸውም ነበር። ጳውሎስ አስቀድመው በጌታ የሞቱት ሕያዋን ከሆኑት ጋር አብረው እደሚነጠቁ ገለጸላቸው (1ኛ. ተሰ. 4:13–18)። ሆኖም የክርስቶስ ምጽአት ቀን አይታወቅም። ሰዎች ስለ ሰላምና ስለ ዋስትና ሲያወሩ ድንገት የጥፋት ቀን ይመጣል። እኛ ግን የብርሃን ልጆች ስለሆንን በጨለማ ውስጥ መመላለስ የለብንም፤ ወይም ልንደነቅ አይገባንም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ቃል ወደ ምጽአቱ ስለሚመራንና ለዚያም ቀን ስለሚያዘጋጀን ነው (1ኛ ተሰ. 5:1–9)።

ክርስቲያኖች ትንቢትን መናቅ የለባቸውም፤ ነገር ግን ሁሉንም መመርመር አለባቸው። ክርስቲያኖች መትጋት፥ መጠንቀቅና እርስ በርሳቸውም መመካከር አለባቸው (1ኛ ተሰ. 5:10–28)።

## 3. የክርስቶስ ምጽአት ምልክቶች

ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ዐመፀኞች በምድር ላይ ይነሣሉ። ከዚያም የክርስቶስ ተቃዋሚ ይነሣና በቤተ መቅደስ ተቀምጦ እግዚአብሔር ነኝ ይላል። በአሁኑ ጊዜ ክፋትን የሚቈጣጠር አለ፤ ግን እርሱ በተወገደ ጊዜም የጥፋት ልጅ በኃይል፥ በምልክትና በተአምራት ይገለጻል። እውነትን የማይቀበሉት ይወገዛሉ (2ኛ ተሰሎ. 2)።

በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራን የሚጠሉና ለዕለት ኑሯቸው ሥራን ሠርተው መብላት የማይፈልጉ ነበሩ። ጳውሎስ በቃልና በሥራ ያስተማራቸውን እንዲያስታውሱና ሥራ ፈትነት በሌሎች ሕይወት ጣልቃ መግባትን ስለሚያመጣ ሥራን ከሚጠሉ እንዲጠበቁ የተሰሎንቄን ክርስቲያኖች ይመክራቸዋል (2ኛ ተሰሎ. 3)።

## 4. የክርስቶስ ትንሣኤ አስፈላጊነት

የክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና መሠረት ነው፤ ይህን መካድም የወንጌልን መሠረት እንደማስወገድ ነው። ጳውሎስ የወንጌልን ዋና

ነጥቦች ለቆሮንቶስ ሰዎች በድጋሚ ያስገነዝባቸዋል። የእነርሱ ትንሣኤ የተመሠረተው በክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ነው። የክርስቶስን ትንሣኤ ከካዱ እምነታቸው ሁሉ ውድቅ ይሆናል፤ በክርስቶስ የሞቱትም ተስፋ የላቸውም ማለት ነው። ክርስቶስ የትንሣኤ በኩር ነው። ሕያው ሆኖ ስለሚኖርም በእርሱ የሚያምኑ ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ።

አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች የሰውን ነፍስ በሚመለከት ረገድ በግሪካውያን ፍልስፍና ያምኑ ነበሩ። የዚህም አስተሳሰብ ነፍስ ከሥጋ በተለየች ጊዜ ወደ ሌላው ዓለም ለመኖር ትሄዳለች፤ ሥጋ ግን ትንሣኤ ሊኖረው አይችልም ይሉ ነበር (1ኛ ቆሮ. 15፡1–19)።

## 5. ክርስቶስ የሙታን በኩር ነው።

ክርስቶስ የትንሣኤ በኩር ሆነ። አዳም ሞትን ወደ ዓለም አመጣ፤ የሰው ልጅ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ግን ሕይወትን አመጣ። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ሁሉ እንደ እርሱ ከሞት ትንሣኤን ያገኛሉ።

በመጨረሻ ኃይላትን፥ ሥልጣናትንና አስተዳደርን ሁሉ አፍርሶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመጣል። ከሚደመሰሱት ጠላቶች በመጨረሻ የሚደመሰሰው ሞት ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 15፡20–28)።

አንዳንድ የቆሮንቶስ ሰዎች ሕያዋን የሆኑት ሰዎች ሳይጠመቁ ለሞቱት ወገኖች ሊጠመቁላቸው ይችላሉ የሚል አሳብ ነበራቸው። ይህንን የሚያስተምሩት ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ስለሌላቸው፥ ክርስቲያኖች ከእነርሱ እንዲጠበቁ ጳውሎስ አስጠንቀቃቸው (1ኛ ቆሮ. 15፡29–34)።

## 6. የትንሣኤ አካል

ግሪኮች፥ ትንሣኤ የሚለውን ቃል በፍልስፍናቸው መሠረት ሲተረጉሙት የሰው መንፈሱ ብቻውን ሳይጠፋ ሕያው ይሆናል ብለው ያስተምሩ ነበር። ጳውሎስ ግን ሕይወትን ለመቀጠል ይህ ሥጋችን መሞት አለበት ብሎ አስተማረ (1ኛ ቆሮ. 15፡36–38፤ ዮሐ. 12፡24)። ጳውሎስ አዲሱ ሕይወት አሮጌውን ቢመስልም አንድ ዓይነት ያለመሆኑን ተናገረ። አዲሱ አካል ከአዲሱ ሕይወት ጋር ይዋሐዳል (2ኛ ቆሮ. 5፡1–4)። ትንሣኤ ማለት የአሮጌው ሕይወት ተሐድሶ ሲሆን በአዲስ መንገድ የሚሠራ ማለት ነው። አካላችን በሕይወት እያለን እንኳ እየተዳከመ ይሄዳል፤ በመቃብር ውስጥም ከሞት በኋላ እንዲሁ እየጠፋ ይሄዳል።

ይህ ሥጋዊ አካላችን የተሠራው ለዚህ ምድራዊ ሕይወታችን ሲሆን፥ አዲሱ አካላችን ደግሞ ለአዲሱ ሕይወት ነው። የመጀመሪያው አዳም ይህንን ሥጋዊ አካላችንን ሲያስገኝ፥ የመጨረሻው አዳም ክርስቶስ ግን የተዋጁትን አዲሱን ትውልድ አስገኘ። አዲሱም አካል ለመንፈስ የተገዛ አካል ነው። ክርስቶስ በውስጣቸው ስላለና እነርሱም በክርስቶስ ውስጥ ስላሉ የአዲሱ ሕይወት ተካፋዮች ናቸው፥ ክርስቶስንም የመሰለ አካል ይለብሳሉ። (1ኛ ዮሐ. 3፡2ን ተመልከት።)

በ1ኛ ተሰ. 4፡15–16 ውስጥ ጳውሎስ የገለጸው ምሥጢር በዚያን ወቅት በምድር ላይ የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ሞትን ሳይቀምሱ በቀጥታ እንደሚለወጡ ነው (ፊልጵ. 3፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡35–53)።

የመጨረሻው የእግዚአብሔር መለከት ሲነፋ ይህ ሥጋዊ አካላችን ለአዲሱ ሕይወት ተገቢ ወደሆነው ወደ አዲሱ አካል ይለወጣል (1ኛ ተሰ. 4፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡53)።

ምንም እንኳ አሁንም ሞት በኃጢአት ምክንያት ቢኖርም በክርስቶስ ምጽአት ፍጹም ይጠፋል። በአሁኑም ሕይወት ቢሆን ክርስቶስ በሞት ላይ ያገኘውን ድል ክርስቲያን ተካፋይ ነው። የእርሱ አዲስ ሕይወት አሁንም በውስጣችን በመሥራት ላይ ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡54–57)።

ጳውሎስ ትምህርቱን ሲያጠቃልል ከዚህ ሁሉ የተስፋ ቃሎች በመንደርደር «ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ» ይላል፥ (1ኛ ቆሮ. 15፡58)።

## 7. የቃል ኪዳኑ መሢሕ

ከሮሜ ምዕራፍ 9–11 ባለው ውስጥ ጳውሎስ «አይሁዶች እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው መሢሑን ባለመቀበላቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ፈረሰን?» የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። አይሁዶች የብሉይ ኪዳን ተስፋ ቃል የሚፈጸምበትን የመጨረሻ ዘመን ይጠብቁ ነበር። ይህ የተስፋ ቃል አሁን በከፊል ተፈጽሟል። የዚህን የመጨረሻውን ዘመን ፍጻሜ የምሥራች ሊያውቁ የሚገባቸው ሰዎች ማለትም አይሁዶች እንዲያውም መቃወማቸውን ተረድቶ ጳውሎስ ይህን ያየውንና የሰማውን ማመን አስቸጋሪ ሆነበት (ሮሜ. 10፡1–4)።

ጳውሎስ በሮሜ 10፡5–17 ደኅንነት ለአንድ አገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝቦች በሙሉ መሆኑን ከሚከተሉት መጻሕፍት ጠቀሰላቸው (መዝ. (19)፡4፤ ዘዳግ. 32፡21፤ ኢሳ. 65፡1)። ይህ ከወንጌል

ክፍል አስፈላጊ ከሆኑት ነጥቦች አንዱ ቢሆንም ለአይሁዶች ግን ለመረዳት ከሁሉ በላይ ያስቸገራቸው ክፍል ነበር።

መሢሁ በመምጣቱ አዲስ ዘመንን ስላመጣ አሮጌው ከአገልግሎት ውጭ ሆነ። ይህም ከባድ ችግር ፈጠረ፤ ይኸውም፦ ብሉይ ኪዳን አሁንም ሥልጣን አለውን? የሚል ነበር። ጳውሎስም በተለይ በሮም ለነበረው ለአይሁድ ቡድን ሲጽፍ፥ ከብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ በመጥቀስ ብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ያለው መሆኑን ጠቁሞ፥ ብሉይ ኪዳን ራሱ ክርስቶስ የመለኮታዊ ራእይ ሁሉ ከፍተኛ ፍጻሜ መሆኑን እንደሚያመለክት አስገንዘበ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ወደ ልጁ ያመለክታል (ዕብ. 1፡1–3)። የአይሁዶችን ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ የያዙት ሙሴና አሮን ይቅሩና አማልክት እንኳ ለእግዚአብሔር ልጅ ሰገዱ (ዕብ. 1፡4–14)። አሁንም እኛ የምንኖርበት ዘመን ብሉይ ኪዳን አስቀድሞ ሙሉ በሙሉ ያመለከተው ዘመን ነው። ስለ አሁኑ ዘመን ማለትም ስለ መጨረሻው ዘመን ዮሐንስ በራእይ እንዲገልጽ መንፈስ ቅዱስ አሳሰበው፤ ይህም ዘመን የክርስቶስ ምጽአት ወደ ፍጻሜ የሚያቀርበው ነው።

## 8. የወደፊቱ ባርኮት

ጳውሎስ ሦስት ዓመት በኤፌሶን በመቆየቱ ወንጌል በኤፌሶን አካባቢ ባሉት አውራጃዎች ሁሉ ተሰራጨ፤ ሆኖም ጳውሎስ በኤፌሶን ብዙ መከራን ተቀበለ።

ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ውስጥ በኤፌሶን ሳለ ስለ ደረሰበት መከራ ምንም አልገለጸም። ከዚህ ይልቅ አሁንና ለወደፊቱ ለክርስቲያኖች የሚሰጠውን በረከት ጻፈ (ኤፌ. 1፡3–9)። የእግዚአብሔር ዓላማ በምድርና በሰማይ ያሉትን ሁሉ ወደ ራሱ ለማሰባሰብ ነው። አማኝ የሆነ ሁሉ በክርስቶስ ምጽአት ወቅት ወራሽ እንደሚሆን ቃል ኪዳን ተደርጎለታል (ኤፌ. 1፡9–18)። የክርስቲያኖች ተስፋ በዚህች ምድር ላይ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት በሚያጋጥማቸው ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው (ኤፌ. 1፡19–23)።

## ማጠቃለያ

ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ምጽአት የሰጠው ትምህርት የተመሠረተው በብሉይ ኪዳን ላይ ነው። «የዘመኑ መጨረሻ በመጣ ጊዜ» የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ዓለም መጥቷል። የክርስቶስ ከሞት መነሣትና መንፈሱም በአማንያን ሕይወት ውስጥ መኖሩ ብኩርና ነው (ሮሜ 8፡23፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡20፥ 23)። የክርስቶስ ምጽአትና የክርስቲያኖች

ንጥቀት የተመሠረተው «የጌታ ቃል» በሚለው ላይ ነው (1ኛ ተሰ. 4፡15–17)። ጳውሎስ ስለ ወደፊቱ ዘመን ያለው አሳብ ሁሉ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ የተመሠረተ ነው።

ጳውሎስ በእስራት ዘመኑ በጻፈው መልእክት ውስጥ በብዛት የጠቀሰው «በክርስቶስ ውስጥ» የሚልና «የክርስቶስ አካል» የሚል ነው፤ ከዚህም ሌላ ጳውሎስ «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒት... ክቡር ሥጋውን እንደሚመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል» ብሷል (ፊልጵ. 3፡20–21)።

ጳውሎስ በቲቶ መልእክቱ ውስጥ «የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን» ብሎ ጽፏል (ቲቶ 2፡13)። የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ማለት ፍርድንም ያጠቃልላል፤ ለክርስቲያኖች ግን የፍርድ ውሳኔ የታወቀ ነው (ሮሜ. 8፡1)። ከክርስቶስ ውጭ ላሉት ምጽአቱ ድንገተኛ ጥፋት፥ ቁጣና ኩነኔ ይሆንባቸዋል (1ኛ ተሰ. 1፤10፤ 5፡3፥ 9፤ 2ኛ ተሰ. 2፡10–12)።

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት፦ 1. የአሕዛብ ቍጥር ይሟላል (ሮሜ. 11፡25)። 2. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባላቸው የተስፋ ቃል በመጨረሻ ይሟላል (ሮሜ 11፡26–31)። 3. በሰው ኃጢአት ምክንያት ተፈጥሮ ከደረሰበት እስራት ነፃ ይወጣል (ሮሜ 8፡19–22፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡31)። 4. ሥልጣንና ኃይላት ሁሉ ለልጁ የተገዙ ይሆናሉ፤ ልጁም እነዚህን ሁሉ ለአባቱ ያስረክባል (1ኛ ቆሮ. 15፡24፥27)። 5. በመጨረሻም ጠላት የሆነው ሞት ይጠፋል (1ኛ ቆሮ. 15፡26)። 6. እንዲሁም ልጁ ራሱም ሁሉን ከበታቹ ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል፤ ይህም እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡28)።

የኢየሱስ የመዋጀቱ ሥራ ተፈጽሟል፤ በተግባር ተፈጻሚነቱ ግን እያደገና እየጨመረ ይሄዳል፤ ፍጻሜ የሚያገኘው ግን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና» ብሎአል (ራእይ 22፡17)።

## ጥያቄዎች

1. አይሁዶች ክርስቶስን እንደ መሢሕ ያልተቀበሉበት አንዱ ምክንያት ምንድን ነው? (የሐዋ. 17፡5)።
2. የተሰሎንቄ ሰዎች ስለ ትንሣኤ የተጨነቁበትና ጳውሎስ በ1ኛ ተሰ. 4፡13–18 መልስ የሰጠበት ጥያቄ ምን ነበር?

3. የክርስቶስ ትንሣኤ በወንጌል ውስጥ ትልቅ ቦታ የያዘው ለምንድ ነው? (1ኛ ቆሮ. 15፡12−19)።

4. አይሁዶች ከተሰበከላቸው የወንጌል መልእክት ትምህርቶች መካከል ለመረዳት የሚያዳግታቸው የትኛው ክፍል ነው? (ሮሜ 10፡12−13)።

5. ክርስቶስ ሲመለስ የሚፈጸም ለክርስቲያኖች የተሰጣቸው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? (ኤፌ. 1፡11፥14፤ ቈላ.1፡12ን ተመልከት)።

# ትምህርት 15

## ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

የትምህርቱ ዓላማ፦ ክርስቶስ በሰጠን ነፃነት ውስጥ ያለውንና ልንኖርበት የሚያስችለንን ኃይል የራሳችን አድርገን መያዝ እንደምንችል ለማመልከት ነው።

### መግቢያ

በጳውሎስ ትምህርት የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን በሚለው እውነት ላይ ነው። ይህም ሕይወት በክርስቶስ ፍቅር የተነቃቃ ነው። ይህንን ሕይወት እንድንኖር መንፈስ ቅዱስ ያስችለናል። ጳውሎስ እንዳስተማረው ከክርስቶስ ውጭ ደኅንነት የለም። ደግሞ ራሳችንን ለክርስቶስ ካላስገዛን በቀር የክርስትናን ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ሌላ መንገድ የለም ብሎ ጳውሎስ አስተምሯል (2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ሮሜ 8፡10−14)። በጳውሎስ ትምህርት ውስጥ የክርስትና ኑሮ ትልቅ ስፍራ አለው።

### 1. የእምነት ነፃነት

በገላትያ ከሕግ በታች ለነበሩት አይሁዶች በጸጋው ደኅንነት ነፃነትን አመጣላቸው። ነፃነት ሰጣቸው። በክርስቶስ በማመን ነፃ የሆኑት ምእመናን ዳግመኛ የሥርዓት ተገዥ እንዳይሆኑ ጳውሎስ መከራቸው። በገላትያ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የክርክር ነጥብ ስለ መገረዝ ጉዳይ ነበር። የመገረዝን ሥርዓት መጠበቅ ከሕግጋቱ ውስጥ አነስተኛ ክፍል ብቻ ነው፤ ነገር ግን ሰውን ከኦሪት ሕግ ሁሉ በታች እንዲሆን ያደርገዋል፤ ይህም ፍጹም መታዘዝን ይጠይቃል። ይሁን እንጂ ለኦሪት ሕግ ፍጹም ተገዥ መሆን በሰው ደረጃ የማይቻል ነው። በክርስቶስ ባገኘነው ነፃነት ላይ የሕግ ሥርዓቶችን ለመጨመር መሞከር ክርስቶስን እንደማንቋሸሽ ይቈጠራል፤ ምክንያቱም አንድ ሰው በኦሪት ሕግ ሥራ ራሱን ለማዳን እየሞከረ በተደራቢ ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ

ለደኅንነቱ ሊያምን ስለማይችል ነው። ደኅንነት በራሳችን ጥረት ማግኘት የምንችለው ጉዳይ ሳይሆን በክርስቶስ የምናገኘው የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ገላ. 5፡1-12)።

ክርስትና የኦሪት ሕግ መጠበቅ አይደለም፤ ክርስትና ከክርስቶስ ጋር የሚኖረን የግል ግንኙነት ነው፤ ይኸውም የፍቅርና የእምነት ሕግ ነው። ይህ ነፃነት ትክክል የሆነውን ነገር የማድረግ ነፃነት ነው፤ የሥጋ ፍላጎትን ለማርኪያ ሳይሆን ለሌሎች ሰዎች ለማሰብና ሌሎችን ለመርዳት ነፃ መሆን ነው። ከሕግ በታች ካለው ይልቅ ከጸጋ በታች ያለው ኃላፊነት የበለጠ ነው። ነፃነታችን በንዝህላልነት ለመኖር ምክንያት አይሆንም (ገላ. 5፡13-25)።

የገላትያ ክርስቲያኖች በአይሁድ እምነት መምህራን በቀላሉና በቶሎ ይማረኩ ነበር፤ እነዚህ ሰዎች ጳውሎስን በየደረሰበት አሳቡን እንዲለውጥ የሚጥሩና አዳዲስ ክርስቲያኖችንም ሁሉ ሲያገኙ የአይሁድ የሕግ ሥርዓቶችን በሙሉ እንዲጠብቁ ለማሳመን የጣሩ ናቸው።

## 2. የንጽሕና ኑሮ

ክርስቲያኖች በንጽሕና እንዲኖሩ የሚያስችላቸው በሕይወታቸው ውስጥ ያለው የክርስቶስ ሙሉ ሥልጣን ነው። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የኖሩት ኑሮ ግን ከክርስቲያኖችም ሆነ ከአይሁድ ኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ በሆነ ኅብረተሰብ ውስጥ መሆኑን ጳውሎስ ያውቅ ነበር።

በሮምና በግሪክ ማኅበረሰብ ውስጥ ዝሙት እንደ ምግብና መጠጥ ያህል ተቀባይነት ነበረው። ጳውሎስ ይህንን በመገንዘብ «እግዚአብሔር ለቅድስና ኑሮ እንጂ ንጽሕና ለሌለው ኑሮ አልጠራንም» ብሎ ይጽፋል። ወንድሞችን አለመበደልና ለአንድ ሚስት ታማኝ መሆንና ራስን መግዛት እንደሚያስፈልጋቸው ይመክራቸዋል። ይህ አባባሉ የሚያመለክተው በተሰሎንቄ አማኞች መካከል ዝሙት እንደ ነበረ ማወቁን ወይም መሥጋቱን ነው። ይህ መልእክት የተጻፈው ከተማይቱን ለቅቆ እንዲሄድ ከተገደደ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ነበር። ጳውሎስ ከተማይቱን እንዲለቅ የተገደደው በእንግድነት የተቀበለውን ኢያሶንን ችግር ሊፈጥሩበት ሲሉ ነበር። እግዚአብሔር የኃጢአት ኑሮን በመቅጣት እንደሚበቀል አስገነዘባቸው (1ኛ ተሰ. 4፡1-7፤ ኤፌ. 5፡6፤ 1ኛ ቆሮ 6፡13-20)።

## 3. የሥራ ክቡርነት

ሌላው የግሪክ- ሮማውያን ኅብረተሰብ ሕይወት ባሕርይ ንዝህላልነትና ሥራ ፈትነት ይኸውም የጉልበት ሥራን ማንቋሸሽ ነበረ። ይህም ሁኔታ ከዚህ ኅብረተሰብ ጋር አብረው የሚኖሩትን ክርስቲያኖችንም ማርኮአቸው ነበር። ሥራ ፈትነት የራስን ጉዳይ አስትቶ በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ሐሜተኝነትን ያስከትላል። በዚህ ምክንያት ጳውሎስ ክርስቲያኖች «በጸጥታ የራሳቸውን ሥራ እንዲሠሩና ለዕለት ኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ» ይመክራቸዋል። የአይሁድ ምሁራን እንኳ ሕግን በማስተማራቸው ጥቅም ለማግኘት ከመሯሯጥ ይልቅ ሥራ በመሥራት የዕለት ኑሮአቸውን እንዲያሸንፉ ይጠበቅባቸው ነበር። ጳውሎስ ድንኳን በመስፋትና ቆዳ በመፋቅ የዕለት ኑሮውን ይገፋ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ግሪኮች ይንቁት ነበር (2ኛ ተሰ. 3፡1–15፤ 1ኛ ተሰ. 4፡11–12)።

## 4. አዲሱ «ግብረ–ገብነት»

የቆሮንቶስ ከተማ ሌላዋ የአሕዛብ ከተማ በመሆኗ ባህሏ ቤተ ክርስቲያንን በጣም አዳከመ። በክርስቶስ ያገኙትን ነፃነት በጣም በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም አንዱ የአባቱን ሚስት ማለትም የእንጀራ እናቱን አገባ። ይህ በአሕዛብ ማለትም ሃይማኖት በሌላቸው ሰዎች ዘንድ እንኳ ትልቅ ነውር ነበረ።

ጳውሎስ በመልእክቱ ስለ ንዝህላልነታቸው ገሠጻቸው፤ እንደዚህ ያደረገውን ሰው በስብሰባ እንዲያወግዙትና ቅጣት እንዲሰጡት ጠይቋቸዋል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለው ርኩሰት ሲሠራ ዝም ብሎ ማየታቸው የበሰሉ አለመሆናቸውን ያሳያል፤ እንዲህ ዓይነቱ ርኩሰት ቤተ ክርስቲያኒቱን በሙሉ የሚያረክስ ነበረ (1ኛ ቆሮ. ምዕራፍ 5)።

## 5. ቅዱሳን በዓለም ይፈርዳሉ

በአሕዛብ ከተሞች የሚኖሩ አይሁዶች ክሳቸውን ወደ አሕዛብ ፍርድ ቤት አይወስዱም። በቆሮንቶስ የሚገኙ ክርስቲያኖች ግን በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ወደ አሕዛብ ፍርድ ቤት እንደሚወስዱና እንደሚካሰሱ ጳውሎስ በሰማ ጊዜ በጣም ደነገጠ። የአሕዛብ ፍርድ ቤት የተበላሸ ነው የሚል አሳብ የለውም፤ ነገር ግን የክርስቲያኖች ችግራቸውን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ የራሳቸውን ጉዳይ መፍታት እንዳቃታቸው ያመለክታል። ክርስቲያኖች በመካከላቸው ያለውን ጉዳይ መፍታት ካልቻሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ አለባቸው

(1ኛ ቆሮ. 6፡1–8፤ ማቴ. 18፡17)። ጳውሎስ «ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን?» ይላል። ይህም የሚፈጸመው በአሁኑ ሕይወት ሳይሆን በሚመጣው ሕይወት ነው።

## 6. መለኮታዊ ፍቅር

መለኮታዊ ፍቅርን የሚገልጸው የግሪክ ቃል በዚያን ዘመን ግሪኮች እምብዛም አይጠቀሙበትም ነበር፤ ክርስቲያኖች ግን ፍቅር ለሚለው የራሳቸው ቃል አድርገው ተጠቅመውበታል። ይህ መለኮታዊ ፍቅር የክርስቲያኖች ባሕርይ መለያ ነጥብ መሆን ይገባዋል። ይህ ፍቅር ለማይገባቸው ሰዎች የሚሰጥ ነው (ሮሜ 5፡8)።

አማንያን የሚቀበሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን መጠናከርና ዕድገት እንዲጠቀሙበት የሚሰጥ ነው፤ ሆኖም በመለኮታዊ ፍቅር መንፈስ ካልተጠቀሙበት ዋጋ አይኖረውም። የዚህ የመለኮታዊ ፍቅር ባሕርያት በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነዚህም ባሕርያት በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መታየት ያለባቸው መልካም ባሕርያት ናቸው። ይህ የፍቅር ዓይነት የሚሰጠው መጠነኛ አገልግሎት እንኳ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ዋጋ አለው (1ኛ ቆሮ. 13፡4–9)። ይህ መለኮታዊ ፍቅር ለክርስትና ሕይወት በሙሉ መሠረት ነው።

ይህን የመሰለውን ፍቅር በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲኖር ጳውሎስ ይመክራል። ይህን ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ለተቀጣውና ንስሐ ለገባው ሰውዬ ማሳየት ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ የቆሮንቶስ ምእመናን ሰውየውን ባለመቅጣታቸው ኃጢአትን ሠሩ (1ኛ ቆሮ. 5)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በደለኛው ሰው ንስሐ በገባ ጊዜ ፍቅር አላሳዩትም፤ ይቅርታ ባለማድረጋቸውም በደለኞች ነበሩ (2ኛ ቆሮ. 2)። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የሰጠው ምክር፡– ጠንካራ ሆኖ መገሠጽ በኋላም በፍቅር ማብረድ እንደሚያስፈልግ ነው።

## 7. ክርስቲያናዊ አገልግሎት

ጳውሎስ የሮሜን መልእክት በጻፈበት ወቅት በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ እንደነበረ ይመስላል። ወደ ሮም ለመሄድ ቢፈልግም እንቅፋቶች አጋጠሙት። በእስያና በግሪክ የነበረው አገልግሎት እንዳበቃ ስለተገነዘበ ወደ ሮምና ወደ እስፓኝ ለመሄድ ዐቀደ (ሮሜ. 15፡22–24)። ጳውሎስ በቅድሚያ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ስለ ተነሣና በኢየሩሳሌምም ምን እንደሚያጋጥመው ስላላወቀ ለሮም ሰዎች የክርስትናን እምነት መግለጫ ሊልክላቸው ወሰነ።

በሮሜ 12 ጳውሎስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት እንደሚጠቅም ገልጿል። መንፈስ ቅዱስ ሥራውን በውስጣችን የሚጀምረው ሥጋችን በፈቃደኝነት ጌታ ለአገልግሎቱ እንዲጠቀምበት አሳልፈን ስንሰጥ ነው። ራሳችንን በማዋረድና እያንዳንዳችን የተቀበልነው ስጦታ የተለያየ ቢሆንም የአንዱ አካል አባሎች መሆናችንን ማወቅ፥ በተሰጠንም ስጦታና ችሎታ ማገልገል አለብን።

በአጠገባችን ላሉት ክርስቲያኖች የምንሰጠው አገልግሎት በፍቅር የታጀበ መሆን አለበት። እንዲሁም በትጋት፥ በደስታ፥ በትዕግሥት፥ እስከመጨረሻው በመጽናት፥ በጸሎት፥ እንግዳን በመቀበል እና የሌሎችን ችግር በመካፈል ልናገለግል ይገባናል (ሮሜ 12፡3–8)።

በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ የሆኑትን ጳውሎስ እንደሚለው፡- በደስታቸውና በኀዘናቸው ልንካፈል፥ ከእነርሱ ጋር በሰላም ልንኖር፥ በክፉ ፋንታ ክፉን ሳንመልስ ብቀላን ለእግዚአብሔር ልንተው ይገባል። ጠላቶቻችንንም በመልካም ሁኔታ ልንቀበላቸውና ክፋታቸውንም በመልካም ልናሸንፍ ይገባናል (ሮሜ 12፡17–21)።

## 8. ኅብረት፥ ራስን ማዋረድ፥ መታዘዝ

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ፡-

ሀ/ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ እርሱን ለመርዳት ስለላኩለት ስጦታ አመሰገናቸው (ፊልጵ. 4፡10፥ 14–18)፤

ለ/ በእርሱ መታሰር የወንጌል ስርጭት ሊቋረጥ እንዳልቻለ በማሳወቅ አጽናናቸው (ፊልጵ. 1፡12)፤

ሐ/ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከፋፈል እንዳለ ስለሰማ በኅብረትና በአንድነት እንዲሠሩና አንድ አሳብ እዲኖራቸው ምክር ሰጣቸው (ፊልጵ. 2፡1–2)።

የእግዚአብሔርን ፍቅርና በረከትን የሚያውቁት ራሳቸውን በማዋረድ ለሌሎች ማካፈል ይገባቸዋል። ክርስቶስ ራሱን በማወረድ ምሳሌያችን ሆኖልናል። የሰውን አካል ከውስንነቱ ጋር በመልበስ ተዋርዶ እስከ መስቀል ሞት ደርሷል። ሆኖም ክርስቶስ በክብር ከፍ ከፍ ብሏል፤ ጕልበት ሁሉ የሚሰግድለትና ምላስም ሁሉ ጌታ መሆኑን የሚመሰርክለት ቀን ይመጣል (ፊልጵ. 2፡5–11)።

## 9. የክርስትና ኑሮ መመርያ

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች መልእክቱን ሲጽፍ በዚያም ጊዜ ለቈላስይስ ሰዎች መልእክት ጻፈ። ለቈላስይስ በጻፈው በዚህ መልእክቱ «አሮጌውን አስወግዱ፥ አዲሱን ልበሱ» የሚል ክርስቲያኖች መፈጸም ያለባቸውን ሁለት ጠቃሚ እውነቶች አስፍሯል። ፍቅር «ከሁሉም በላይ» ተብሏል፤ የኅብረትንም አስፈላጊነት አጠንክሮ ገልጾታል። እነዚህ አስፈላጊና ጥራት ያላቸው ነገሮች ቃሉን ከማወቅ፥ በኅብረት ከሚገኘው አንድነትና ከምስጋና መንፈስ ይገኛሉ (ቈላ. 3፡5–17 በጥንቃቄ አንብብ)።

ጳውሎስ ለክርስቲያኖች ኑሮ መመሪያ ከሰጠ በኋላ አሳቡን በመቀጠል በባልና ሚስት መካከል፥ በልጆችና በወላጆች መካከል፥ እንዲሁም ከሠራተኛ ጋር ቤተሰቡ ስለሚኖረው ግንኙነትና ኅብረት በሚመለከት ግልጽ የሆነ ምክር ሰጣቸው (ቈላ. 3፡18–25)።

## 10. በዓለም ወስጥ የክርስቲያን መመላለስ

ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎችም የጻፈው መልእክት ከእስር ቤት ሲሆን ዐቢይ ትምህርቱም ክርቲያኖች በዓለም ውስጥ እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው የሚያስረዳ ነው። የጳውሎስ የመጀመሪያና ተደጋጋሚ ትእዛዝ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆናችሁ «በፍቅር ተመላለሱ» የሚል ነበረ። በክርስቶስም አርአያነት እንዲመሩ ነው (ኤፌ. 5፡1–3)።

ጳውሎስ በሌሎቹ የእስር ቤት መልእክት እንዳስረዳው ሁሉ ስለ ኅብረት ወይም አንድነት ጻፈላቸው። ክርስቲያኖችን ለዓለም ምስክርነት ለመስጠት የሚያበቁአቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ፍቅርና አንድነት ናቸው።

የአማኞች ዓላማ በሁሉም መንገድ ክርስቶስን ማስደሰት ነው (ኤፌ. 5፡10፤ ቈላ. 3፡17)። ክርስቶስን ማስደሰት አንዳንድ ሕጎችን ከመጠበቅ የተለየ ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለማቋረጥ የክርስቶስን ፈቃድ ለማወቅ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው። ይህ ማለት በየዕለቱ ለሚኖረን ባሕርይና በየዕለቱ የምንጠቀምበትን ጊዜ ለእርሱ ክብር እንዲውል ወደ ጥበቡ መቅረብ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን እንዲገዛና የማያቋርጥ ምስጋና ለጌታ የምናቀርብበትን መንፈስ እንዲሰጠን መፍቀድ ነው (ኤፌሶን 5፡11–20)።

የቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስና ለበላይነቱ መታዘዝ ሚስት ከባሏ ጋር ለሚኖራት ግንኙነት ትክክለኛ ምሳሌ ነው። ባል የቤተሰቡ ራስ

እንዲሆን በእግዚአብሔር የተቀባ ነውና። ይህም በፊቃደኝነት ለጌታ የሚሰጥ መለኮታዊ የሆነ ፍቅር ነው (ኤፌ. 5፡23-31)።

## 11. የጌታ አገልጋይ በሥሩ ካለው ተገልጋይ ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት

ጳውሎስ በኤፌሶን ለሚያገለግለው ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት ወደ ስሕተት ሊመራው ከሚችል በአካባቢው ከሚገኝ አንዳንድ ተግባር ራሱን እንዲለይ መከረው። እንደ ወንጌል አገልጋይ እውነትን በሕዝቡ ዘንድ መጠበቅና በሕይወቱም ምሳሌ ለመሆን ጠንቃቃ መሆን እንዳለበት መከረው። ጢሞቴዎስ ወጣት እንደመሆኑ መጠን ሽማግሌዎችና አሮጊቶችን መቈጣት እንደማይኖርበት ይልቁንም እንደ እናትና እንደ አባት እንዲጠነቀቅላቸው አሳሰበው። በተለይም ወጣት ልጃገረዶችን በሚመለከት አግባብ ያልሆነ አሳብ እንዳያቀርብ በጣም መጠንቀቅ እንደሚኖርበት ጻፈለት (1ኛ ጢ.ሞ. 5፡1-2)። ጳውሎስ ሲጽፍለት «በሚገባ የሚያገለግሉትን ሽማግሌዎች አክብር፥ ከሁለት ወይም ከሦስት ምስክር በቀር በሽማግሌዎች ላይ ክስ አትቀበል። በማንም ላይ አድልዎ አታድርግ፥ በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን። ራስህን በንጽህና ጠብቅ» ብሎታል (1ኛ ጢ.ሞ. 5፡17-25)።

## 12. ለባልቴቶች መጠንቀቅ

ቢቻል ባልቴቶች ልጆቻቸው ወይም ቤተሰባቸው ጥንቃቄ ሊያድርጉላቸው ይገባል። ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ፥ መልካም ምስክርነት ያላቸውና ለጌታ ታማኝ የሆኑ ባልቴቶች በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት ከቤት ወደቤት እየተዘዋወሩ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ወጣትነት ያላቸው ሴቶች ግን እንደገና አግብተው የቤተሰብና እንግዳን የመቀበል ኃላፊነት ቢወስዱ የተሻለ ነው (1ኛ ጢ.ሞ. 5)።

## 13. ሠራተኞችና አሠሪዎች

ሠራተኞች አሠሪዎቻቸውን እንዲያከብሩ ጳውሎስ ይመክራል። ክርስቲያኖች የሆኑት ማስታወስ የሚገባቸው በጌታ ወንድሞች መሆናቸውን ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ጢ.ሞ. 6፡1-5 የሚገኘውን በሚጽፍበት ጊዜ የባሪያና የጌታን ሥርዓት ለመደገፍ ሳይሆን በዘመኑ በነበረው ሥርዓት ባሪያዎች እንዴት መመላለስ እንደነበረባቸው ለመግለጽ ነው።

## 14. ስለ ሀብት ሊኖረን የሚገባ አመለካከት

ብዙዎች እውነትን በማጣመም እግዚአብሔርን የመምሰል ኑሮ ለቍሳዊ ጥቅም እንደሆነ አድርገው ስለሚያስተምሩ ጳውሎስ የማስተማር አገልግሎት በትክክለኛ መንፈስ መሆን እንደሚኖርበት አስጠነቀቀ። እውነተኛ ሃይማኖት ያለው ሰው ስግብግብ ሳይሆን ጌታ በሰጠው ደስ ይለዋል። እውነተኛ እግዚአብሔርን መምሰል የሚሰጠው ጥቅም መንፈሳዊ እንጂ፥ ለዚህ ላለንበት ሕይወት ማለትም ለጊዜያዊው ቍሳዊ ጥቅም አይደለም። የክርስቲያን አእምሮ ሀብትን በማከማቸት ላይ ማተኮር የለበትም፤ ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር አሳቡን ከጌታ እንዲያነሣና ሌሎች ተጨማሪ ኀዘኖችም ወደ አሳቡ እንዲመጡ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ በመጀመሪያ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖረውና በክርስቶስ የዘለዓለም ሽልማት ለመቀበል በሚችልበት መንገድ አእምሮውን በእግዚአብሔር አሳብ መሙላት አለበት።

## 15. ክርስቲያንና ባለ ሥልጣኖች

ክርስቲያን መልካምና ታዛዥ፥ በጥሩ ሥራ ሁሉ ንቁ ተሳታፊ የሚያደርግ ዜጋ መሆን አለበት። ስለ ሌሎች ክፉ የማይናገር፥ ከጸብ የሚርቅ፥ አስተዋይና ከሁሉም ጋር በሰላም የሚኖር፥ እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠውን ጸጋና ምሕረት የሚያስብ መሆን አለበት።

### ማጠቃለያ

በጳውሎስ ትምህርት መሠረት የክርስቲያን ሥነ-ምግባር ማንኛውንም የክርስቲያን ሕይወት የሚመለከት ነው። መመዘኛውም የክርስቶስ ፍጹም ቅድስና ነው። ክርስቶስ ክርስቲያኖችን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቃቸው ቅዱስ፥ ያለነቀፋና ያለነውር ሆነው ለእግዚአብሔር ሊያቀርባቸው ብሎ ነው (ኤፌ. 1፡22)። ክርስቲያን የሚፈረድበት በውጫዊ ተግባር ሳይሆን በውስጣዊ ሕይወቱና በግብረገባዊ ባሕርዩ ነው። ክርስቲያን ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ባስገዛና ትእዛዙን ለመጠበቅ ፈቃደኛ በሆነ መጠን ለቅድስና ሕይወት የሚያበቃው ኃይል ይሰጠዋል።

### ጥያቄዎች

1. ከአይሁድ ወገን ያመኑት ክርስቲያኖች ራሳቸውን ከታሰሩበት ወጥመድ ለማላቀቅ ተቸግረዋል፤ ታዲያ ይህ የታሰሩበት ወጥመድ ምንድን ነው? (ገላ. 5፡1-7።)

2. የክርስቲያኖችን ሥነ-ምግባር ከሮማውያንና ከግሪክ ኅብረተሰብ ሥነ-ምግባር ጋር አወዳድር። በጉልበት ሥራ ላይ የነበራቸው አመለካከት ምን ነበር? ስለ ዝሙትስ?

3. ክርስቲያኖች ከመንግሥት ፍርድ ቤት ይልቅ ልዩነታቸውን ራሳቸው ማስወገድ ያለባቸው ለምንድን ነው?

4. የመንፈስ ስጦታ የሚሰጥበት ዓላማው ምንድን ነው? (ኤፌ.4፡11-13።)

5. ክርስቶስና ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ለዓለም ምስክርነት እንዲሰጡ የሚያደርጉትን ሁለት ነገሮች አጥብቀው ተናግረዋል፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን ምን ናቸው? ዮሐንስ 13፡35ን ከኤፌ. 5፡21፤ ደግሞም ዮሐንስ 17፡20-21ን ከኤፌሶን 4፡3 ጋር በማገናዘብ አንብቡ።

# ትምህርት 16

## የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

የትምህርቱ ዓላማ፡- ቤተ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ግለሰቦች አገልግሎታቸውን ለዓለም እንዴት እንደሚሰጡ እንድንረዳ ነው።

### መግቢያ

እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠሩለት ያቋቋማቸው ሁለት ብቸኛ ድርጅቶች ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን ናቸው። በዕቅዱ ውስጥ ሌሎች ድርጅቶችንም አስገብቶ ቢጠቀምባቸውም ለዓለም ተቀዳሚና ዋንኛ ምስክሮቹ ግን ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ስሕተት ላይ ብትወድቅ ወይም ዓለማዊነት ቢታይባትም እንኳ ክርስቶስ በእርስዋ ውስጥ ለመጠቀም ይፈልጋል (ራእይ 2ና 3)።

### 1. ስደት ቀጠለ

ከ35-45 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ያለችው ቤተ ክርስቲያን በስደት ላይ ነበረች (ሐዋ. 12፡1-5)። የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ተገደለ፤ ጴጥሮስም ታስሮ ነበር። የአይሁድና የሮም ባለሥልጣኖች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማጥፋት ተባብረው ተነሥተው ነበር። ደቀ መዛሙርት በብዙ ተቃውሞ ውስጥ ምስክርነታቸውንና ሥራቸውን ያከናውኑ ነበር (የሐዋ. 12፡6-9)። እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ጴጥሮስን ከእስር አስፈታው፤ በሄሮድስ ሞትም ለቤተ ክርስቲያን ተዋጋላት (የሐዋ. 12፡20-25)። ከ15 ዓመት በኋላ ማለት በ52 ዓ.ም ጳውሎስ በሁለተኛው ወንጌላዊው ጉዞ እንኳ ወደ ቆሮንቶስ ምኩራብ በመሄድ

ለአይሁድ ወንጌልን ያዳርስ ነበር (የሐዋ. 18፥1-17)። ሆኖም የአይሁድ አመለካከት አልተለወጠም ነበር። አይሁድ በምኩራብ በተቃወሙት ጊዜ ምኩራቡን ትቶ ኢዮስጦስ ወደሚባል ሰው ቤት ገብቶ በዚያ ያስተምር ነበር። የምኩራብ አለቃ ቀርስጶስና ብዙ ሌሎች የቆሮንቶስ ሰዎች በጌታ አመኑ፤ ተጠመቁም። ቀርስጶስ ካመነ በኋላ የምኩራቡ አለቃ ሆኖ የተሾመው ሶስቴንስ ተደበደበ፤ በኋላ ግን ይህ ሰውም እንዳመነ በ1ኛ ቆሮ. 1፥1 በግልጽ እናገኛለን።

በዚህ ጊዜ የአይሁድ ወገን የሆነው አጵሎስ ከእስክንድሪያ ወደ ቆሮንቶስ መጣ። እርሱም ጐበዝ ተናጋሪ ከመሆኑም በላይ መጻሕፍትን በደምብ የሚያውቅ ነበር። እርሱም የዓቅሙን ያህል የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ያስተምር ነበር፤ አቂላና ጵርስቅላ ግን ስለ ኢየሱስ በበለጠ አብራርተው በሰፊው አስረዱት። አጵሎስና ሌሎች አማኞች ማለትም እንደ ጢሞቴዎስና ቲቶ ያሉት እየዞሩ ቃሉን ያስተምሩ ነበር።

ጳውሎስ በሦስተኛ ወንጌላዊ ጉዞው መጀመሪያ ላይ በኤፌሶን ሦስት ዓመታት ያህል ተቀመጠ (የሐዋ. 19፥1-10)። ከኤፌሶን ጀምሮ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እስያ በመስፋፋቱ አይሁዶችና ግሪኮች ቃሉን ሰሙ። እግዚአብሔር በጳውሎስ በመጠቀሙ ብዙ ተአምራት ተፈጸሙ፤ ሆኖም፥ ጳውሎስ ከርኩሳን መናፍስት ጋር ብዙ ውጊያ ነበረበት (የሐዋ. 19፥11-20)። የክርስትና እምነት ከግሪኮች ሃይማኖት ጋር በመቃረኑ ብጥብጥ ተነሣ፤ በዚህ ጊዜ ግን የሮም መንግሥት ለጳውሎስ መከታ ሆነው (የሐዋ. 19፥23-24)።

ስለሆነም በስደት ውስጥ በመስበኩ፥ በማስተማሩና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቤተ ክርስቲያን በእስያና በአውሮፓ እየተስፋፋችና እያደገች መጣች።

## 2. የተለዩ በመሆን መመስከር

በኃጢአት በተሞላች በአረመኔዎች ዓለም ክርስቲያኖች ተደበደቡ፤ ታሰሩ፤ እንዲሁም ዓመፅ ፈጠራችሁ በመባል ተከሰሱ፤ ሆኖም በሥነ-ምግባራዊ ሕይወታቸው ያለው ልዩነት ጐልቶ የሚታይ ነበር። በውስጣቸው ባለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከፍተኛ የሕይወት አቋም ነበራቸው፤ ይህም ለመንግሥታዊ አስተዳደር እንዲታዘዙ፥ ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ታማኞች እንዲሆኑና ለጐረቤቶቻቸው ፍቅርን እንዲያሳዩ አድርጎአቸዋል (ሮሜ 13)።

ምንም እንኳ ከእያንዳንዱ የአሕዛብ ባህል መለየት ቀላል ቢሆንም በሌላ መንገድ ሲታይ ለክርስቲያኖች መሰናከያና ለማያምኑት ሰዎች

ዕንቅፋት ሆኑ (ሮሜ 14)። ክርስትና አዲስ ነፃነትን አምጥቷል፤ ያም ነፃነት ገደብ አለው። ከገበያ ሥጋ ገዝቶ መብላትን ወይም በማያምኑ አሕዛብ ግብዣ መሣተፍን በሚመለከት ክርስቲያኖች ነፃነት አላቸው፤ ነገር ግን ያ ነፃነት በክርስቲያናዊ ፍቅር መገዛትና መመራት አለበት። ሌላውን የሚያሰናክል ወይም የሚያስቀይም ከሆነ ማድረግ አይኖርብንም።

የክርስትና ሕይወት ዓላማ ሌሎችን ማገልገል ነው እንጂ የግል ጥቅም መፈለግ አይደለም (1ኛቆር. 14)።

የክርስትና አምልኮ ከማያምኑ አሕዛብ አምልኮ የተለየ በመሆኑ ራሱ አንድ ምስክርነት ነበረ። ሆኖም የቆሮንቶስ ክርስቲያን ሴቶች የቀድሞውን ባህላቸውን በማንቋሸሽ ምስክሮች አልሆኑም (1ኛ ቆር. 11:1–16)። የጌታን እራት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ቤተ ክርስቲያን በስሕተት ወድቃ ነበር። የጌታን እራት ለእነርሱ ሲል ለሞተው ጌታ መታሰቢያ ማድረጋቸውን ትተው ስስትነት ያለበት ግብዣ አድርገውት ነበር (1ኛ ቆር. 11:17–34)።

የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ አንዱ ሌላውን በፍቅር ማገልገልና የሚያደርጉትን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግ ነው።

## 3. በቤተሰብ ኑሮ የሚሰጥ ምስክርነት

ክርስቲያኖች በአካባቢያቸው ከሚገኘው ከማያምን ኅብረተሰብ ልዩ የሚያደርጋቸው አዲስ የሆነው የክርስቲያኖቹ የቤተሰብ ኑሮ ነበር (ኤፌ. 6:1–9፤ ቈላስይስ 4:1–6)።

እነ ጳውሎስና በርናባስ በግለሰብ ደረጃ የሚሰጡት ምስክርነት አስፈላጊ ነበር። ክርስቲያኖች በአንድነትም ምስክሮች ነበሩ፤ አሁንም መሆን አለባቸው። ሆኖም የክርስቲያን ቤተሰቦች ለቤት ሠራተኞቻቸው በሚያደርጉት ጥንቃቄ የሚሰጡት ምስክርነት እንኳ በሚኖሩበት አካባቢ ላለው ኅብረተሰብ አዲስ ነገር ነበር።

ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ የሚያጋጥማት ግጭት ሁሉ መንፈሳዊ ውጊያ ነው። ከሰዎች ኃይል ጋር የሚካሄድ ትግል ሳይሆን ከአጋንንት ኃይላት ጋር ነው።

## 4. ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰብ ውስጥ

ለአስተዳዳሪዎችና ለባለሥልጣኖች በመጸለይ ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ አገልግሎቷን ትሰጣለች። በኅብረተሰቡ መካከል ሰላምን ለማምጣት ትጥራለች፤ ሁሉም በሰላምና በታማኝነት እንዲኖሩ ትጸልያለች (1ኛ ጢሞ. 2)።

ቤተ ክርስቲያን ለሴቶች በተለይ ታስብላቸዋለች (1ኛ ጢሞ. 2፡9–15)። ጳውሎስ ሴቶችን ይጨቍናል ተብሎ ብዙ ጊዜ ይነቀፍ ነበር፤ ሆኖም ጠለቅ ተብሎ ሲጠና ጳውሎስ ሴቶችን እንደሚያከብር እንመለከታለን። ወንዶችንና ሴቶችን በእኩልነት ይመለከታል (ገላ. 3፡23)። በማያምኑ አሕዛብና በአይሁዶች ዘንድ ሴቶች እንደ ዕቃ ይታዩ ነበር፤ አሁን ግን ከወንዶች እኩል የቤተ ክርስቲያን አካል ሆነዋል። ሴቶቹ በወንጌል አገልግሎት ከጳውሎስ ጋር ሠርተዋል፤ እነርሱም፡– ጵርስቅላ (የሐዋ. 18፡18–27)፥ ማርያም (ሮሜ 16፡16)፥ ፕሮፌሞናና ጢሮፌሞስ (ሮሜ 16፡12) ምናልባት እኅትማማቾች ይሆናሉና ፌቤን (ሮሜ 16፡1–2) ናቸው። ሴቶች በቤተ ክርስቲያን አምልኮና በጌታ እራት ሥነ–ሥርዓት ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው ጳውሎስ ያምናል (1ኛ ቆሮ. 11፡5)። ሴቶች የሚጫወቱት ሚናና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስላላቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊጠቀሙት ይገባቸዋል።

የክርስትና ሕይወት አኗኗር ዘይቤ በአካባቢው ላለው ኅብረተሰብ ሙሉ በሙሉ አዲስ ነበር፤ ነገር ግን ይህ የአኗኗር ዘይቤ በአብርሃም ዘመን የተለመደ ነበር።

ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉትን እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ቤተ ክርስቲያን ተቀብላለች (2ኛ ጢሞ.3፡16–17)። ክርስቲያኖች በሕይወትም ሆኑ በሞት በእምነት ይኖራሉ (ዕብ. 11)። ይህም የቤተ ክርስቲያን ኃይልና መሠረት ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ያሳያል።

## ማጠቃለያ

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚካሄደው በመከራ ውስጥ፥ ከማያምኑ አሕዛብ መጥፎ ባህል በመለየት፥ በሴቶች እኩልነት፥ ለባለሥልጣኖች በሙሉ በመጸለይ፥ ለጐረቤቶቻቸው ፍቅርን በማሳየትና በአጠቃላይ በአዲስና በተለየ የአኗኗር ዘይቤ ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሠረት በመጀመሪያ በቃል የተላለፈ፥ ቀጥሎም በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት በጽሑፍ የሰፈረ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

## ጥያቄዎች

1. በኢየሩሳሌም የሚካሄደውን የወንጌል አገልግሎት የረዳው መለኮታዊ ሥራ ምን ነበር? (የሐዋ. 12፡20–25።)
2. ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ የምታገለግለው እንዴት ነው? (1ኛ ጢሞ. 2፡1–2።)

3. ጳውሎስን በአገልግሎቱ የረዱት የሦስት ሴቶችን ስም ጥቀስ።

4. እግዚአብሔር ሥራውን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው ሁለት ድርጅቶች ምንና ምን ናቸው?

# ትምህርት 17

## የቤተ ክርስቲያን ወደ ብስለት መድረስ

የትምህርቱ ዓላማ፦ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንዴት እንዳደገችና በድርጅታዊ አቋሟ በኩል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በአማኞቿ ሕይወት ውስጥ መሥራት ሲጀምሩ እንዴት እንደተስፋፋች ማየት እንድንችል ነው።

### መግቢያ

ስለ ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ አሠራር ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው መመሪያ የለም። ከበዓለ-ኀምሳ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ከእስራኤላዊ የአኗኗር ዘይቤ የመለየት ሐሳብ በአእምሮአቸው አልነበረም። የራሳቸው የሆነና የተለየ ድርጅት የማቋቋሙ አስፈላጊነት አልታያቸውም ነበር። በቤተ መቅደስ አምልኮ መካፈላቸውን አላቋረጡም፤ ሆኖም የኅብረት ጸሎትና የአንድነት ጊዜ እንዲሁም የጌታ እራት በአንድነት ይወስዱ ነበር።

የሥርዓት ሕግን በመጠበቅ ረገድ በክርስቲያኖችና በአይሁድ እምነት መካከል መራራቁ እየሰፋ ስለሄደና ለባልቴቶች ምግብን ለማደል ሐዋርያቱን የሚረዱቸው ሰዎች መምረጥ ስላስፈለገ አንድ ዓይነት ድርጅታዊ መዋቅር ማቈጥቈጥ ጀመረ (የሐዋ. 6፡2፥4)። በመጀመሪያ መሪዎቹና አስተማሪዎቹ ሐዋርያት ብቻ ነበሩ፤ እያደር ግን ቤተ ክርስቲያን በየአገሩ እየተስፋፋችና ብዙ ሰዎችም እያመኑ ሲመጡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሙሉ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መሥራታቸው አስፈላጊ ሆነ (ሮሜ 12፡1-8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡1-11፥ 28)። ይህም መሪዎችን፥ ማለትም ሽማግሌዎችን፥ ዲያቆናትንና አስተማሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን ወደ መምረጡ እንዲያመሩ አደረገ።

### 1. የወንጌል ምስክርነት መስፋፋት

በኢየሩሳሌም ካሉ አይሁዶች ጋር የተፈጠረው ግጭት ወንጌል የቱን ያህል መስፋፋት እንዳለበት ግልጽ ለማድረግ ረድቷል። ይኸውም ብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ መምጣት ምን እንደሚናገር ለማወቅ አይሁዶች አሳባቸውን ወደ ብሉይ ኪዳን መለሱ፤ ያም አሕዛብም በዚህ ውስጥ መጠቃለላቸውን እንዲያዩ አደረገ። ለዲያቆንነት የተመረጡት

ሰባቱ ሰዎች ወደ ግሪክ አገር ከተበተኑ አይሁዶች መካከል መሆናቸውን ከስማቸው መረዳት እንችላለን። ቤተ ክርስቲያን ልትስፋፋ የቻለችው በእነኚህ ሰዎች ምክንያት ነበረ፤ በተለይም በእስጢፋኖስና በፊልጶስ በኩል ነው። እስጢፋኖስ በስብከቱ ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መቅደስ አምልኮ የተለየ በጣም መንፈሳዊና አዲስ ይዘት ያለው አምልኮ እንደሚኖራት ይተነብያል (የሐዋ. 7፡47–53)። የአይሁዶችን አሳብ አነሣሥቶ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ለመግደል ያበቃቸውም ይህ ነበረ። ይህም በክርስቲያኖች ላይ የተደረገው ስደት መንሥኤ ሆነ።

ክርስቲያኖችም ከተማይቱን ለቅቀው በኢየሩሳሌም ዙሪያ ወዳሉት ከተሞች ተበተኑ። ይህ የክርስቲያኖች በይሁዳ፥ በሰማርያና በሌሎቹም አውራጃዎች መበተን ክርስቲያኖች ስለ ሌሎች ያለባቸውን ኃላፊነት በበለጠ እንዲረዱ አመለካከታቸውን አሰፋላቸው።

እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት የሚለውጠው በሰባኪዎች አፍ በሚነገረው ቃል ብቻ ሳይሆን ተአምራትንም በማሳየት አገልጋዮቹ ከእርሱ ጋር እንደ ታረቁ ይመሰክር ነበር (የሐዋ. 4)። በእግዚአብሔርና በኃይሉ ላይ ካላት እምነት የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በቁጥርም በሥልጣንም እያደገች ሄደች።

ጳውሎስ ገላትያን የጐበኘው በ47–48 ዓ.ም. ውስጥ ሳይሆን አይቀርም። በዚያም አንዳንድ አይሁድ ወንጌልን በማጣመም አሕዛብ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን ከፈለጉ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶችን መጠበቅ አለባቸው በማለት አስተማሩ። ይህም ጳውሎስን አስቈጣው። ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱም ከእምነት በፍጥነት እንዲህ መራቃቸውን በመጥቀስ ገሠጻቸው (ገላ. 1፡6–9፤ 6፡11–15)።

## 2. የቤተ ክርስቲያን ብስለት አራት መንገዶች

### ሀ. የቤተሰብ ኑሮ፥ እንዲሁም የሴቶች ድርሻ በኅብረተሰብ ውስጥና በቤተሰባቸው ውስጥ (1ኛ ቆሮ 7)።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻን በሚመለከት ረገድ ጳውሎስ እንዲያስረዳቸው በደብዳቤ ጠየቁ። ጥያቄአቸው ሊነሣ የቻለው በጋብቻ በተጣመሩ የግሪክ፥ የአይሁድና የሮም ሰዎች ሳይሆን አይቀርም። ለእነዚህ ስድስት ጥያቄዎች ጳውሎስ መልስ የሰጠው፥ ከጌታ ባገኘው ሐዋርያዊ መገለጥ ነው (1ኛ ቆሮ. 7፡40)፤ ወይም እርሱ እንደ ገለጸው፥ አንዳንድ አሳብ ከራሱ የመነጨ ነው። የሰዎች ጥሪና ስጦታ የተለያየ መሆኑን በመረዳቱ ጋብቻን በሚመለከት የእርሱ የግል ምርጫ የሁሉም መሆን እንደሌለበት ያስረዳል (1ኛ ቆሮ. 7፡7)።

ጳውሎስ አጥብቆ የሚገልጸው ያገቡትም ሆኑ ያላገቡት፥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በግላቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነትና ለእርሱ ስለመታዘዛቸው ነው። የሥራ ድርሻቸው ቢለያይም እንኳን ጳውሎስ ወንዶችንና ሴቶችን የሚመለከታቸው በእኩልነት ነው። የተጋቡ ሰዎች በጋብቻቸው እርስ በርስ ታማኞች መሆን አለባቸው። ያላገቡትን ግን እግዚአብሔር ሕይወታቸውን በመራው መንገድ ለመሄድ ምርጫ አላቸው።

ባላመኑ አሕዛብ ኅብረተሰብ ጋብቻ ደካማ ስለሆነ እንዲሁም በአይሁድ ኅብረተሰብ ውስጥ ማንኛውም ንብረት ከሴት ጭምር የባልየው ንብረት ስለሆነና ክርስቲያን ሴቶች በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ ያላቸው እኩልነት፥ የመምረጥ ነፃነትና ግልጽነት ለማያምነው ኅብረተሰብ አዲስ ከመሆኑም ሌላ አስደናቂ ምስክርነት ነበር።

## ለ. የክርስቲያን ነፃነትና ኃላፊነት (1ኛ ቆሮ. 8)።

ስለ ሥጋ መብላት የሚገልጸው አሮጌው ሥርዓት ከእንግዲህ ክርስቲያኖችን አያስራቸውም፤ ሆኖም የክርስቲያን ነፃነት ለሌሎቹ ዕንቅፋትና መሰናክል የሚሆን ከሆነ ሌሎችን የሚያስከፋ ከሆነ፥ የፍቅር ሕግ በነፃነቱ ላይ ይሠራል። (1ኛ ቆሮ. 8ን በጥንቃቄ አንብብ።)

## ሐ. በግሪክ አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ ስብሰባ (2ኛ ቆሮ. 8 እና 9)።

ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ክርስቲያኖች ገንዘብ መሰብሰብ የጀመረው አጋቦስ የተባለው ነቢይ ስለ ራብ መምጣት ከተናገረ በኋላ ነው (የሐዋ. 11፡27–30)።

መስጠት ለሚሰጡት ግለሰቦችና ለምትሰጠው ቤተ ክርስቲያን በረከትን የሚያመጣ ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን ጳውሎስ ያውቅ ነበር። ይሁን እንጂ ስጦታው መሰጠት ያለበት ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑና ራሳቸውንም አስቀድመው ለጌታ በሰጡ ሰዎች ነው (2ኛ ቆሮ. 9፡7፤ 8፡5፤ ሮሜ 12፡1–2)። ክርስቶስ በፈቃደኝነት ክብሩንና የራሱን ሕይወት በመስጠት ምሳሌያችን ነው (ፊልጵ. 2፡5–8)።

ለአሕዛብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርቲያን ባለዕዳዎች መሆናቸውን ጳውሎስ ያምናል። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ በረከት እንዳካፈለቻቸው ሁሉ እነርሱም ቁሳዊ ከሆነው ነገር ሊያካፍሏት ይገባል (ሮሜ 15፡27)። የሌላውን ችግር መካፈል የችግሩ ተካፋይ ለሚሆነው ሰው በረከትን ይሰጣል። ጳውሎስ የአሕዛብ ወገን የሆኑትን

ክርስቲያኖች ተቀባይነትም እንዲያገኙ የሚረዳቸው መሆኑን ያምናል (2ኛ ቆሮ.8፡13–15፥ 9፡12–15)።

እኛ በፈቃደኝነት ከሰጠን እግዚአብሔር በሌላ መንገዱ ለእኛም ይሰጠናል (2ኛ ቆሮ. 9፡6፥ 8፥10–11)።

## መ. በሮምና ከዚያም አልፎ ያሉትን አገሮች ወንጌልን ማዳረስ 58–61 ዓ.ም (ሮሜ 15፡13–33)።

የአሕዛብን ዓለም በወንጌል ለማዳረስ በተሰጠው ተልእኮ ላይ ጳውሎስ ጭራሽ አላወላወለም። እስከ እልዋሪቆን ድረስ በመሄድ ወንጌልን ሰብኮአል። የጳውሎስ ዓላማ ክርስቶስ ወደ አልተሰበከበት አካባቢ መሄድ ነበር። ሆኖም ጳውሎስ በዚህ ወቅት በእስያ፥ በመቄዶንያና በአካይያ የነበረውን አገልግሎት እንደጨረሰ ያምን ነበር። ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመጓዝ ወደ እስፓኝ ለመሄድና እግረ መንገዱን ሮም ያሉትን ክርስቲያኖች ለመጐብኘት ፈልጎ ነበር፤ ለመሄድም ዝግጁ ነበር። በቅድሚያ ግን የተሰበሰበውን የእርዳታ መዋጮ ለተቸገሩት የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ማድረስ ነበረበት (ሮሜ 15፡25)።

ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መከራ እንዲሚጠብቀው ያውቅ ነበር፥ በደረሰበትም ስፍራ ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ተነግሮታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ጳውሎስ በወሰነው ጊዜ ሮሜ እንደሚደርስ ሙሉ በሙሉ ተስፋ ያደርግ ነበር። በመጨረሻ በእስር ወደ ሮም ሄደ። በእስራቱ መካከል ከሮም ወደ እስፓኝ ሳይሄድ አልቀረም።

## 3. ትንቢት ተፈጸመ 62–67 ዓ.ም (የሐዋ. 28)።

ለጳውሎስ ቀደም ተብሎ እንደተነገረው በኢየሩሳሌም እስራት ጠበቀው (የሐዋ. 20፡23–24)። በቂሣርያ ለሁለት ዓመት ከታሰረ በኋላ እስረኛ ሆኖ እያለ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጉዞውን ጀመረ።

በጣም አደገኛ ከሆነ ጉዞ በኋላ ጳውሎስ ሮም ደረሰ (የሐዋ. 28፡16)። ምንም እንኳ በሮም የቁም እስረኛ ቢሆንም ጳውሎስ ከአይሁድ መሪዎች ጋር በመገናኘት ለምን ይግባኝ እንዳለና ወደ ሮም እንደመጣ ያስረዳቸው ነበር። በሐናንያ ትንቢት መሠረት ማለት ለአሕዛብና ለአይሁድ እንዲሁም ለነገሥታት ምስክር እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ስለሆነ ጳውሎስ በመጨረሻ ሮም ደረሰ። ጳውሎስ በቅድሚያ ወገኖቹ ለሚላቸው ለአይሁድ መሰከረ፤ አንዳንዶቹ አመኑ፤ ሌሎቹም ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም፤ ከዚያም ጳውሎስ ወደ አሕዛብ ዞረ (የሐዋ. 9፡15 ና 28፡23–31)።

ጳውሎስ ለሁለት ዓመት እየተፈራረቁ ለሚጠብቁት ወታደሮች ይመሰክር ነበር፤ ከዚህም ሌላ ወደ እርሱ ለሚመጡ ሁሉ ይመሰክር ነበር። ታሪክ እንደሚያመለክተው ጳውሎስ በእስሩ መካከል አንድ ዓመት ያህል ተፈትቶ ነበር። በዚያም ጊዜ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በድጋሚ ሲጐበኝ እንደ ዕቅዱ እስፓኝንም ሳይጐበኝ አልቀረም። ታሪክና አፈ–ታሪክ እንደሚነገረን ጳውሎስ የተገደለው ኔሮ ክርስቲያኖችን በሚያሳድድበት ወቅት ነበር። ስለዚህም ምናልባት ጳውሎስ ለኔሮ ሳይመሰክርለት አይቀርም፤ ይህም የተነገረለትን ለነገሥታትና ለገዢዎች ይመሰክራል የሚለው ትንቢት ፍጻሜ ነው።

ጳውሎስ በሮም ከአይሁድ ጋር ያደረገውን ግንኙነት አይሁድ በአጠቃላይ ወንጌልን ለመንቀፋቸው ሌላ ተጨማሪ እርምጃ ነበረ። ከዚህ ቀደም ክርስቶስ የጠቀሰውን ኢሳይያስ 6፡9–10ን ጳውሎስ በድጋሚ ሲጠቅስላቸው ምናልባት ለእነርሱ ያቀረበው የመጨረሻው ምስክርነት ይህ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም የዕብራውያን መልእክት የተጻፈላቸው ለእነኚሁ አይሁዶች ሳይሆን አይቀርም (ማርቆስ. 4፡12፤ ዮሐንስ 12፡39–40)።

## 4. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕድገት

ጢሞቴዎስ፤ ቲቶና ሌሎቹም በጳውሎስ ሠልጥነው የእስያና የቆጵሮስ አብያተ ክርስቲያናት አማካሪዎችና መሪዎች ሆኑ።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በጻፋቸው መልእክቶቹ ለአብያተ ክርስቲያናት ስለሰጠው አገልግሎት መመሪያ ሰጣቸው። እንዲህም ሲል አበረታታቸው፡–

ሀ/ ስሕተትን ተዋጉ (1ኛ ጢሞ. 4፡1–5)። እነዚህን ጥቅሶች አንብባችሁ ከአሁኑ ዘመን ሁኔታ ጋር አገናዝቧቸው።

ለ/ ትክክለኛ ትምህርት አቅርቡ (1ኛ ጢሞ 4፡6–10)።

ሐ/ ምሳሌነት ያለው ሕይወት ኑሩ (1ኛ ጢሞ 4፡11–16)።

መ/ ሥራው እንዲካሄድ አስፈላጊ ከሆነ መከራን ተቀበሉ (2ኛ ጢሞ. 2፤ ዕብ. 12፡1–15)።

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን ለመስፋፋት የበቃችው በስደት ውጤትና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በደቀ መዛሙርት ሕይወት ውስጥ በሠራው ውጤት ነው። ቤተ ክርስቲያን እያደገች በቤተሰብ መካከል ባለው ግንኙነት ስለ ሌሎች የኃላፊነት ሸክም በመቀበል ምሳሌ የሚሆን ሕይወት በመኖር፥

ችግረኞችን በመርዳትና ያልዳኑትን በወንጌል በማዳረስ ረገድ እየጐለመሰች መጣች።

## ጥያቄዎች

1. ቃሉ በሚሰበክበት ጊዜ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ይገልጽ ነበር። የተአምራቱ ዓላማ ምን ነበር? (የሐዋ. 4፡29–31።)

2. ምጽዋት መስጠትን በሚመለከት ጳውሎስ የሰጠው ሁለት መሪ አሳቦች ምን ምን ናቸው? (2ኛ ቆሮ. 8፡5፤ 8፡12፤ 9፡7።)

3. አሕዛብ በኢየሩሳሌም የሚገኙትን የአይሁድ ችግረኞችን መርዳት እንዳለባቸው ጳውሎስ ለምን አመነ? (ሮሜ 15፡27)

4. ወንጌልን በማዳረስ ረገድ የጳውሎስ ዓላማ ምን ነበር? (ሮሜ 15፡20።)

5. ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መከራ እንደሚጠብቀው እያወቀ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ አስፈላጊ ነው ብሎ ያሰበው ለምንድን ነው? (ሮሜ 15፡25–26።)

# ትምህርት 18

# መንፈስ ቅዱስና የወንጌል ስርጭት

የትምህርቱ ዓላማ፡– ለወንጌል ስርጭት፤ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ለእያንዳንዱ ግለሰብ የግል ሕይወትና ዕድገት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንድናውቅና እንድንታመንበትም ነው።

## መግቢያ

የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ እየደከመች ስትሄድ በእስያና በግሪክ ግን ክርስትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየበዛና እየተስፋፋ መሄዱን የሐዋርያት ሥራ ይገልጻል። ከማንኛውም አገር ወይም ቡድን ወይም መንግሥታት አስተዳደር ወይም ሃይማኖት ጋር ያልተያያዘ አዲስ ራእይ በታሪክ ውስጥ መከሠቱን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ገልጿል።

## 1. የቤተ ክርስቲያን አጀማመር

ሐዋርያት፥ የኢየሱስ እናትና የኢየሱስ ወንድሞች ከሌሎች 120 አማኞች ጋር ኢየሱስ ባዘዛቸው መሠረት ለጸሎት ተሰብስበው ነበር። መንፈስ ቅዱስ በሚታይና በሚሰማ ሁኔታ ወረደባቸው። በአካባቢው

የነበሩ ሰዎች እንዲሰሙ «የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በክርስቶስ የተደረገውን» በልሳኖቻቸው ተናገሩ (የሐዋ. 2፡5–13)።

የመንፈስ ቅዱስ መውረድ መጥምቁ ዮሐንስ አስቀድሞ የተነበየው ነበር (ሉቃስ 3፡15–16)። ኢየሱስ የሰጠው የተስፋ ቃል ፍጻሜ ነበር (ሉቃስ 24፡49)። ኢዩኤል የሰጠው የትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ጴጥሮስ ገለጸ (የሐዋ. 2፡16–21)። ጴጥሮስ ደግሞ የትንሣኤው ማረጋገጫ መሆኑንም ተናገረ (የሐዋ. 2፡32–36)።

የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በአማኞች መካከል ቀድሞ ያልነበረውን አንድነት ሰጣቸው፤ እንዲሁም ስደትን መቋቋም እንዲችሉ ድፍረትን ሰጣቸው (የሐዋ. 2፡4፤4፡8፥31–32፤6፡8–15)። ሐዋርያት ከስብከታቸውና ከማስተማራቸው የተነሣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ። በዚያን ጊዜ የጥንት ቤተ ክርስቲያን በጣም የተጠናከረ ድርጅታዊ አካል አልነበራትም።

## 2. ጥንታዊው ሐዋርያዊ መልእክት

የሐዋርያት ስብከት ፍጹም በብሉይ ኪዳን ላይ የተደገፈ ነበር። በዚያን ጊዜ አዲስ ኪዳን አልተጻፈም ነበር፤ ስብከታቸው ግን በብሉይ ኪዳን ጥቅስና ትንቢት የተሞላ ነበር። የመልእክታቸው ማዕከል የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፥ ማንነት፥ ሥራና ትንሣኤው ነበር። እንዲሁም ደግሞ ሰዎች እንዲመለሱና በስሙ እንዲያምኑ ወደ ንሥሐ ማቅረብ ነበር። ከሞት የተነሣውን ጌታ እንደ መሢሕ አድርገው መቀበል እንዳለባቸው፥ በግልና ግልጽ በሆነ መንገድ ንሥሐ፥ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን የመቀበል አስፈላጊነትን ይገልጹ ነበር (የሐዋ. 2፡14–40፤ 6፡8–7፡54)።

## 3. የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።

እስጢፋኖስ የእስራኤል ሕዝብ ክርስቶስን እንደ መሢሕ አድርጎ ያለመቀበሉን በግልጽ በተናገረ ጊዜ ከባድ ስደት በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ላይ ደረሰባት። አይሁዶች በጣም ከመናደዳቸው የተነሣ እስጢፋኖስን በሕጋዊ መንገድ ለፍርድ ሳያቀርቡት በድንጋይ ወግረው ገደሉት (የሐዋ. 7፡54–60)።

የእስጢፋኖስን መገደል ተከትሎ የመጣው ስደት ደቀ መዛሙርትን ከከተማ እንዲወጡ አደረጋቸው። ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ሄደ። በዚያ ያለውም ሕዝብ ድብልቅ ነገድ ነበር፤ በአይሁድም ዘንድ ተቀባይነት አላገኙም። አምልኮአቸውም ከአይሁድ የተለየና በአይሁድ ዘንድ የተጠላ ነበር። ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ሄዶ ማስተማሩ አይሁድን በጣም

አስገረማቸው፤ ፊልጶስ ግን ወንጌል ከአይሁድ ውጭም ለሆነ መዳረስ ያለበት መሆኑን ተረድቶ ነበር። ፊልጶስና ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት ይህንን ሊረዱ የቻሉት መንፈስ ቅዱስ ገልጾላቸው ነው።

በፊልጶስ ስብከት አማካይነት ሰማርያውያን ባዕድ አምልኮ ማመናቸውን ትተው በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። መንፈስ ቅዱስም በአይሁዶች ላይ እንደወረደባቸው በእነርሱም ላይ ወረደ። ጴጥሮስና ዮሐንስም ሰማርያን የጎበኙበት ምክንያት ሰማርያውያን መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ለማረጋገጥ ነበር (የሐዋ. 8፡1–17)።

## 4. አሕዛብ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ

ጳውሎስ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር (የሐዋ. 9፡15፤ 22፡21፤ 26፡17፤ ሮሜ 15፡16፤ ገላ. 1፡16፤ 2፡7–8 እና ኤፌ. 3፡1–7)። ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በሮም ወደ ነበሩት ቤተ ክርስቲያን መሸጋገሪያ የሆነው የጳውሎስ መለወጥ ነበር።

እግዚአብሔር በቆርኔሌዎስ አማካይነት ለጴጥሮስ በሰጠው መገለጥ በአሕዛብ ዘንድ የታቀደለትን አገልግሎት እንዲፈጽም ዝግጁ እንዲሆን አደረገው። ቆርኔሌዎስ የሮም መኮንን ሲሆን ኢየሱስን ለመቀበል የተዘጋጀና መንፈስ ቅዱስንም የተቀበለ ሰው ነበር። የጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት መመራት በጣም አስፈላጊ ነበር፤ ምክንያቱም ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ደኅንነትን የሰጠው ለአንዱ ነገድ ብቻ ያለመሆኑን ነው። እንዲሁም የቆርኔሌዎስ መለወጥ አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ በር ከፈተላቸው። ይህም በር ከሐዋርያት በአንዱ መከፈቱ አስፈላጊ ነበር። ይህ ለአሕዛብ የተደረገው የቤተ ክርስቲያን መከፈት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተካሄደ ሲሆን በቆርኔሌዎስና በሌሎቹም አሕዛብ ላይ መንፈስ ቅዱስ ልክ በአይሁድ ላይ እንደወረደ በመውረዱ አስመሰከሯል (የሐዋ. 10፡9፥ 43–44)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ «የመንፈስ ቅዱስ ሥራ» ቢባል የተሻለ ስም ነው።

## 5. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

የሐዋርያት ሥራ እንደሚያመለክተን የወንጌል ሥርጭት በኮሚቴና በኮንፍራንስ ከሚደረገው ዕቅድ ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በግለሰቦችና በቡድኖች ሕይወት ውስጥ የሚሠራ መሆኑን ያሳያል። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ በሁለቱም መንገዶች ይሠራል። የሚሠራውም ወንጌልን ለማስፋፋት ብቻ ሳይሆን አማኞችንም በእምነታቸው ለመገንባት ነው። አማኞች ሁሉ በክርስቲያኖች ስብሰባ በመሳተፍ እንዲያመልኩ የጳውሎስ ዕቅድ ነበር።

ኢየሱስ ጌታ መሆኑን በማስታወስ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማስተማር ጀመረ፤ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ኢየሱስን ጌታ እንደማይለው በመግለጹ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፥1–3)።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን አጠቃቀም በሚመለከት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለመግባባት ነበረ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመቀበልም የሚደረገው ፉክክር ቤተ ክርስቲያኒቱን ከፋፈላት።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለፉክክር ወይም ለመቀናናት ሳይሆን ለአካሉ ሁሉ ጥቅም ነው። አባላት ሁሉ እንደ አንድ አካል በመሆን አንዱ ከሌላው ጋር መሥራት አለበት፤ የጠቅላላው አካል ክፍል በመሆን መሥራት ያስፈልጋል።

ስጦታዎቹ በቆሮንቶስ ለሚገኝ ቡድን ለዕድገትና ለብርታቱ ቢሰጥም ያለአግባብ ተጠቀመበት፤ ከዚህ የተነሣ አለመግባባትና መለያየት ተፈጠረ።

እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል የሆኑት አባላት ሁሉ፥ ከመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ኃይል ሰጭነት ውጭ፥ ለመንቀሳቀስ ነፃ እንዳልሆኑ ማስታወስ ይኖርባቸዋል (1ኛ ቆሮ.12፥4–31)።

## 6. ለቅዱሳን መዋጮዎችን መሰብሰብ

የማኅበሩ አባላት እርስ በርሳቸው መረዳዳታቸው በቂ ክርስቲያናዊ ሥነ–ምግባር አይደለም። እያንዳንዱ ማኅበር በመስበክ ብቻ ሳይሆን በሌላ ስፍራ የሚገኙትን ክርስቲያኖችንም ሆነ ክርስቲያን ያልሆኑትን በቁሳዊ ርዳታ ማገልገል ይኖርበታል።

ይኸኛውን የወንጌል ስርጭት ክፍል ያስተዋወቀው ጳውሎስ ሲሆን፥ ለቅዱሳን ገንዘብ ይዋጣ በማለቱ ብዙ ችግሮችና ያለመግባባት ፈጥሮበታል (1ኛ ቆሮ. 16፥1–4)። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በመሠረተበት ስፍራ ሁሉ በይሁዳ በተነሣው ከባድ ድርቅ ምክንያት በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚሠቃዩትን አማኞች እንድትረዳ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያበረታታ ነበር። ይህ መንገድ አሕዛብን ከአይሁድ ጋር እንዲተሳሰሩ ያደርጋል ብሎ ጳውሎስ ሳያምን አልቀረም። ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ የተሰበሰበውን ገንዘብ እንዲያስረክቡ ከየቤተ ክርስቲያኖቹ አንዳንድ ተወካዮችን አስከትሎ ነበር (ሮሜ 15፥25–28)። ጳውሎስ ምንም እንኳ እንዳይሄድ ብዙዎቹ ቢያስጠነቅቁትና ራሱም ምን ክፉ ነገር እንደሚያጋጥመው እርግጠኛ ባይሆንም፥ በሦስተኛ ወንጌላዊ ጉዞው መጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም

የሄደበት ምክንያት ይህንን ስጦታ ለማስረከብ ነበር (የሐዋ. 20፡22፥ 35–38 አንብብ)።

ማንም ሰው የተሰበሰበውን ገንዘብ ለእርሱ እንደተጠቀመበት አድርገው እንዳይጠረጥሩ፥ ጳውሎስ የራሱን ኑሮ በራሱ ሥራ በሚያገኘው ገንዘብ ይሠራ ነበር (የሐዋ. 20፡33–34)።

በ56–57 ዓ.ም. ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን ሲጽፍ ሁለት ዓይነት ቡድኖች በአእምሮው ሳይኖሩ አልቀሩም። ከምዕራፍ 1–9 የጻፈው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አሳባቸውን ለውጠው የጳውሎስን ሐዋርያዊ ሥልጣን ለተቀበሉት ነው።

ከምዕራፍ 10–13 ደግሞ የጳውሎስን ሐዋርያዊ ሥልጣን የመጠቀምን ተገቢነት ለሚጠራጠሩ የተጻፈ ነው። በምዕራፍ 12 ውስጥ በተሰጠው ነገርና ለጌታ ሲል በተቀበለው መከራ ያለውን ሥልጣን ያረጋግጥላቸዋል።

## 7. ከሕግ መዳን የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ጳውሎስ በሮም ለሚገኙት ክርስቲያኖች በስፋት በጻፈላቸው የእምነት መግለጫ ላይ ከክርስቶስ ጋር ባለው አዲስ መንፈሳዊ ግንኙነት ምክንያት ያጋጠመውን አንዳንድ የግል ችግሮች የሚመለከት ነው። «ሕግ ኃጢአት ነውን?» እና «ከዚህ ከሚሞት ሥጋ ማን ያድነኛል?» የሚሉት ጥያቄዎች በሮሜ 7ና 8 ውስጥ ከሚገኙት ጥያቄዎች መካከል ሁለቱ ናቸው። ጥያቄውን ለመመለስ ጳውሎስ ለራሱ ያጋጠሙትን ነገሮች ተጠቀመ። ሕግ ኃጢአት ነውን? የኦሪት ሕግ ኃጢአትን ያስታውቃል፤ እንዲያውም ኃጢአትን ይቀሰቅሳል (ሮሜ 7፡7–8)። ጳውሎስ ሕግን ሲያውቅ ኃጢአተኛነቱን ተረዳ፤ ከዚያም ሕግ እስከ ሞት ኮነነው፤ ምክንያቱም ጳውሎስ የሕግን ደረጃ ለመጠበቅ ስላልቻለና ስላልጠበቀም ነው። ይህም በመንፈስና በሥጋ መካከል ያለ ውጊያ ነው። ይህንንም ማወቁ ጳውሎስን «ከዚህ ከሚሞት ሥጋ ማን ያድነኛል?» ብሎ ወደሚጠይቅበትና ወደሚገነዘብበት ሁኔታ አደረሰው (ሮሜ 7፡15–24)። ጳውሎስ ወደዚህ ነጥብ ሲደርስ በክርስቶስ የተዘጋጀለትን መልስ ለመቀበል ዝግጁ ሆነ። ኃጢአት በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ተሸንፏል። ሕግ ተግባሯን እንድትፈጽም ከተፈቀደላት ሕግ ለእኔ ረዳት ነች። በክርስቶስ በኩል የኦሪት ሕግ ጠንካራ በመሆኗ በሥጋ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ትኮንናለች። ክርስቶስ ጻድቅ ስለሆነና በውስጣችን ስለሚኖር የእርሱ መታዘዝ የአማኞች መታዘዝ ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን አማኞች የሕይወትን መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ይፈጽማሉ (ሮሜ 7፡25–8፡4)።

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ትተውት የሸሹት ተከታዮቹ ይህን አዲስ እምነት በድፍረት ለማወጅ የበቁት ምን ቢለውጣቸው ነው? እነኚህ «መጻሕፍትን የማያውቁና ያልተማሩ» ሰዎች በዓለም ላይ ይህንን የመሰለ ፋና በማብራት በምዕራብ ሥልጣኔ ላይ ሙሉ በሙሉ አዲስ ባህልና ለውጥ እንዲፈጠር ያደረገው ምን ነበር?

ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ከማሳደድ ሙሉ በሙሉ ተመልሶ የወንጌላቸውን መልእክት እንዲያውጅ ያደረገው ኃይል ምንድን ነው?

ዛሬም በዓለም ላይ በመሥራት ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ የሚያቀርባቸው ይህ ኃይል ነው። ያም ኃይል የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

## ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ትንቢት የተነገረው በየትኛው የትንቢት መጽሐፍ ነው? ኢዩኤል 2፡28–32።
2. ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በውስጣቸው የታዩት ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው? የሐዋ. 4፡31–32።
3. በሐዋርያት መልእክት ውስጥ የተጠቀሱትን ሦስት ነጥቦች ስጥ። የሐዋ. 2፡14–40፤ 7፡1–53፤ 8፡35 እና 10፡34–43።
4. ወንጌል ለሰማርያ፥ ለአሕዛብና እንዲሁም ለአይሁዶች እኩል መሆኑን ሳያሻማ የሚያረጋግጠው ማስረጃ የቱ ነው? የሐዋ. 8፡14–17፤ 10፡44–45።
5. በቁሳዊ ነገር ክርስቲያን ለሌሎች ያለው ኃላፊነት ምንድን ነው? የሐዋ. 20፡35።

ግምታዊ የጳውሎስ ሕይወት የዘመን ተራ

# ክፍል አንድ

## ጳውሎስ ከጢሞቴዎስና ከቲቶ ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ወቅታዊ ሁኔታዎች | ጥቅሶች | ቀን |
|---|---|---|
| 1. ልደቱ | | በክርስቶስ ልደት አካባቢ |
| 2. የተለወጠው | የሐዋ.9፡1-19 | ከ33 ዓ.ም. |
| 3. የመጀመሪያው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ<br>ጢሞቴዎስ በደርቤን ተለወጠ፥ በለጋ ወጣትነቱ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። የገላትያ መልእክት የተጻፈው በዚህ ጉዞው መጨረሻ አካባቢ ከሶሪያዋ አንጾኪያ ሊሆን ይችላል። | የሐዋ.13፡1-14፡28 | 47-48 ዓ.ም. |
| 4. በኢየሩሳሌም ጉባኤ ቲቶ ጳውሎስን ተከተለው። | የሐዋ. 15፡1-35<br>ገላትያ 2፡1 | 49 ዓ.ም. |
| 5. ሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ<br>ጢሞቴዎስና ጳውሎስ<br>በመጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ የተደረገውን ጉዞ ያጠቃልላል። 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ የተጻፉት ከቆሮንቶስ ነው። | የሐዋ.15፡36-18፡22 | 49-52 ዓ.ም. |

# ክፍል ሁለት

## ከጢሞቴዎስና ከቲቶ ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ወቅታዊ ሁኔታዎች | ጥቅሶች | ቀን |
|---|---|---|
| 6. ሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ<br><br>ለ3 ዓመት ያህል ከጢሞቴዎስ ጋር በኤፌሶን ቆየ<br><br>በዚህ ጊዜ ቢያንስ መቄዶንያን ሁለት ጊዜ ጎብኝቷል፤ የሐዋ.20፡1-31፤ 2ኛ ቆሮ.2፡12-13።<br><br>ቲቶ በቆሮንቶስ ሲያገለግል<br><br>1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስና የሮሜ መልእክት የተጻፉት በዚህ ጉዞ ወቅት ነበር። | የሐዋ.18፡23-21፡17<br><br>2ኛ ቆሮ7፡6<br>7፡13፤ 7፡14<br>8፡6፥ 16፥ 23 | 52-56 ዓ.ም. |
| 7. በኢየሩሳሌም መታሰር | የሐዋ. 21፡18-23፡30 | 56 ዓ.ም. |
| 8. የጳውሎስ ፊስጦስና ፊሊክስ በተባሉ አገር አስተዳዳሪዎች ፊት መቅረብ | የሐዋ.23፡31-25፡12 | 56-58 ዓ.ም. |

# ክፍል 3

## ጳውሎስ ከጢሞቴዎስና ከቲቶ ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ወቅታዊ ሁኔታዎች | ጥቅሶች | ቀን |
|---|---|---|
| 9. በንጉሥ አግሪጳ ፊት መቅረብ | የሐዋ.25፡13–26፡32 | 58 ዓ.ም. |
| 10. የሮም ጉዞና አስራት ከእስር ቤት የተጻፉት መልእክቶች፥ ቈላስይስ፥ ኤፌሶን፥ ፊልሞና፥ ፊልጵስዩስ። | | 56–61 ዓ.ም. |
| 11. ከእስር መፈታት | ፊልጵ.1፡22፥25 | 62 ዓ.ም. |
| 12. ከተፈታ በኋላ እስከ ትንሹ እስያ ድረስ ያደረገው ጉዞ | | 62–66 ዓ.ም. |
| ጢሞቴዎስን በኤፌሶን ተወው 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡3 | | |
| ወደ መቄዶንያ ሄደ | | 62 ዓ.ም. |
| ለጢሞቴዎስ መልእክት ጻፈለት | | |
| ወደ ኤፌሶን ተመልሶ መጥቶ ሊሆን ይችላል። | | |

# ክፍል አራት

## ጳውሎስ ከጢሞቴዎስና ከቲቶ ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ወቅታዊ ሁኔታዎች | ጥቅሶች | ቀን |
|---|---|---|
| ወደ ቀርጤስ መሄድ<br><br>በቀርጤስ ቲቶን ተወው።<br>ቲቶ 1፡5<br>ወደ ቆሮንቶስ መሄድ<br><br>ለቲቶ መልእክት ጻፈለት<br>ሌሎች ጉዞዎች | | |
| 13. የሮም መቃጠል፥ ኔሮ በክርስቲያኖች ላይ ስደቱን እንዲያበዛ አደረገው<br>14. ሁለተኛው እስራት፡— በጢሮአዳ (?) | 2ኛ ጢሞ. 1፡16—17<br>4፡6—16 | 64 ዓ.ም.<br>66 ዓ.ም.<br>67 ዓ.ም. |
| 15. ሁለተኛው እስራት፡— በሮም<br>ሁለተኛውን መልእክት ለጢሞቴዎስ ጻፈ | | 67 ዓ.ም. |
| ሞት፡— በኔሮ ተገደለ | | 67 ዓ.ም. |

## የጳውሎስ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

| የጳውሎስ ልደት | በክርስቶስ ልደት አካባቢ |
|---|---|
| የጳውሎስ መለወጥ | 33 ዓ.ም. |
| የመጀመሪያው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 47-48 ዓ.ም. |
| ከመጀመሪያው ጉዞ በኋላ ገላትያ ተጻፈ | 48 ዓ.ም. |
| የኢየሩሳሌም ሐዋርያዊ ጉባኤ | 49 ዓ.ም. |
| ሁለተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 49-52 ዓ.ም. |
| በሁለተኛው ወንጌላዊ ጉዞ ላይ 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ተጻፉ | 52 ዓ.ም. |
| ሦስተኛው የጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞ | 52-56 ዓ.ም. |
| በሦስተኛው ወንጌላዊ ጉዞ 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ ተጻፉ | 55 ዓ.ም. |
| በሦስተኛው ወንጌላዊ ጉዞ ሮሜ ተጻፈ | 56 ዓ.ም. |
| በኢየሩሳሌም ታሰረ | 56 ዓ.ም. |
| ወደ ሮም ጉዞ | 60-61 ዓ.ም. |
| በሮም ከተማ ፍርድ ይጠባበቃል | 61 ዓ.ም. |
| ፊልሞን፥ ቈላስይስ፥ ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስ በእስር ቤት ተጻፉ | 61 ዓ.ም |
| የጳውሎስ መፈታት፥ አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘቱና የወንጌላዊነቱን ሥራ መቀጠል | 62-66 ዓ.ም. |
| 1ኛ ጢሞቴዎስና ቲቶ ተጻፉ | 62-65 ዓ.ም. |
| ጳውሎስ በሮም ታሰረ | 66-67 ዓ.ም. |
| 2ኛ ጢሞቴዎስ በእስር ቤት ተጻፈ | 67 ዓ.ም. |
| ጳውሎስ ተሰየፈ | 67 ዓ.ም. |